# አል-ኢማማህ

# IMAMATE

በ ሰይድ ሰዒድ አክተር ረደዊ

ትርጉም፡-

ጧሂር መሐመድ አል-ኀዳነምቢ

# አል-ኢማማህ

# IMAMATE

በ ሰይድ ሰዒድ አክተር ረደዊ

ትርጉም:-

ጣሂር መሐመድ አል-ጎዳነምቢ

**ማውጫ** **ገጽ**

## ክፍል 1 አጠቃላይ ግንዛቤ/ትርጉም

የኢማማህ እና የኺላፍ ትርጓሜ....3
የልዩነቶች ማጠቃለያ....5
መሰረታዊ ልዩነቶች....8
የኢስላማዊ አስተዳደር (መሪነት) ሥርዓት....15

## ክፍል ሁለት የሺዓዎች እይታ

የኢማማህ አስፈላጊነትና ለኢማምነት የሚያበቁ መስፈርቶች
- የኢማማህ አስፈላጊነት....22
- በላጭነት (አፍደሊያህ)....23
- ስህተት አልባነት (ዕስማህ) (እንከን የለሽነት)....24
- በአላህ መመረጥ....26
- የቁርአን አናቅፅ ማስረጃዎች....27
- ተዓምራት....33
- ቀደምት ታሪክ....34
- አሳማኝ ምክንያቶች....34

የኢማሞቹ እንከን የለሽነት....36
የዓሊ (ዐ.ሰ) ታላቅነትና የበላይነት....42
የዓሊይ መመረጥ....46

የአል-ዊላያ አንቀጽ (አያት አል-ዊላያህ) ........................................49
የገዲር ኹም ግልጽ አዋጅ ............................................................51
የገዲር ሐዲስ ሙተዋትር (ሰንሰለቱ ሳይቆረጥ በበርካታ ዘገባዎች የተገኘ መሆኑ)..........................................................................58
የገዲር ሐዲስ ሰነዶች (አስናድ)...................................................68
የ «መውላ» አጠቃላይ ትርጉም ...................................................71
የ«መውላ» ዐውዳዊ ትርጉም........................................................75
ዓሊ (ዐ.ሰ) የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «አካል» ..............................................80
ሀዲሶች .................................................................................83
ዑሉል አምር ከሀጢአት የፀዱ (መዕሱም) መሆን አለባቸው.........87
ኡሉል አምር ማለት የሙስሊም መሪዎች ማለት ነውን? ............96
የኡሉል አምር ትክክለኛ ፍቺ/ትርጉም........................................101
አስራ ሁለት ኸሊፋዎች ወይም ኢማሞች ..................................105
ስለ አሥራ ሁለቱ ኢማሞች በጥቂቱ/በአጭሩ............................108
የመጀመሪያው ኢማም...........................................................108
ሁለተኛው ኢማም..................................................................109
ሦስተኛው ኢማም .................................................................109
አራተኛው ኢማም ................................................................110
አምስተኛው ኢማም ..............................................................110
ስድስተኛው ኢማም...............................................................110
ሰባተኛው ኢማም ..................................................................111
ስምንተኛው ኢማም ..............................................................111
ዘጠነኛው ኢማም ..................................................................112

አሥረኛው ኢማም ............ 112
አስራ አንደኛው ኢማም ............ 112
አሥራ ሁለተኛው ኢማም ............ 113

## ክፍል ሦስት ኢማማህ በሱኒዎች ዕይታ

ኸሊፋነት (ኺላፈህ) በሱኒ ዕይታ ............ 115
ኸሊፋ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች ............ 118
የአቡ በክር ወደ ስልጣን መውጣት ............ 120
አጭር ዳሰሳ ............ 130
የዑመር መመረጥ ............ 138
አል-ሹራ (ጉባዔ/ምክር ቤት) ............ 144
ወታደራዊ ኃይል ............ 152
አጠቃላይ ዳሰሳ ............ 154
ተግባራዊ ጎኑ ............ 156
አል-ወሊድ እና ሃሩን አል-ረሺድ ............ 161
በአላህ ፍትሃዊነትና በነቢዮች እንከን-የለሽነት (እስመህ) እምነት ላይ ያለው ተጽዕኖ ............ 163
ሺዓነት ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነው? ............ 166
በዘር የሚተላለፍ ስልጣን? ............ 175

ዋቢ መጻሕፍት ............ 178

እጅግ በጣም ርህሩህና አዛኝ በሆነው በአላህ ስም

ምስጋና ለአላህ ነው። የአለማት ጌታ ለሆነው፣
እጅግ በጣም ርህሩህና እጅግ በጣም መሃሪ፣
የፍርድ ቀን ጌታ

አንተን ብቻ በአምላክ እንገዛለን
ለስኬታችን በሙሉ አንተን ብቻ እንታገዛልን።
ቅኑን መንገድ አንተ ምራን
የነዛን የባረካቸውን መንገድ ምራን
ከተቆጣህቸው ህዝቦች መንገድ ጠብቀን
ከአፈነገጡ ሰዎች አካሄድም ሰውረን

**አላህ ሆይ! የመልዕክተኞች አለቃና የመጨረሻው ነቢይ በሆነው መሐመድና ከእንከን ሁሉ ባጠራሃቸውና ባጸዳሃቸው ቤተሰቡ ላይ በረከትህን በብዙ አውርድባቸው፤ በሁሉም መልዕክተኞችና ነቢዮች ላይም እንዲሁ በረከትህን አብዛ!**

# ክፍል 1

# አጠቃላይ
# ግንዛቤ/ትርጉም

## የኢማማህ እና የኺላፍ ትርጓሜ

«አል-ኢማማህ» የሚለው ቃል በግርድፉ ሲታይ «መሪነት» ሲሆን «አል-ኢማም» ማለት ደግሞ «መሪ» እንደማለት ነው። በኢስላማዊ ስያሜው ደግሞ «አል-ኢማማህ» ማለት «የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተተኪ በመሆን ሃይማኖታዊም ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን አስመልክቶ ሁለንተናዊ ስልጣን የተጎናጸፈ» እንደማለት ሲሆን «አል-ኢማም» ማለት ደግሞ «ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)ን ተክቶ ሃይማኖታዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ባልሆኑ ጉዳዮች በሙሉ ላይ አጠቃላይ ስልጣን የተሰጠዉ ሰዉ» ማለት ሲሆን «ሰዉ» የሚለዉ ቃል በአረብኛዉና በእንግሊዝኛዉ አገባብ የወንድ ጾታ አመልካች በመሆኑ ሴት ለኢማምነት እንደማትታጭ ይገልጻል።

«አጠቃላይ ስልጣን» የሚለዉ ደግሞ የጸሎት (ሰላት) ኢማሞችን (መሪዎች) ከዚህ ዉጭ ያደርጋቸዋል። ምንም እንኳ የሰላት መሪዎችም ኢማሞች ቢባሉም ሁለንተናዊ ስልጣን ግን የላቸዉም። «የነቢዩ ተተኪ በመሆን» የሚለው ደግሞ በነቢዩና ኢማም መካከል ያለዉን ልዩነት ይገልጻል። ስለዚህ ኢማሙ ስልጣኑን የሚጠቀመዉ ቀጥታ (ከራሱ ሳይሆን የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምትክ ሆኖ ነዉ ማለት ነዉ።

«አል-ኺላፋህ» የሚለዉ ቃል ደግሞ «ተተኪነት » ማለት ሲሆን «አል-ኸሊፋህ» የሚለው ደግሞ «ተተኪ» ማለት

ነዉ:: በኢስላማዊ አገባቡ አል-ኺላፋህ እና አል-ኸሊፋህ የ አል-ኢማማህ እና አል-ኢማም አይነት ትርጉም አላቸው:: «አል-ዊሳያህ» ማለት «አደራ (ኑዛዜ) ተሰጪነት» እንደማለት ሲሆን «አል-ዋሲ» ማለት ደግሞ «አደራ (ኑዛዜ)ውን የሚፈጽም - ሀላፊነቱን የተረከበ» ማለት ሲሆን በሙስሊሞች ድርሳናት ዉስጥ ያላቸው ቦታ ኺላፋና ኸሊፋህ ካላቸው ቦታ ጋር ተመሳሳይ ነው:: በርካታ የሆኑት ቀደምት ነብያት የተቀዳሚው ተተኪ (ኸሊፋህ) እንደነበሩ ማስተዋል ያስፈልጋል:: ስለዚህ አብዛኛዎቹ ነቢይም ኸሊፋም የነበሩ ሲሆን አዲስ ህግጋትን (ሸሪዓን) ይዘው የመጡ ነቢያት ግን የቀደምት ነቢያት ተተኪ (ኸሊፋህ) አልተባሉም:: እንዲሁም ነቢይ ሳይሆኑ የነቢያት ተተኪ (ኸሊፋ) የተባሉ ሰዎች ነበሩ::

ይህ የኢማምነትና የኸሊፋነት ጉዳይ የሙስሊሙን ማህበረሰብ የከፋፈለና በብዙ ቡድኖች አስተሳሰብና ፍልስፍና ላይ ተጽዕኖ በማምጣት በአላህ አንድነት እምነት (ተውሂድ) በነቢይነት (ኑቡዋ) ላይ እንኳ ሳይቀር የተለያየ አስተሳሰብንና ልዩነት የፈጠረ ጥያቄ ከሆነ ሰንብቷል::

ይህ ጉዳይ በእስልምና በአስተምህሮት ውስጥ ለክርክር ከበቁት ርዕሶች ቀዳሚው ነው:: ኺላፋነትን በተመለከተ ሙስሊሞች እልፍ አዕላፍ መጽሐፍትን ጽፈዋል:: ከፊቴ የተደቀነው ችግር ምን መጻፍ አለበት ሳይሆን ምን መጻፍ የለበትም የሚለው ነው:: በእንዲህ አይነት አጭር ጽሁፍ ዉስጥ ስለ እያንዳነዱ ነገር በጥልቀት ማቅረብ ይቅርና

በርዕሱ ዙሪያ እንኳን ሁሉን መዘርዘር የማይሞከር ነገር ነው። ይህች አጭር ጽሁፍ ኺላፋነትን በተመለከተ ያሉትን መሰረታዊ ልዩነቶች ለመጠቀም ያህል ብቻ ነዉ።

ይህንን ጥያቄ በተመለከተ ሙስሊሞች በሁለት ጎራ እንደተከፈሉ ከወዲሁ ማሳወቅ የሚረዳ ይመስለኛል።

1. አቡበክር የመጀመሪያዉ የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋህ እንደሆነ የሚያምኑ ሱኒዎች፣
2. አሊ ኢብን አቡ ጧሊብ (ዐ.ሰ) የመጀመሪያው ኢማምና ኸሊፋ ነበር ብለው የሚያምኑ ሺዓዎች

ይህ መሠረታዊ ልዩነት ሌሎች ልዩነቶችን እንደወለደ በሚቀጥሉት ምዕራፎች ውስጥ ይገለጻል።

## የልዩነቶች ማጠቃለያ

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በሁሉም የኢስላም ቡድኖች ዘንድ ተቀባይነት ባለው (ሁሉም በሚስማሙበት) ሐዲስ እንደተናገሩት፡-
«የኔ ህዝብ (ኡማህ) በሰባ ሶስት ቡድኖች ይከፋፈላል። ከአንዱ ቡድን በስተቀር ሌላው በሙሉ ጠፊ ነው (የእሳት ነው)» ማለታቸው ይታወቃል።

ከጠፊዎቹ ቡድኖች ላለመሆን ትክክለኛዉን መንገድ ለማግኘት፤ መዳን የሚሹና ይህ ክፍፍል መኖሩ ያሳሰባቸው

ሁሉ ሳይታክቱ የዚችን የአንዷ ቡድን ቅን መንገድ ለማግኘ ት ሌት ተቅን ሲለፉ ኖረዋል፡፡

በእርግጥም ይህ የእንያንዳንዱ ሰው አንገብጋቢ ጥያቄ መሆንና ሰዎች ሁሉ ምክንያት ማስረጃን መሪያቸዉ አድርገዉ ሁኔታውን በማመንና በማጥናት እዉነቱ እስኪጋለጥ ድረስ መታከት የግድ ማለቱ አማራጭ የሌለዉ እርምጃ መሆን አለበት፡፡ እዉነታው እስኪታወቅ ድረስ ደግሞ ወደ ኋላ መመለስና ተስፋ መቁረጥ ፈጽሞ አይገባም፡፡

ይህ መሆን የሚችለዉ ግን መጀመሪያ ያለዉን መሰረታዊ ልዩነትና የልዩነቱ መንስኤዎች ምን እንደሆኑ በግልጽ ሊታወቅና ግላዊ ስሜትና በአሉባልታ ላይ የተገነባ ኢ-ምክንያታዊ የሆነ ስሜታችንን ገተን በንጹህ ልቦናና አስተዋጽኦ አዕምሮ ነገሮችን በማስረጃ ነጥብ በነጥብ ስንመረምርና እውነታውን የመቀበል ዝግጁነትና ጭፍንነትን ስናስወግድ መሆኑን ቀድሜ ማስቀመጥ እፈልጋለሁ፡፡

በመሆኑም ያለውም መሰረታዊ ልዩነትና ግጭት እንዲሁም እያንዳንዱ ቡድን የሚያስቀምጠውን ማስረጃ ክርክር እና ምክንያት ጭምር ቀድሞ ማሳወቁ ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡
ዋና ዋና ጥያቄዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. የእያንዳንዱ ነብይ ምትክ (ኸሊፋህ) የመምረጥና ስልጣን የመስጠቱ ጉዳይ የአላህ ፍቃድ ነው ወይስ የፈለጉትን ሰው የነብይ ምትክ አድርገው የመምረጡ መብት የህዝቡ (ኡማው) ነው?

2. በሌላው መንገድ ደግሞ፣ አላህ ወይም ነብዩ ህዝቡ ኸሊፋህ እንዴት መምረጥ እንደሚችሉ የሚገልጽ ህግና መመሪያ ለህዝቡ ያስቀመጡት ነገር አለ ወይስ ህዝቡ በራሱ ኸሊፋህ ከመምረጣቸው በፊት ያረቀቁትና የተስማሙበት ህግና ደንብ አለ ወይስ ህዝቡ በጊዜው ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት በማድረግና በተገኘው አጋጣሚ መሠረት ውሳኔውን ወሰኑ? ይህንንስ የማድረግ መብት ነበራቸው ወይ?

3. የተወሳ ነገር ኢማምና ኸሊፋህ ለመሆን የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎችና ተፈላጊ ችሎታዎች መኖር እንዳለባቸው (ምክንያታዊ ገለፃም ሆነ ሰማያዊ ህግ) ይኖር ይሆን? ካሉ ምንድን ናቸው?

4. የአላህ መልዕክተኛ ኸሊፋቸውን መርጠዋል፣ አልመረጡም? መርጠው ከሆነ ማንን ነበር? ካልመረጡ ለምን?

5. ነቢዩ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለዩ በኋላ የሳቸው ኸሊፋ (ተተኪ) ሆኖ ይታወቅ የነበረው ማን ነው? ለኸሊፋነት የሚያበቁ ሁኔታዎች መለያና ችሎታስ ነበረው?

**መሰረታዊ ልዩነቶች**

የኢማማህና ኺላፋህን ሁናቴ ተፈጥሮና ባህሪ ቀድሞ መግለጽ ጊዜ የሚቆጥብ ይመስለኛል። የኢማምነት ዋና ባህሪ ምንድን ነው? በመጀመሪያ ደረጃ ኢማም ማለት የአንድ ግዛት ገዢ ወይም መሪ ወይም ንጉስ ማለት ነው? ወይስ በምድር ላይ የአላህና የነቢዩ ምትክ ነው?

ኢማማህና ኺላፋ የነቢዩ ምትክነት ተብሎ እስከታመነ ድረስ ከላይ የተጠቀሱ ጥያቄዎች መልስ የሚያገኙበት በመጀመሪያ የነቢዩን መሠረታዊ ባህርያት ላይ ውሳኔ ሲሰጥ ብቻ ነው። በመጀመሪያ ነቢዩ የንጉሳዊ ግዛት መሪ (አስተዳዳሪ) ነበሩ ወይስ የአላህ ምትክ ወይም ወኪል ነበሩ? በሚለው ላይ የግድ ውሳኔ መስጠት አለብን።

በእስልምና ታሪክ ውስጥ የነቢዩን ተልዕኮ ንጉሳዊ መንግስት/ ግዛትን ለመፍጠር የተሞከረ እርምጃ አድርገው የወሰዱ ቡድን እንደነበረ እናውቃለን። የዚህ ቡድን አይታና አስተሳሰብ ቁሳዊ፣ ሀብት፣ ውበትና ሀይል ነበር። የነቢዩን ተልዕኮ አላማም በዚህ ሁኔታ ነበር የተገነዘቡት።
በጊዜው የነበረውን ቁሳዊና የድንቁርና አስተሳሰብ በተገነዘቡት አኳኋን ነበር የነቢዩንም ተልዕኮና ተግባር የተረጎሙት።

የአቡ ሱፍያን አማች የነበረው ዑትባህ ኢብን ረቢአህ የቁረይሾችን መልዕክት ለነቢዩ ለማድረስ ተልኮ ነበር።

«ሙሐመድ! የምትፈልገው ነገር ዕውቅናና ስልጣን ከሆነ፣ በመካ ላይ ጌታ እናደርግሃለን። ከተከበረ ቤተሰብ የሆነች ሚስት ማግባት ከፈለግክም በሀገሩ አለች የምትባል ውብ ሴት እንድርልሃለን። የብርና የወርቅ ክምችትም የምትሻ ከሆነ ከዚህም በላይ ለማድረግ ዝግጁ ነን። ነገር ግን እነዚህን ጣዖታትን ሲያመልኩ የኖሩትን አያቶቻችንን የሚያዋርድ ይህን ስብከትህን ብቻ አቁምልን።»

ቁረይሾች ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ሐሳባቸውን በደስታ እንደሚቀበል እርግጠኞች ሆነው ይጠባበቁ ነበር። ነገር ግን ቅዱሱ ነቢይ(ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለው አያህ ያለበትን ከሱራ 41 በመቅራት ነበር ምላሽ የሰጡት።

فَإِنْ أَعْرَضُوا فَقُلْ أَنْذَرْتُكُمْ صَاعِقَةً مِثْلَ صَاعِقَةِ عَادٍ وَثَمُودَ﴿١٣﴾

«***(ከእውነታው) የሚያፈነግጡ (የሚዞሩ) ከሆነ በአድና ሰሙድ ህዝቦች ላይ በወረደው ዓይነት የመብረቅ ቁጣ አስጠነቅቃችኋለሁ።***»

ዑትባህ በምላሹ እጅግ ተገርሞ ነበር። በማስጠንቀቂያው ግልፅነትና ቆራጥነት ተደናግጦ ክው አለ። እስልምናን ባይቀበልም ቁረይሾች ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲተዉትና ከሌሎች ጎሳዎች ጋር ተጋፍጦ ጉዳዩን የት እንደሚያደርስ ከዳር ሆኖ ብቻ መታዘብ እንዳለባቸው መከራቸው። በዚህን

ጊዜ ሙሐመድ በዑትባህ ላይም ድግምት ሰርቷል ብለው ደመደሙ፡፡ *(ሲራህ ኢብን ሂሻም 1፡ 313-4)*

ዑትባህ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለሌሎች ጎሳዎች እንዲተዉ ፈለገ፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜና ቁረይሾች በተከታታይ ጦርነት ሲያውጁባቸው ሌሎቹ ጎሳዎችም ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ለራሱ ጎሳዎች ቢተው ተመራጭ ነው ብለው ይመካከሩ ነበር፡፡

የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባ የሆነው አምር ኢብን ሰልማህ የሚከተለውን እንደተናገረ ይነገራል፡፡

*«አረቦች የቁረይሾችን እስልምና መቀበል ይጠባበቁ ነበር፡፡ ሙሐመድን ለራሱ ጎሳዎች መተው አለብን፡፡ በእርግጥ በቁረይሾች ላይ ድልን መቀዳጀት ከቻልን ያኔ ያለጥርጥር እውነተኛ ነብይ መሆኑ ይረጋገጣል ብለው ይናገሩ ነበር፡፡ መካ የተከፈተች ጊዜ ሁሉም ጎሳዎች በጥድፊያ ወደ እስልምና ይጎርፉ ገቡ፡፡» (ሰሂህ ቡኻሪ 7፡119፣ ኢብን ከሲር አል-ቢዳያህ ወ አል-ኒሃያህ 7፡40)*

ስለዚህ በነርሱ አስተሳሰብ መሠረት ድል ማድረግ ወይም ማሸነፍ ለእውነተኛነት እንደ ምክንያት የሚቀርብ ነገር ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተሸንፈው በነበር እንደ ውሸታም ይቆጠሩ ነበር ማለት ነው፡፡

ይህ የተቀደሰ የነብዩ ተልዕኮ ከዓለማዊ ጉዳይ ሌላ ምንም እንዳልነበረ በአቡ ሱፍያንና በጎሳው አባላት በተደጋጋሚ ይነገር ነበር።

መካ በሙስሊሞች እጅ በገባች ጊዜ አቡ ሱፍያን የሙስሊሞችን የሀይል ጭፍራ ሁኔታ ለማጤን ብሎ ከመካ ወጣ ብሎ ይጠባበቅ ነበር። በዚህን ጊዜ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት አል-አባስ አቡ ሱፍያንን ያየዋል። ከዚያም አል-አባስ አቡ ሱፍያንን ወደ ነብዩ ወሰደውና ምናልባት እስልምናን ይቀበል ይሆናል በሚል ዓላማ ደህንነትና ከለላ እንዲሰጠው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) አማከራቸው።

ነገሩን ጠቅለል አድርጎ ለመናገር አል-አባስ አቡ ሱፍያንን ይዞ የሙስሊሙን ጭፍራ ሁኔታ ማስቃኘት ጀመረ። በጭፍራው ውስጥ የነበሩትን ከተለያዩ ጎሳዎች የተውጣጡ ታዋቂ ሰዎችን ጭምር እያዞረ አሳየው። በዚሁ ወቅት አረንጓዴ ልብስ የለበሱ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የነበሩትን ቡድን ሲያልፍ ተመለከተ። በዚህን ጊዜ አቡ ሱፍያን በአግራሞት ጮክ ብሎ፡-

«*አባስ ሆይ! ኧረ ጉድ ነው! የአጎትህ ልጅ ትልቅ ግዛት (ንጉሳዊ) ይዞ የለም እንዴ?!*» አለ።

አል-አባስ ሲመልስ፡ «*ወየውልህ! ይህ ንግስና አይደለም። አንተ እንደምታስበው ንጉሳዊ መንግስት አይደለም። ይህ ነብይነት ነው።*» አለው። *(አቡል ፊዳ፡ አል-መክተሰር 1:143 - 144፣አል- ያዕቁቢ፣ አል-ታሪክ 2:59)*

እዚህ ላይ ሁለት ተቃራኒ አስተሳሰቦችን በግልጽ ንጽጽር እናስተውላለን፡፡ አቡ ሱፍያን አስተሳሰቡን በፍጹም እንዳልቀየረ እናያለን፡፡ ኡስማን የኸሊፋነቱን ስልጣን እንደተረከቡ በአንድ ወቅት አቡ ሱፍያን ወደ ኡስማን በመምጣት እንዲህ በማለት እንደመከረው ተዘግቧል፡፡

*«የኡመያህ ልጆች ሆይ! እነሆ አሁን ንግስናውና ግዛቱ በእጃችሁ ገብቷል፡፡ ልጆች በኳስ እንደሚጫወቱ ደህና አድርጋችሁ ተጫወቱበት፡፡ ከዚያም በትረ ስልጣኑን ጎሳችሁ ለሆኑት አስተላልፉ፡፡ አንዱ ለአንዱ ያስተላልፍ፡፡ ይሄ ነው እውነታው! ጀነትም (ገነትም) ሆነ ጀሀነም (ገሀነም) ይኑር አይኑር የምናውቀው ነገር የለም፡፡»*

*(ኢብን አብዱል በር፡- አል-ኢስቲዓብ ቅጽ 4፡ ገጽ 1679፣ ኢብን ኢቢል ሀዲድ የመጨረሻውን የአቡ ሱፍያን አባባል እንደሚከተለው ጠቅሶታል፡- «በርሱ አቡ ሱፍያን በሚምለው ይሁንብኝና ቅጣትና ሒሳብ የሚባል ነገር በጀነት ወይም ጀሃነም እንዲሁም ከሞት መቀስቀስና የፍርድ ቀን የሚባል ነገር ሁሉም የሉም፡፡» (ሸርህ ነህጁል በለጋህ 9:53))*

ከዚያም ወደ እሁድ ሄዶ የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የሆኑትን የሀምዛን መቃብር በእግሩ ከረገጠ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ፡-

*«አንተ አቡ ያዕላ! በጽኑ የተፋለምክለት ስልጣን የማታ ማታ በእጃችን እንደገባ ይታይሃል?! ብሎ አሳገጠ።»* (*ኢብን አብል ሀዲድ 16:136*)

የአቡ ሱፍያን የልጅ ልጅ የሆነው የዚድም ይህንኑን የአያቱን አስተሳሰብና እምነት እንደደገመ ታሪክ አስፍሯል።

لعبت هاشم بالملک فلا خبر ولا وحی نزل

«ለዒበት ሀሺሙ ቢልሙልክ ፈላ ኸበሩን ጃአ ወላ ወህዩን ነዘል»

(*ሲብጥ ኢብኑል ጀዉዚ፦ ተዝክረህ-ባህሩል ዑሉም፡ ገፅ 261፣ አል-ጠበሪ፦ አል-ታሪክ 13: 2174*)

*«የሐሺም ልጆች እንዲሁ በስልጣን (ንግስና) አፌዙ። የመጣ ዜናም (ኸበርም) ሆነ የወረደ ወህይ የሚባል ነገር የለም።»*

እንግዲህ በማንኛውም ሙስሊም ውስጥ ያለው አስተሳሰብ እላይ የተገለጸው አይነት ከሆነ የኢማማህ አስተዳደር ሥርዓትና የንጉሳዊ አገዛዝን መንግስት በአንድ እይታ ለማየት ይገደዳል ማለት ነው። በእንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መሰረት የነብዩ ዋነኛ ተግባር ስልጣንን ተቆናጦ ግዛትን ማስፋት ስለሆነ ማንኛውም ስልጣን መቆናጠጥ የሚችል አካል ወይም ግለሰብ ትክክለኛው የነብዩ ተተኪ ወይም ኸሊፋህ መሆን ይችላል ማለት ነው።

ነገር ግን ቆም ብለን ስናስበው ይህንን አስተሳሰብ ትልቅ ችግር ይገጥመዋል፡፡ ይኸውም ከተጨባጭ ታሪክ እንደሚታየው ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑ ነብያት የፖለቲካ ስልጣንና ሃይል አልነበራቸውም፡፡ አብዛኞዎቹ ነብያት በጊዜያቸው በነበሩ ሃያላን መንግስታትና ገዢዎች ይሳደዱና የባለ ስልጣናቱ ሰለባ እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ክብራቸው ዘውድና ዙፋን አልነበረም፡፡ እጣ ፈንታቸው ሰማዕትነትና መሰቃየት ነበር፡፡ የነብይነት ዋነኛው ባህሪና መገለጫው የፖለቲካ ስልጣንና ንጉሳዊ ግዛት ቢሆን ኖሮ ከ 124,000 ነብያት ለ50ዎቹ እንኳን የነብይነትን ማዕረግ ማቆየት የማይቻልበት ሁኔታ ነው ያለው ማለት ነው፡፡

ስለዚህ በማያሻማ ሁኔታ የምንረዳው ነገር ቢኖር የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) መሠረታዊ መገለጫ የፖለቲካ ስልጣንና ንግስና ሳይሆን በምድር ላይ የአላህ ኸሊፋ (ወኪል) ነበሩ፡፡ ይህ ኸሊፋነት ደግሞ የተሰጣቸው በህዝባቸው ሳይሆን በራሱ በአላህ ነው፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የነብዩ ተተኪ ባህሪና ተልዕኮም የፖለቲካ ስልጣን ሊሆን አይችልም፡፡ በእርግጥ ነብዩንም የሚተካው ኸሊፋ በምድር ላይ የአላህ ወኪል (ኸሊፋ) በመሆኑ ኸሊፋነቱ የሚሰጠው በህዝቡ ሳይሆን ከራሱ ከአላህ ነው ማለት ነው፡፡ በአጭሩ አንድ ኢማም (መሪ) አላህን የሚወክል ከሆነ የግድ በአላህ መመረጥ አለበት ማለት ነው፡፡

## የኢስላማዊ አስተዳደር (መሪነት) ሥርዓት

በአንድ ወቅት ዘውዳዊ አገዛዝ በህዝቡ ዘንድ የሚታወቅ ብቸኛው የአስተዳደር ወይም የመንግስት ዓይነት ነበር። በዛን ወቅት የሙስሊም ምሁራን አላህ ጥላ እንዳለው አድርገው «*ንጉስ የአላህ ጥላ ነው*» እያሉ ነገስታቱንና ዘውዳዊ መንግስትን ያወድሱ ነበር። አሁን አሁን በዘመናዊው ወቅት ደግሞ «ዲሞክራሲ» የሚለው ቃል ፋሽን ሆኖ ብቅ አለ። የሱኒ ምሁራን ደግሞ በሺዎች በሚቆጠሩ መጽሐፍት፣ ጥንታዊ ጽሁፍ አርትክሎችና የስምምነት መረጃዎችን በመጻፍና በማጣቀስ የኢስላማዊ መንግስት ስርዓት በዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ለመግለጽና ለማስረዳት ታክተው አያውቁም። እንዲያውም ዲሞክራሲ የተመሠረተው በኢስላም ላይ ነው እያሉ ፈጥነው ሲናገሩ ይስተዋላል። የግሪክን ሲቲ ሪፐብሊኮች የረሱ ይመስላሉ።

በዚህ ምዕተ አመት ሁለተኛው አጋማሽ ሶሻሊዝምና ኮሚኒዝም ያላደጉና በማደግ ላይ ያሉትን ሐገሮች የተቆጣጠረበት ጊዜ በመሆኑ ታዋቂ ብለው ሲናገሩ ብሰማ ብዙም አያስደንቀኝም። ፓክስታንና ሌሎች ቦታዎች የሚገኙ አንዳንድ ሰዎች «እስላማዊ ሶሻሊዝም» የሚል መፈክር ፈጥረዋል። ይህ «እስላማዊ ሶሻሊዝም» ምን ማለት እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን በአስር ወይም ሃያ ዓመታት ውስጥ ደግሞ እነዚሁ ሰዎች እስልምና «ኮሚዩኒዝም»ን ያስተምራል የሚል አቋም ቢይዙ አሁንም አይደንቀኝም።

ይህ «ነፋስ ወደነፈሰበት የማንጋለል» ሁኔታ በእስልምና የአስተዳደር ስርዓት ላይ ማፌዝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በአንድ ወቅት በአንድ የአፍሪካ አገር፣ የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የክብር እንግዳ በነበሩበት ስብሰባ ላይ በርካታ ሙስሊሞች በተሰበሰቡበት አንድ የሙስሊም መሪ እስልምና የሚከተለውን አስተሳሰብ እንደሚያስተምር እንዲህ ሲል አስተማረ:

*«አላህን ታዘዙ፣ መልዕክተኛውንና መሪዎቻችሁንም ታዘዙ፡፡»*

ፕሬዚዳንቱ (በአጋጣሚ ታማኝ የሮማ ካቶሊክ የሆኑ) ሲመልሱ አላህንና ነብዩን (መልዕክተኛውን) መታዘዙን ህግ ካደነቁ በኋላ መሪዎችን የመታዘዙ ምክንያታዊ ገለጻ እንዳልገባቸው ተናገሩ፡፡ መሪው ፍትሃዊ ካልሆነና አምባገነን ከሆነስ? ሙስሊሞች ያለምንም ተቃውሞ ቀጥ ለጥ ብለው መታዘዝ እንዳለበት እስልምና ያስገድዳል?

ይህ በሳል የሆነ ጥያቄ በሰል ያለ መልስ ይጠይቃል፡፡ ቀላል ተደርጎ የሚታይ ጥያቄ አይደለም፡፡ እውነታው ለዚህ ትችት የተጋበዘው ሰው ወይም ለትችቱ በር የከፈተው ሰውየው ለቁርአን የተሳሳተ ትርጓሜ ወይም ማብራሪያ በመስጠቱ ነው፡፡

እስቲ የኢስላማዊ አስተዳደር ሥርዓትን እንመርምር፡፡ ዲሞክራሲያዊ ነው? በጣም ጥሩ የሚባል «የዲሞክራሲ»

**ድፍየና (ትርጓሜ) የሰጠ 16ኛው የአሜሪካን ፕሬዚዳንት (1861 - 65) የነበረ አብርሃም ሊንከን ነበር፡፡ እንዲህ በማለት ነበር የተረጎመው፡-**

«*በህዝቡ ለህዝቡ የህዝቡ መንግስት*»

**ነገር ግን በእስልምና ውስጥ «የህዝቡ መንግስት» የሚባል ነገር የለም፡፡ የህዝቡ ሳይሆን «የአላህ መንግስት» ነው፡፡ ህዝቦች ራሳቸውን እንዴት ነው የሚያስተዳድሩት? የራሳቸውን ህግ በማውጣት ራሳቸውን ይገዛሉ/ያስተዳድራሉ? በእስልምና ውስጥ ግን ህግ አውጪዎች ሰዎች ሳይሆኑ አላህ ነው፡፡ እነዚህ ህግጋት ደግሞ ለህዝቡ የሚደርሱትና ተፈጻሚነት የሚያገኙት በህዝቡ ፍላጎትና አዋጅ ሳይሆን በአላህ ትዕዛዝ በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት ነው፡፡ ህግን በማውጣቱና በማርቀቁ ላይ ህዝቡ ምንም ድርሻ የለውም፡፡ ህግጋቱን በተመለከተ ህዝቡ ከመቀበልና ከመታዘዝ ውጭ አስተያየትና ሃሳብ መስጠት አይችሉም፡፡**

وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ وَلَا مُؤْمِنَةٍ إِذَا قَضَى اللَّهُ وَرَسُولُهُ أَمْرًا أَنْ يَكُونَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ مِنْ أَمْرِهِمْ

«***አላህና ነብዩ በአንድ ጉዳይ ላይ ፍርድ ከሰጡ ለወንድም ለሴት ምዕመናን ሌላ አማራጭ መሻት አይገባም፡፡***» **(ቁርአን 33:36)**

በህዝቡ ወደሚለው አባባል ስንመጣ ደግሞ እስቲ ህዝቡ ራሱን እንዴት እንደሚያስተዳድር እናስብ፡፡ ይህንን የሚያደርጉት መሪ የሚሆናቸውን ሰው መምረጥ ነው፡፡ እስልምናን መንግስት በአጠቃላይነት ህግጋቱንና በአጠቃላይ ጉዳዮችን አስመልክቶ በከፍተኛ አመራርነት የማስተዳደርና የመምራት ሃላፊነት የተሰጣቸው ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በህዝቡ አልተመረጡም ነበር፡፡ በእርግጥ የመካ ሰዎች የመምረጥ መብታቸው ቢጠበቅላቸው ኖሮ የጧኢፍን ኡርዋህ ኢብን መስዑድ ወይም የመካውን አል-ወሊድ ኢብን አል-ሙጊራህ የአላህ ነብይ አድርገው በመረጡ ነበር፡፡ የተከበረው ቁርአን እንዲህ ይገልጻል፡-

وَقَالُوا لَوْلَا نُزِّلَ هَٰذَا الْقُرْآنُ عَلَىٰ رَجُلٍ مِنَ الْقَرْيَتَيْنِ عَظِيمٍ﴿٣١﴾

«***ለመሆኑ ይህ ቁርአን ከሁለቱ ከተሞች በታወቁ አንድ ሰው ላይ ለምን አልተወረደም ነበር?***» **(ቁርአን 43:31)**

**(*ለተጨማሪ ማብራሪያ አል-ሱዩጢ፡- ሉባብ አል-ኑቁል ፊ አስባብ አል-ኑዙል በተፍሲር አል-ጀላለይን ጋር የታተመውን በገጽ 298: 649 ይመልከቱ*)**

ስለዚህ ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለኢስላማዊ መንግስት ከፍተኛ መሪነት ህዝቡ ሳይማከርበት የተመረጡ ብቻ ሳይሆን ምርጫው የተፈፀመው የህዝቡን ፍላጎትና ምኞት በሚፃረር መልኩ ነበር ማለት ነው፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የእስላምን የመጨረሻው ከፍተኛ አመራርነት የተረከቡ ናቸው፡፡ ህግን

የማርቀቅን፣ የመፈፀምን እንዲሁም ፍርድና ውሳኔ የማስተላለፍን ተግባራት ቅርንጫፎች በአንድ ጠቅልለው የያዙ መሪ ነበሩ፡፡ ነገር ግን የተመረጡት በህዝቡ አልነበረም፡፡

ስለዚህ ኢስላም የህዝብ መንግስትም አይደለም፣ ከህዝብ የመነጨ መንግስትም አይደለም፡፡ ከህዝብ የሆነ ህግ የለም፡፡ የህግ ፍጻሜና የፍርድ አሰጣጥም ህዝቡን በኃላፊነት የሚጠቅስ አይደለም፡፡ ለነገሩ «ለህዝብ የሆነ መንግስትም» አይደለም፡፡

ኢስላማዊ ስርዓት ከመጀመሪያ እስከ ፍፃሜው «ለአላህ» ነው፡፡ ሁሉም ነገር መተግበር ያለበት ለአላህ ነው፡፡ ለ «ሰዎች» ተብሎ የሚሰራ ከሆነ «ድብቁ/ስውሩ ሽርክ/ማጋራት» ይባላል፡፡ ማንኛውም የሚሰራ ነገር፣ ስግደትም ሆነ ልግስና፣ ማህበራዊ አገልግሎት ሆነ የቤተሰብ ኃላፊነትን መወጣት፣ ለወላጆች መታዘዝም ሆነ ጎረቤትን መውደድ፣ ፀሎት መምራትም ሆነ በአንድ ጉዳይ ላይ ፍርድ መስጠት፣ ወደ ጦርነት መግባትም ሆነ ወደ ሰላም ስምምነት መግባት፣ ሁሉም መሰራት ያለበት «ቁርበተን ሊላህ» (ወደ አላህ ለመቅረብ) ና የአላህን ውዴታ ለማግኘት ተብሎ መሆን ይኖርበታል፡፡ በኢስላም ሁሉም ነገር ለአላህ ነው፡፡

በአጭሩ የኢስላማዊ ስርዓት ያለው መንግስት አላህ በወከለው/ በመረጠው የሚመራ ለአላህ ውዴታ የሚሰራ የአላህ መንግስት ነው።

وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴿٥٦﴾

«***ጋኔንም ሆነ ሰዎችን (የፈጠርኳቸው) እንዲገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።***» **(ቁርአን 51፡56)**

የኢስላም መንግስት «ኃይማኖታዊ» መንግስት ነው። የእስልምና አስተዳደር ተፈጥሮና ባህሪ እንዲህ ነው። «መታዘዝ»ንና «መገዛት»ን በተመለከተ እላይ የተጠቀሰውን የቁርአን ጥቅስ ትርጉም ላይ ያለውን እንድምታ በቀጣይ ምዕራፎች እናያለን።

# ክፍል ሁለት

# የሺዓዎች እይታ

## የኢማማህ አስፈላጊነትና ለኢማምነት የሚያበቁ መስፈርቶች

### የኢማማህ አስፈላጊነት

በሺዓዎች እይታ የኢማማህ ተቋም በምክንያት ላይ የተመሠረተ አስፈላጊ ተቋም ነው፡፡ ኢማማህ ሰዎች በምንም መልኩ ሳይገደዱ ወደ መታዘዝ የሚመጡበትና ካለመታዘዝ ወይም ከእምቢተኝነት የሚጠበቁበት የአላህ ሉጥፍ (ፀጋ) ነው፡፡

አላህ ሉጥፍን በራሱ ላይ «ግዴታ» እንዳደረገ በሺዓዎች አስተምህሮ ተረጋግጧል፡፡ አላህን ሰው አንድን ተግባር እንዲፈፅም በሚያዝበት ጊዜ ሰው ያንን ትእዛዝ ያለ እርሱ እርዳታና ድጋፍ ማድረግ አለመቻሉን እያወቀ ትእዛዙን እንዲቀበል የሚያስገድድ ከሆነ የራሱን ዓላማ እየተቃረነ ነው ማለት ነው፡፡ በርግጥ እንዲህ ዓይነቱ ችላ ባይነት ምክንያታዊ ሆነን ስናጤነው ክፉ ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ ሉጥፍ በአላህ ላይ ግዴታ ነው፡፡

ኢማማህ ሉጥፍ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የሚታዘዙት፣ የተጨቆኑትን የሚክስ፣ የጨቋኞችን ተግባር የሚገታና የሚቀጣ ኃላፊ (ረኢስ) ና መሪ (ሙርሺድ) ሲኖራቸው ከሙስና የፀዱና ወደ ፅድቅ ጎዳና የቀረቡ ዜጋ ይሆናሉ፡፡

ስለዚህ ሉጥፍ ስለሆነ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ህዝቡን የሚመራና የሚያስተዳድር ኢማም መምረጥ በአላህ ላይ «ግዴታ» ነው፡፡ (*አል-ዓላማህ አል-ሂሊ፦ አል-ባቡል ሃድ ዓሸር፣ የእንግሊዝኛ ትርጉም* W.M Miller, *ገፅ 50;60-4*)

**በላጭነት (አፍደሊያህ)**

ሺዓዎች እንደሚያምኑት አንድ ኢማም፣ ልክ እንደ ነብይ፣ ህዝቡን በሁሉም ትሩፋቶች፦ ለምሳሌ በዕውቀት፣ በጀግንነት፣ በፅድቅ፣ በልግስና በልጦ መገኘትና እንዲሁም ሰማያዊ ህግ በተመለከተ የተሟላ ዕውቀትና ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፡፡

ይህ ሳይሆን ሲቀርና ለዚህ ከፍተኛ ቦታ የሚገባ ሰው እያለ መስፈርቶችን ለማያሟላ ዝቅተኛ ሰው መሰጠት ከበላጩ ይልቅ ለዝቅተኛው ቅድሚያ መሰጠቱ ስለሆነ ይህ ደግሞ ምክንያታዊ አስተሳሰብን ሆነ ሰማያዊ ፍትህን የሚጻረር ነው። ስለዚህ ኢማምነት (መሪነት) መስፈርቱን የሚያሟላ፣ ቦታው የሚገባው በላጭ ሰው እያለ ለተበለጠው ሰው ሀላፊነቱን አሳልፎ መስጠት የማይሆን ነገር ነው ማለት ነው፡፡

(*ቀደም ሲል የተጠቀሰው ምንጭ ገጽ 69*)

**ስህተት አልባነት (ዕስማህ)          (እንከን የለሽነት)**

ሁለተኛው መስፈርት ደግሞ ዕስማህ ወይም እንከን የለሽ መሆን መቻል ነው፡፡ ኢማሙ ስህተት አልባ ወይም እንከን የለሽ (መዕሱም) ካልሆነ ለስህተት የተጋለጠና ሌሎችንም ሰዎች የማሳሳትና የማታለል አደጋ ውስጥ የወደቀ ይሆናል፡፡ (*ቀደም ሲል የተጠቀሰው ምንጭ፣ ገፅ 69*)

ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ኢማሙን የሚናገራቸውን ነገሮችና የሚያስተላልፋቸውን ትዕዛዛት ያለ ጥርጣሬ መቀበል አዳጋች ይሆናል ማለት ነው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ኢማሙ የህዝቡ የበላይ መሪና ገዢ ስለሆነ ህዝቡ ያለምንም ማወላወል በሁሉም ጉዳዮች ላይ ኢማሙን መከተልና መታዘዝ ሊኖርባቸው ነው፡፡ እንግዲህ አሁን ለምሳሌ ኢማሙ ቢሳሳትና ኃጢአት ቢሰራ ህዝቡ ከነኃጢአቱ በመከተልና በመታዘዝ ችግር ውስጥ ሊገቡ ነው ማለት ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ ለመጋፈጥ የማይቻል ሁናቴ አግባብነት የሌለው መሆኑ የማያሻማ እውነታ ነው፡፡ ለጥፋትና ለሀጢአት መታዘዝ እርኩስ፣ የማይፈቀድና ፍፁም የተከለከለ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ሁኔታ ካለ ኢማሙን በተመሳሳይ ወቅት የመታዘዝም ያለመታዘዝም ሁኔታ

ይፈጠራል ማለት ነው። ይህም ማለት ኢማሙን መታዘዝ ግዴታም የተከለከለም ይሆናል ማለት ነው። ይህ ደግሞ ትርጉም የሌለው አስተሳሰብ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ አንድ ኢማም ለጥፋት ወይም ለሀጢአት የመዳረግ ሁኔታ ካለ ከጥፋቱ ይታቀብ ዘንድ ህዝቡ ኢማሙን የመገሰፅ ግዴታ አለባቸው ማለት ነው። ምክንያቱም በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ በበጎ ነገር የማዘዝና ከመጥፎ ተግባር የመከልከል ግዴታ አለበትና። እንዲህ ከሆነ ደግሞ ኢማሙ በመጥፎ ነገር ይጠራና በህዝቡ ውስጥ ከነበረው ከፍተኛ ቦታ ወርዶ በዝቅተኛነት ይታያል ማለት ነው። ህዝቡን ከመምራት ይልቅ የህዝቡ ተከታይ ወይም ታዛዥ ይሆንና መሪነቱ ጥቅምና ትርጉም ያጣ ይሆናል።

አራተኛ ደግሞ ኢማም ማለት የአላህን ህግጋት የሚጠብቅና የሚከላከል እስከሆነ ድረስ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ለጥፋትና ለስህተት ለተጋለጠ ሰው አልፎ መስጠት ተገቢ አይሆንም። እንዲህ አይነቱ ሰው ይህንን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጣው አይችልና። በዚህ ምክንያት ነው እንግዲህ እንከን የለሽ ወይም ስህተት አልባ መሆን ለነብይነት ለመብቃት የማያሻማ መስፈርት ሆኖ የሚታመነው።

ለነብይነት መስፈርትነት አስፈላጊ ስለመሆኑ የተነሱ ነጥቦች ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ለኢማምነትና ለኸሊፋነትም ቀንደኛው መስፈርት መሆን እንዳለበት በማያሻማ መልኩ የተቀመጠበት ሁኔታ ነው ያለው ማለት ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ በተመለከተ «ሉሉል አምር እንከን የለሽ (መዕሱም) ናቸው» በሚለው ርዕስ ሥር በሰፊው እናያለን፡፡

**በአላህ መመረጥ**

ነብያትን በተመለከተ እላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች ብቻ ቀጥታ ለኢማምነት ለመብቃት በቂ አይደሉም፡፡ «*ኢማማህ በውድድር የሚገኝ ክፍት የሥራ ቦታ አይደለም፡፡ በማንም የሚሰጥ ኃላፊነት አይደለም፡፡ ከአላህ ብቻ የሚመነጭ ሹመት ነው፡፡*» (*ቀደም ሲል የተጠቀሰው ምንጭ፡- ገፅ 68*)

በአሥራ ሁለቱ ኢማሞች የሚያምኑ ሺዓዎች (ሺዓ እስነ ዓሸሪያህ) የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተተኪ ወይም ኸሊፋህ የሚመረጠው በአላህ ብቻ ነው ብለው የሚያምኑት ይህንን ምክንያት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ውስጥ ህዝቡ ምንም ድርሻና ምርጫ እንደሌላቸው አጥብቀው ያምናሉ፡፡

የህዝቡ ተግባር አላህ የመረጠውን ኢማምና ኸሊፋ መከተልና መታዘዝ ብቻ ነው፡፡

**የቁርአን አናቅፅ ማስረጃዎች**

የሚከተሉት የቁርአን አናቅፅ ይህንኑን የሺዓዎች አቋም ያረጋግጣሉ፡፡

وَرَبُّكَ يَخْلُقُ مَا يَشَاءُ وَيَخْتَارُ مَا كَانَ لَهُمُ الْخِيَرَةُ سُبْحَانَ اللَّهِ وَتَعَالَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ﴿٦٨﴾

«*አላህ ያሻውን ይፈጥራል፣ ይመርጣልም፡፡ እነርሱ ምርጫ የላቸውም፡፡ ለአላህ ጥራት ይገባዋል፡፡ አላህ እነርሱ ከሚያገሩት የላቀ ነው፡፡*» **(ቁርአን 28፡68)**

ይህ በግልፅ የሚያመለክተው የሰው ልጅ በምርጫው ጉዳይ ላይ ምንም ምርጫ እንደሌላቸው ነው ጉዳዩ በአላህ እጅ ውስጥ ብቻ እንደሆነ ነው፡፡

አላህ አደምን (ዐ.ሰ) ከመፍጠሩ በፊት ጉዳዩን ለመላኢኮች ነገራቸው፡-

إِنِّى جَاعِلٌ فِى الْأَرْضِ خَلِيفَةً

«***በምድር ላይ ተተኪ (ኸሊፋህ) ላደርግ ነው፡፡***» **(ቁርኣን 2፡30)**

መላኢኮቹ ስለ ዕቅዱ ደስተኛ አለመሆናቸውንና ተቃውሞአቸውን ለማስወገድ አላህ ቀጥተኛ መልስና ገለፃ ነበር የሰጣቸው፡-

إِنِّى أَعْلَمُ مَا لَا تَعْلَمُونَ﴿٣٠﴾

«***በእርግጥ እናንተ የማታውቁትን እኔ አውቃለሁ፡፡***» **(ቁርአን 2፡30)**

እንከን የለሽ (መዕሱም) የሆኑ መላኢኮች የኸሊፋን ምርጫ በተመለከተ ምንም ድርሻ እንደሌላቸው ከተናገራቸው ተራ የሆነ የሰው ልጅ የምርጫን ጉዳይ በተመለከተ አጠቃላይ ስልጣን በእጁ ያስገባል ብሎ ማሰብ የማይመስል ጉዳይ ነው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዳውድን (ዐ.ሰ) ኸሊፋ አድርጎ የሾመው አላህ ራሱ እንደሆነ ከቁርኣን እንረዳለን፡፡

يَا دَاوُودُ إِنَّا جَعَلْنَاكَ خَلِيفَةً فِي الْأَرْضِ

«*ዳውድ ሆይ! እነሆ በመሬት ላይ ኸሊፋህ አድርገን መርጠንሃል፡፡*» **(ቁርኣን 38፡26)**

በሁሉም ሁኔታዎች አላህ ኸሊፋን ወይም ኢማምን የመምረጡን ጉዳይ የራሱ ብቻ እንዳደረገ እናያለን፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥሪው ለነብዩ ኢብራሂምም መጣ፡-

قَالَ إِنِّي جَاعِلُكَ لِلنَّاسِ إِمَامًا قَالَ وَمِن ذُرِّيَّتِي قَالَ لَا يَنَالُ عَهْدِي الظَّالِمِينَ ﴿١٢٤﴾

(አላህ) አለ፡- «*በእርግጥ ለሰዎች ኢማም አድርጌ ልመርጥህ ነው፡፡*»
(ኢብራሂምም) አለ፡- «*ከዙርያዬስ?*»
(አላህ) አለ፡- «*ቃል ኪዳኔ በዳዮችን አያካትትም፡፡*»

ይህ አንቀፅ ኢማማህ (መሪነትን) በተመለከተ ለሚነሱ ጠቃሚ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት ወደሚያስችል ጎዳና ይመራናል፡፡

ሀ) አላህ እንዲህ ይላል፡- «*በርግጥ ለሰዎች ኢማም (መሪ) አድርጌ ልመርጥህ ነው፡፡*» ይህ የሚያመለክተው ኢማማህ ሰማያዊ ሹመት እንደሆነና ከህብረተሰቡ (ኡማህ) ፍርድ ውጭ መሆኑን ነው፡፡

ለ) «*ቃል ኪዳኔ በዳዮችን አያካትትም*» የሚለው ደግሞ እንከን የለሽ (መዕሱም) ያልሆነ ኢማም መሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ምክንያታዊ ሆነን ካሰብነው ሰዎችን በአራት ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡

1. ህይወታቸውን በሙሉ በዳይ ወይም ኢ-ፍትሃዊ (ዛሊም) ሆነው የሚያሳልፉ፣
2. በህይወታቸው ጭራሽ በዳይ ወይም ኢ-ፍትሃዊ (ዛሊም) ሆነው የማያውቁ፣
3. በህይወታቸው መጀመሪያ አካባቢ ዛሊም የነበሩና የኋላ ኋላ ግን ፍትሃዊ ለመሆን የበቁ እና
4. በህይወታቸው መጀመሪያ አካባቢ ፍትሃዊ የነበሩና የኋላ ኋላ ግን ዛሊም ለመሆን የበቁ ናቸው፡፡

ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ) ካላቸው ክብርና ከፍተኛ ቦታ ለመጀመሪያውና ለአራተኛው ቡድን ዓይነት ሰዎች የኢማምነት ቦታን ይጠይቃሉ ብሎ ማሰብ ዘበት ነው፡፡

ስለዚህ ሁለት ቡድኖች ብቻ ይቀሩናል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን አላህ ከነዚህ ሁለቱ ቡድኖች አንዱን ውድ ያደርጋል። እነዚህም በመጀመሪያው የህይወት ዘመናቸው ኢ-ፍትሃዊ የነበሩና የኋላ ኋላ ግን ፍትሃዊ ለመሆን የበቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ በመጨረሻ ለኢማማህ የሚበቃ አንድ ቡድን ብቻ ይቀራል ማለት ነው፡፡ እነዚህም በህይወት ዘመናቸው በሙሉ ዛሊም (ኢ-ፍትሃዊ) ሆነው የማያውቁ መዕሱም (ፍትሃዊ) የሆኑ ናቸው ማለት ነው፡፡

ሐ) የመጨረሻው ዐረፍተ-ነገር (አባባል) በግርድፉ ወይም በጥሬው ሲተረጎም፦ «*ቃል ኪዳኔ ዛሊሞችን (በዳዮችን) አይደርስም*» የሚል ሃሳብ ይኖረዋል፡፡ እዚህ ጋር ማስተዋል ያለብን አላህ «*ዛሊሞች (በዳዮች) ለቃል-ኪዳኔ አይደርሱም*» አላለም፡፡ ምክንያቱም በዚህ መልኩ ቢገለጽ ኖሮ መሪነቱን የመጎናደፉ ሂደት በሰዎች ስልጣንም ኃይልም መገኘት የሚችል ነገር እንደሆነ የሚያመለክት አዝማሚያ ይኖር ነበር፡፡

የዓረፍተ-ነገሩን አገላለጽ ግን ለእንዲህ ዓይነቱ የተዛባ አስተሳሰብ ክፍተት የማይሰጥና፣ ኢማምነትን መጎናጸፍ የሚቻለው በሰዎች ምርጫና ፍርድ ሳይሆን በአላህ እጅ ውስጥ ብቻ ያለ መሆኑንና አላህ ለፈለገው ሰው

የሚሰጠው ሹመት መሆኑን በማያወላውል መልኩ ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡

ለዚህም እንደ አጠቃላይ መመሪያ በሚከተለው መልኩ የተገለፀው፡-

وَجَعَلْنَاهُمْ أَئِمَّةً يَهْدُونَ بِأَمْرِنَا

«***በኛ ትዕዛዝ (መመሪያ) መሠረት ሰዎች የሚመሩ ኢማሞች አደረግናቸው፡፡***» **(ቁርአን 21፡73)**

ነብዩ ሙሳ (ዐ.ሰ) ኃላፊነቱን ተጋርቶት የሚረዳውን እንደራሴ (ወዚር) ሲያስፈልገው በራሱ ስልጣን የሚፈልገውን ሰው አልመረጠም፡፡ ወደ አላህ ዱዐዕ (ፀሎት) አደረገ፡-

«***ከቤተሰቤ የሆነን ሰው፣ ወንድሜ ሐሩንን ወዚር አድርግልኝ፡፡***» **(ቁርአን 20፡29-30)**

አላህም እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጠው፣

«***ሙሣ ሆይ! የጠየቅከው ነገር ተሰጥቶሃል (ጥያቄህ ተቀባይነት አግኝቷል)***» **(ቁርአን 20፡36)**

በኣላህ የተወሰነው ምርጫ ለህዝቡ ይፋ የሆነው በነብዩ ወይም ቀድሞ በነበረው ኢማም መሆኑን በግልፅ እናውቃለን፡፡ ይህ ውሳኔ «ነስ» ይባላል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ነብዩ ወይም ቀድሞ የነበረው ኢማም ተተኪ ሆኖ

የሚሰራውን ኢማም መለየት፣ መወሰን ወይም መሾም እንደማለት ነው፡፡ በሺዓ እምነት ኢማም በአላህ ተመርጦ የተሾመ (መንሱስ ሚነላህ) መሆን አለበት፡፡

### ተዓምራት

አንድ ሰው የኢማምነት ነስ (ድንጋጌ) ባይደርሰውና ባይሰማ እውነታውን ማረጋገጥ የሚችለው በተዓምር (ሙዕጅዛ) ብቻ ነው፡፡ (*አል-ዓለማህ አል-ሂሊ፡- አል-ባቡል ሃደ ዓሸር፣ የእንግሊዝኛ ትርጉም በ W.M. ሚለር፣ ገፅ 69*)

በአጠቃላይ ስናየው ማንኛውም ሰው ተነስቶ የነብዩ ኸሊፋ ነኝ ወይም ኢማም ነኝ፣ እንከን የለሽ (መዕሱም) ነኝ ብሎ ሊያስብ ይችላል፡፡ ነገር ግን ተዓምር እውነታውን ለማረጋገጥ መጠቀም የሚቻል ብቸኛው መሣሪያ ነው፡፡ ኢማም ነኝ ባዩ የይገባኛል ማረጋገጫውን በተዓምር (ሙዕጅዛ) አስደግፎ ማሳመን ከቻለ ያለጥርጥር ተቀባይነት ያገኛል ማለት ነው፡፡ ይህንን ማድረግ ካልቻለ ግን ለኢማምነት የሚያበቃው መስፈርቶችን ያላሟላ ስለመሆኑ እንደ ማስረጃ ተይዞ ይገባኛል ባይነቱ ሐሰትና ተቀባይነት እንደሌለው ይረጋገጣል ማለት ነው፡፡

### ቀደምት ታሪክ

ካለፈው የነቢያት ታሪክ እንደምንረዳው ተተኪያቸውን መምረጥ በተመለከተ የተለመደው ሥርዓት በአላህ ትዕዛዝ መሰረት ነቢያቱ ኸሊፋቸውን የመምረጥ ብቸኛው አካሄድ ነበር እንጂ ህዝቡ ጣልቃ ገብቶ ድርሻ የወሰደበት ሁኔታ አልነበረም። በዚህ ረዥም ታሪክ ውስጥ ከዚህ አኳኋን ውጭ ተከታዩ (ህዝቡ) የነብይን ተተኪ (ኸሊፋ) የመረጠበት አንዳችም ምሳሌ የለም። ስለዚህ ይህ ሰማያዊ ህግ የመጨረሻው ነብይን (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋ ብቻ አስመልክቶ የሚቀየርበት ምንም ምክንያት የለም።

አላህ እንዲህ ይላል፡- «***በአላህ ህግ ውስጥ በጭራሽ ለውጥ አታገኝም፡፡***» **(ቁርአን፣ 33፡62)**

### አሳማኝ ምክንያቶች

**1.** ነብይ በአላህ የሚመረጥ ስለመሆኑ የተወሱ ማስረጃዎች እንደሚያረጋግጡት ሁሉ በተመሳሳይ ምክንያት የነብይ ተተኪ (ኸሊፋህ) መመረጥ ያለበት በአላህ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው ማለት ነው። ኢማም ወይም ኸሊፋህ፣ ልክ እንደ ነቢይ አላህ ያዘዘውን ስራ የመስራትና የማስፈጸም ኃላፊነት ስለተሰጠው፣ ተጠሪነቱ ለአላህ መሆን አለበት። በህዝቡ የሚመረጥ ከሆነ ግን የመጀመሪያው ተጠሪነቱ ወይም ታማኝነቱ ለሹመቱ

መሰረት ለሆኑት ለህዝቡ እንጂ ለአላህ አይሆንም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሁሌ ሰዎችን ለማስደሰት ይሞክራል ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የመረጡት ሰዎች ካልተማመቡነትና የማይመቻቸው ከሆነ ስልጣኑን ስለሚያጣ ነው፡፡ ስለዚህ ያለ ፍራቻና አድሎ የሃይማኖት ስራ መስራትና ኃላፊነቱን መወጣት አይችልም፡፡ ትኩረቱ በሙሉ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የአላህ ስራ ይጎዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዳግም በሰው የተመረጡ ኸሊፋዎች ገና ከጅማሬው መሰረታዊ የሃይሞኖት መርሆዎችን እንደጣሱና ተገቢውን ቦታ እንዳልሰጡ የእስላም ታሪክ ተጨባጭ ማስረጃ ይሰጣል፡፡

ስለዚህ ይህ ፅንሰ-ሀሳብ ወይም አቋም አዕምሮአዊ (ትምህርታዊ) ገለፃን ብቻ የተከተለ አቋም ሳይሆን ተጨባጭ ታሪካዊ ማስረጃም ከጀርባው አለው፡፡

2. ከዚህም ባሻገር የሰውን ውስጣዊ ማንነትና ስሜት አብጠርጥሮ የሚያውቅ አላህ ብቻ ነው፡፡ ከአላህ ውጭ ማንም ሰው የሰውን እውነተኛ ተፈጥሮ ሊያውቅ አይችልም፡፡ ማን ያውቃል ምናልባት አንድ ሰው ባልደረቦቹን ለማስደሰት ለዓለማዊ ጥቅምና በሰው ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት አላህን ፈሪና ፃድቅ መስሎ ለመታየት ይታገል ይሆናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ምሳሌዎች

በታሪክ መኖራቸው ደግሞ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ለምሳሌ የአብዱል መሊክ ኢብን መርዋንን ታሪክ እንመልከት፡፡ ይህ ሰው ጊዜውን በሙሉ የሚያሳልፈው መስጊድ ውስጥ ሶላት በመስገድና ቁርአንን በመቅራት ነበር፡፡ የአባቱ የሞት እረፍት ሲሰማና ሲነገረው ቁርአን በመቅራት ላይ ነበር፡፡ ህዝቡ ቃልኪዳንን (በይዓ) ሊገቡለት እየተጠባበቁ መሆኑን ሲሰማ ቁርአኑን ዘጋውና እንዲህ አለ፡-

*«ይህ በእኔና በአንተ መካከል መለያያ (ቀን) ነው፡፡» (አል-ሱዩጢ፡- ታሪኹል ኹሉፋእ፣ ገፅ 217)* ስለዚህ አንድ ሰው ለኢማምነት ወይም ለኸሊፋነት የሚያበቁ መስፈርቶች እንዳለውና እንደሌለው በትክክል መታወቅ የሚችለው በአላህ ብቻ ስለሆነ ኢማም ወይም ኸሊፋህ መምረጥ ያለበት አላህ ብቻ ነው ማለት ነው፡፡

**(ኢማሞቹ እንከን የለሽ ስለ መሆናቸው)**

**የኢማሞቹ እንከን የለሽነት**

እስቲ አሁን ደግሞ አህሉል በይት (የነብዩ የቤተሰብ አባላት)ን አስመልክቶ ቁርአን ምን እንደሚል እናስተውል፡፡ በቁርአን መሠረት የሚከተሉት ሰዎች ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት የተለየበት ወቅት ሐጢአት የሌላቸውና

እንከን የለሽ ነበሩ። እነርሱም፡- ዓሊ፣ ፋጡማ፣ ሐሰን እና ሁሴን ናቸው። ማጥራት አንቀጽ (አያት አል-ተጥሂር) እንደሚከተለው ይነበባል።

إِنَّمَا يُرِيدُ اللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنْكُمُ الرِّجْسَ أَهْلَ الْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِيراً ﴿٣٣﴾

«***የነብዩ ቤተሰቦች ሆይ! አላህ የሚሻው ከናንተ ላይ ርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው።***» (**ቁርአን፡- 33:33**)

እላይ የተጠቀሱት አራት ሰዎች «የነብዩ ቤተሰቦች» (አህሉል ቤይት) እንደሆነ ከሀጢአትና ከማንኛውም ርክሰት ነፃ እንደሆኑ ሁሉም የሚስማማበት ጉዳይ ነው።

ከዚህ አንቀጽ (አያህ) በፊትና በኋላ ያሉ አናቅፅ (አያቶች) የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶችን (ሚስቶች) በተመለከተ የወረደ አያህ እንደሆነ ለመረዳት አያዳግትም። በነዚህ አናቅጽ ውስጥ የተጠቀሱ ተውላጠ ስሞች (ስምን ተክተው የሚገቡ ቃላት ወይም የቃላት ክፍል) አነስታይ (ሴት) ጾታ የሚያመለክቱ ሲሆን በማጥራት አንቀጽ (አያህ አል-ተጥሂር) ውስጥ የተጠቀሱ ተውላጠ ስሞች ግን ተባዕታይ

(ወንድ) ጾታ የሚያመክቱ ናቸው። ይህ አንቀጽ በዚህ መልኩ የመገለጹ ምክንያት ምን እንደሆነ ለመገመት አስቸጋሪ አይሆንም።

ታዋቂው ምሁር «አላማህ ፑያ» የ *S.V. Mr አህመድ ዓሊ የቁርአን ተፍሲር የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1857* ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል።

ይህ የቅዱሳን አህሉል ቤይቶችን ንጽህና የሚገልጽ የአንቀድ ክፍል አገባቡን በትክክል ያገናዘበ ተተኪ የሆነ ማብራሪያ መስጠት የግድ ይላል። ይህ የአንቀጽ ክፍል ለተለየ ሁናቴ የተለየ ክስተትን በተመለከተ ራሱን የቻለ የተለየ አንቀጽ ሆኖ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶችንም የሚመለከት በመሆኑ አሁን ባለው መልኩ ተቀምጧል። የዚህ አያህ (አንቀጽ) አቀማመጥ አጢኖ ላየው ሰው ራሱን የቻለ አስፈላጊና ጠቃሚ ዓላማ ከጀርባው አለው። የአያቱ የመጀመሪያው ክፍል በአነስታይ ጾታ የሚገለጹ እድምተኞችን ሊያናግር ቀጠል በማድረግ ግን ከአነስታይ የጾታ መልዕክት ተቀባዮች ወደ የተባዕታይ ጾታ የምስራች ተቀባዮች በቅጽበት ይሸጋገራል።

አንቀጾቹ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የትዳር አጋሮችን የሚመለከት ሲሆን ወጥ በሆነ መልክ የአነስታይ (ሴት) ጾታ የተገለጸ ሲሆን ወንዶችና ሴቶች በአንድነት ሆነው ሲገኙ ደግሞ

የተባዕታይ (ወንድ) ጾታ መጠቀም የተለመደ ነገር መሆኑ ማንም አያጣውም፡፡ የጾታ አገላለጽ ለውጥ መኖሩና ከአንዱ ጾታ ወደ ሌላው ጾታ የመሸጋገሩ ሚስጢር (በአጠቃላይ የሰዋሰው ሽግግር) ጉዳዩ የተለያየ መሆኑን፣ አንዱ ቡድን ከሌላው የተለየ መሆኑን፣ መልዕክቱ (የምስራቹ) ለመጀመሪያው ቡድን ሳይሆን ለሌላው እንደሆነና አያው በዚህ ተስማሚ ቦታ የተቀመጠው የአህሉል ቤይትን ቦታና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሚስቶችን ቦታ በንጽጽር ለማየት ይረዳ ዘንድ የተደረገ መሆኑን መረዳት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡

አምር ኢብኑ ሰለማህ የሚባል ነቢዩ ያሳደጉት ሰሃባ የሚከተለውን ዘገባ እንዳስተላለፈ ተዘግቧል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

ይህ አንቀጽ በወረደ ጊዜ ነቢዮ (ሰ.ዐ.ወ) በአሙ ሰለማህ ቤት ውስጥ ነበሩ፡፡ «የነቢዩ ቤተሰቦች ሆይ! አላህ የሚሻው ከናንተ ላይ ርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ነው» የሚለው አንቀጽ ሲወርድ፣ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ልጃቸውን ፋጡማን፣ ሐሰንና ሁሴንንና የፋጡማ ባልና የነብዩ አጐት ልጅ የሆነውን ዓሊን አንድ ላይ ሰብስበው እራሳቸውንም ጨምረው በካባቸው ሸፍኖአቸው የሚከተለውን አሉ፡- «*አላህ ሆይ! ቤተሰቦቼ /አህሉል ቤይቶቼ/ እነኚህ ናቸው፡፡ ከርክስት ሁሉ አርቃቸው፤ ማጥራትንም አጥራቸው፡፡*» በዚህን ጊዜ

ተወደጂ የነቢዩ ባለቤት የሆነችው ኡሙ ሰላማህ ክስተቱን በደንብ ካመነች በኋላ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በትህትና እንዲህ አለቻቸው፡- «እኔም ቡድኑን መቀላቀል እችላለሁ?»

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመልሱ «*አይደለም፡፡ አንቺ ባለሸበት ቆይ፡፡ አንቺ መልካም ነገር ላይ ነሽ*» አሏት፡፡

ይህንን አንቀጽ በተመለከተ ያሉትን ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ዋቢ መጽሐፍት እዚህ ቦታ መዘርዘሩ ጊዜና ቦታው አይደለም፡፡ የሱኒ ምሁር የሆኑትን መውላና ዋሂዱ ዘማንን ሳልጠቅስ ማለፍ አልፈልግም፡፡ ይህ ምሁር በቁርአን ተፍሲራቸውና አንዋር አል-ሉጋ (የሐዲስና የቁርአን መዝገበ ቃላት) በተሰኙ ሥራቸው ይታወቃሉ፡፡ ቀደም ሲል የተነሳውን የቁርአን አንቀጽን አስመልክተው በተፍሲራቸው ላይ የሚከተለውን አስቀምጠዋል፡፡

«አንዳንድ ሰዎች ይህ አያህ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የስጋ ዝምድና ያላቸውን የቤተሰብ አባላት፣ ማለትም፡ አሊ፣ ፋጡማ፣ ሐሰንና ሁሴንን በተለየ ሁኔታ የሚመለከት ነው ብሎ ያስባሉ፡፡ በጠንካራ ሰንሰለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር የደረሱ ዘገባዎች (ሀዲሶች)ና ትክክለኛነታቸው (ሰሂህ) የተረጋገጡ የነብዩ ቃላትም ይህንኑ እንደሚያረጋግጡ እኔም አሳምሬ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እራሳቸው «የቤተሰብ አባላቴ» (አህሉል ቤይቴ) እነኚህ ብቻ ናቸው» ብለው ስለተናገሩ ነገሩን መቀበልና ማመን ግድ ይላል፡፡ ሌላኛው ማረጋገጫ ደግም ከዚህ

የተለየ የአንቀጽ ክፍል በፊትና በኋላ ያሳት የአንቀጽ ክፍሎች በሴት ጾታ የተገለጹ ሲሆን ሌላኛው አንቀጽ በወንድ ፆታ የተገለጸ መሆኑ ነው፡፡ *(ዋሂዱ ዘማን፣ ተፍሲር ዋሂዱ፣ አንቀጽ 22፣ የግርጌ ማስታወሻ 7፣ ገጽ 51)*

በተጨማሪም አንዋር አል-ሉጋ በተሰኘው ሥራቸው ውስጥ የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

«ትክክለኛ ዕይታ ይህ የማጥራት አንቀጽ (አያህ አል-ተጥሂር) የሚያካትተው እነዚህን አምስት ሰዎች ብቻ ነው፡፡ እነርሱም፣ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ዓሊ፣ ፋጡማ፣ ሐሰንና ሁሴን ናቸው፡፡ ምንም እንኳን በአረብኛ ቋንቋ «አህሉል ቤይት» የሚለው ሐረግ ለሚስቶችም መቆም የሚችል ቢሆንም በማያሻማ ሁኔታ የተቀመጠው ግን በተጠቀሱት ሰዎች ብቻ የተሰጠ ስያሜ መሆኑ ነው፡፡ ይህንን አንቀጽ መሠረት በማድረግ አንዳንድ ሰዎች እነዚህ አምስቱ ሰዎች ሀጢአት የሌላቸው እንከን የለሽ (መዕሱም) እንደሆነ ያረጋግጣሉ፡፡ ነገር ግን መዕሱም ባይሆኑ እንኳን መህፉዝ (ሐጢአትን ከመፈጸምና ከመሳሳት የተጠበቁ) ስለመሆናቸዉ በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡ *(ዋሂዱ ዘማን፤ አንዋር አል-ሉጋ፣ አንቀጽ 22፣ ገጽ 51)*

እነዚህን ሁለት መጽሐፍት እንደማስረጃ የጠቀስኩበት ምክንያት የእስነ ዓሸሪያ ሺዓዎች (በአሥራ ሁለቱ

ኢማሞች የሚያምኑ) ብቻ ሳይሆን የታወቁ የሱና ምሁራንም ትክክለኛ ሃዲሶችንና የአረብኛ ቋንቋ ሰዋሰው ህግጋትን መሠረት በማድረግ የተጠቀሰው የቁርአን አያህ የሚያካትተው ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ጨምሮ ዓሊ፣ ፋጡማ፣ ሐሰንና ሁሴን ብቻ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጡ ለመግለጽ ነው። በተጨማሪም እነዚህ የተጠቀሱ ሰዎች ከሀጢአት የፀዱና እንከን የለሽ ስለመሆናቸው በሱኒ ምሁራንም እንደሚታመን ለመጠቆም ነው። ቀደም ሲል እንደተናገረው እንከን የለሽ ናቸው ተብለው በሙሉ ልብ ለመናገር ባይደፍሩም ቢያንስ ቢያንስ ከማንኛውም ርክሰት እንዳተጠበቁ (መህፉዝ እንደሆኑ) በግልጽ ተቀምጧል።

የአህሉል ቤይትን ንጽህናና እንከን የለሽነት በተመለከተ በርካታ የሆኑ ሌሎች የቁርአን አናቅጽና ሐዲሶች ቢኖሩም እዚህ ቦታ ላይ ሁሉንም ለመዘርዘር ቦታው አይፈቅድልኝም።

**የዓሊ (ዐ.ሰ) ታላቅነትና የበላይነት**

አፍዳሊያህ (በላጭነት/የበላይነት) በእስላም ውስጥ ያለው ትርጉም፡- «በመልካም ሥራው/ዋ ከአሏህ የበለጠ ሰዋብ (ሽልማት) የሚገባው/ት» ማለት ነው።

ይህ የበላይነት በኛ አስተያየትና አስተሳሰብ መወሰን እዳማይችልና በቁርአንና በሐዲስ አማካኝነት ካልሆነ በምንም ምልኩ ማወቅ እንደማይቻል ሁሉም ሙስሊሞች የሚስማሙበት ጉዳይ ነው፡፡

ታዋቂው የሱኒ ምሁር አል-ጋዛሊ የሚከተለውን ጽፈዋል፡- «የየበላይነት እውነታው በአሏህ ፊት ብቻ ያለ ነገር ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሆኑ በስተቀር በሌላ ሰው መታወቅ የማይችል ጉዳይ ነው፡፡»

*(አል-ጋዛሊ፡- አህያዕ ዑሉሚዲን 1፡2፣10)*

አብዛኛው የሱኒ ወንድሞቻችን በላጭነት/የበላይነት በኸሊፋዎች ቅደም ተከተል እንደሆነ ያምናሉ፡፡ ይህ ማለት አቡ በክር የበላይነት ነበራቸው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ኡመር፣ ከዚያ ቀጥሎ ኡስማን፣ ከዚያ ደግሞ ዓሊ (ዐ.ሰ)፡፡

ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ ማስረጃን መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የሁሉም ቀደምት ሱኒዎች እምነትም አልነበረም፡፡ በቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን ብዙ የተከበሩ የነቢዩ ሰሃቦች፡- እንደ ሰልማን አል-ፋርሲ፣ አቡዘር አል-ግፋሪ፣ ሚቅዳድ አል-ክንዲ፣ አማር ኢብን ያሲር፣ ኸባብ ኢብን አረት፣ ጃቢር ኢብን አብደላህ አል-አንሳሪ፣ ሁዘይፋህ ኢብን የማን፣ አቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ፣ ዘይድ ኢብን

አርቀምና ሌሎች ብዙ ሰሃቦች ዓሊ (ዐ.ሰ) ከሁሉም አህሉል ቤይትና ሰሃቦች ሁሉ በላጭ እንደነበረና የበላይነት እንደነበረው ያምኑ ነበር፡፡
*(ኢብን ዓብድል በር፡- አል-እስቲአብ፣ 2፡470)*

በላጭነትን (የበላይነትን) በተመለከተ አህመድ ኢብን ሀንበል በልጃቸው ጥያቄ ተጠይቀው እንዲህ ሲሉ መልሰዋል፡-
«*አቡበክር፣ ከዚያ ኡመር፣ ከዝያ ኡስማን፡፡*»
ልጃቸው፡- «*አሊይ ኢብን አቡ ጧሊብስ?*» ብሎ ጠየቃቸው፡፡
አህመድ ኢብን ሀንበል፡- «*እሱማ የአህሉል በይት አባል ነው፡፡ ሌሎች ከርሱ ጋር መወዳደር አይችሉም*» ብለው መለሱ፡፡ *(አል-ቁንዱዚ፡- የናቢዑል መወደህ ገጽ 253)*

አርጀሁል መጣሊብ በተሰኘ መጽሐፋቸው ውስጥ ዑበይዱሏህ አምርስታሪ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡
«በላጭ መሆን ማለት (ብዙ ሰዋብ/ምንዳ ማግኘት) ስለሆነ ማረጋገጫውን ማግኘት የሚቻለው ከነብዩ ሐዲሶች ብቻ ነው፡፡ የሚጋጩና የሚቃረኑ ሐዲሶች ከተገኙ ደግሞ ትክክለኛው ሐዲስ ብቻ ተቀባይነት ማግኘት አለበት፡፡ ጠንካራ ሐዲሶች ከደካማ ሐዲሶች መለየት አለባቸዉ፡፡»

አል-አላማህ ኢብን ዓብድል በር አል-እስቲአብ በተሰኘ መጽሐፋቸው ቅጽ 3፣ ገጽ 1115 ላይ አሚሩል ሙእሚኒን ዓሊን (ዐ.ሰ) በተመለከተ ስለተዘገቡ ሐዲሶች ሲገልጹ፡- ኢማም አህመድ ኢብን ሐንበል፣ አል-ቃዲ ኢስማኢል ኢብን ኢስሃቅ፣ ኢማም አህመድ ኢብን ዓሊ ኢብን ሹዓይብ አል-ነሰኢና አል-ሀፊዝ አቡ ዓሊ አል-ነይሳቡሪ እንዲህ ብለዋል፡-

«የዓሊይ ኢብን አቡ ጧሊብን ታላቅነትና መልካም ስብዕናን በተመለከተ የተዘገቡ ጠንካራ የዘገባ ሰንሰለት (አሳኒድ) ያላቸው ሀዲሶች ብዛታቸውን ስናይ ለሌላ ለማንም ሰሃባ እንደዛ ብዛት ያለው ጠንካራ ሀዲስ አልተገኙም፡፡» *(ኢብን ሀጀር አል-ሀይተሚ፡- አስልዋኢቁል ሙህሪቃህ፣ ገጽ 72፣ ኢብን ሀጀር አል-ዐስቀላኒ፡- ፈትሁል ባሪ፣ ቅጽ 8፡ ገጽ 71)*

በተጨማሪም የአሚሩል ሙዕሚኒን ዓሊ (ዐ.ሰ) ብቸኛ ትሩፋቶችና መልካም ስብዕናዎችን ስናይና ከአሏህ ዘንድ ብዙ ሰዋብ እንዲጐናጸፍ ያደረጉትን ነገሮች ስናስብ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ ያለ ብቸኛው ብልጫ (አፍደሊያ) ያለው ሰው መሆኑን ለማመን እንገደዳለን፡፡ *(አሚሪስታሪ፡- አርጀሁል መጣሊብ፣ ገጽ 112)*

ጸሐፊው ሱኒ ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ እላይ በተገለጸው መጽሐፍ ምዕራፍ 3፣ ገጽ 103-516፣ ላይ በሰፊው ገልጿል፡፡

በእርግጥ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ያሉትን የቁርአን አናቅጽና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶችን በአጭሩ እንኳን ዘርዝሬ መጨረስ አልችልም፡፡ የዓሊን (ዐ.ሰ) «አፍደሊያ»ን በተመለከተ ብዙ ተብሏል፡፡ በአጭሩ የአሊን (ዐ.ሰ) ታላቅነትና የበላይነት የሚያወሱ ቢያንስ 86 የቁርአን አንቀጾችና ተቆጥረዉ የማያልቁ ሀዲሶች እንዳሉ መግለጹ በቂ ነው፡፡

ስለዚህ ለአንድ ተራ ሰው እንኳን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ ከሙስሊሞች በሙሉ ላይ ብልጫ (አፍደሊያ) ያለው ሰው ቢኖር ዓሊይ ኢብን አቡ ጧሊብ (ዐ.ሰ) መሆኑ ግልጽ ነው ማለት ነው፡፡

**የዓሊይ መመረጥ**

የዓሊይ ኢብን አቡ ጧሊብን (ዐ.ሰ) እንከን የለሽነት (ዕስማህ) ና የበላይነት (አፍደሊያህ) ይህን ያህል በአጭሩ ካልን የሚቀጥለው ትልቁና አስፈላጊ ጥያቄ በአላህ ስለመመረጡ ጉዳይ ነው፡፡

በተለያዩ አጋጣሚዎች ላይ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊይ (ዐ.ሰ) ተተኪያቸውና ኸሊፋቸው እንደሚሆን በይፋ ደንግገዋል፡፡

የመጀመሪያው በግልጽ የነቢይነት ድንጋጌና (ነብይነታቸውን በግልጽ የተናገሩበት) የአሊይን (ዐ.ሰ) ኸሊፋነትም በግልጽ የተነገረበት አጋጣሚ አንድ ዕለት መሆኑ የማያሻማ እውነታ ነው። ይህ የሆነው «በቤተ-ዘመድ ግብዣ» ዕለት ነበር።

«***የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ***» **(ቁርአን፡- 26፡214)**

የሚለው አያህ ሲወርድ ቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊይ (ዐ.ሰ) ምግብ እንዲያዘጋጅና የአብዱል ሙጠሊብ ልጆችን እንዲጋብዝና ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህን ቃል መልዕክት እንዲያሰማቸው እዲያደርጉ አዘዙት።

ግብዣው ካበቃ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመናገር አስበው ነበር። ሆኖም አቡ ለሀብ ጣልቃ በመግባት፡-

«*በእርግጥ ወዳጃችሁ ዛሬ አስደሰታችሁ*» አለ።

ይህን በሰሙ ጊዜ ሁሉም ተነስተው ተበታተኑ።

በሚቀጥለው ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ደግሞ ለግብዣ ጠሯቸው። ሁሉም ምግባቸዉን በልተው ከጨረሱ በኋላ ቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ንግግር አደረጉ።

«የአብዱል ሙጠሊብ ልጆች ሆይ! ለዚህኛው ዓለምም ሆነ ለሚቀጥለው ዓለም የሚሆን መልካም ነገር ይዤ መጥቻለሁ። ወደ እሷ ህ ጥሪ እንዳደርግላችሁ በአላህ ተመርጫለሁ። ስለዚህ ከናንተ ውስጥ ይህንን ጉዳይ

የሚከታተልልኝ ወንድሜ፣ (ወራሼና) ኸሊፋዬ የሚሆነው ማነው?» ብለው ጠየቁ፡፡

ከተሰበሰቡት ሰዎች ውስጥ በዕድሜው የመጨረሻ ልጅ የነበረው ዓሊይ (ዐ.ሰ) በስተቀር ለነቢዩ ጥሪ ማንም ምላሽ አልሰጠም፡፡

ከዚያም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የዓሊይን (ዐ.ሰ) ትከሻ ነካ ነካ አደረጉና፡-

«ህዝቤ ሆይ! ይህ ዓሊ ወንድሜ፣ ተተኪዬና ኸሊፋዬ ነው፡፡ እሱ የሚላችሁን ስሙ፣ ታዘዙትም፡፡» አሉ፡፡

*(ኢብንል አሲር፡- አል-ካሚል ፊ ታሪክ፣ ቅጽ 5፡ ገጽ 62-3፣ አል-በገዊ፡- አል-ተፍሲር፣ ቅጽ 4፡ ገጽ 127፣ አል-ካዚም፡- አል-ተፍሲር፣ ቅጽ 4፡ ገጽ 127፣ አል- በይሐቂ፡- ዳላእል አል-ኑቡወህ፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 428-30፣ አል-ሱዩጢ፡- አል-ዱር አል-መንሱር፣ ቅጽ 5፡ ገጽ 97፣ አል-ሙተቂ አል-ሂንዲ፡- ከንዙል ዑማል፣ ቅጽ 14፡ ገጽ 100፣ 113፣ 115-7፣ አቡል ፊዳ፡- አል-ሙክተሰር፣ ቅጽ1፡ ገጽ 116-7፣ አል-ጠበሪ፡- አል-ታሪክ፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 171-3፣ Carlyle,T.: On Heroes, Hero-Worship and the Heroic in History, ገጽ 54፣ Gibbon,E.: The Decline and Fall of the Roman Empire, ቅጽ 3፡ ገጽ 94፣ Davenport,J.: An apology for Mohammed and the Koran, ገጽ 21፣ Irving, W.: Mohammet and His Successors, ገጽ 45፣ ለተጨማሪ ዝርዝር አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 278-89 ይመልከቱ፡፡*

**የአል-ዊላያ አንቀጽ (አያት አል-ዊላያህ)**

ከዚያ በኋላ በተለያዩ አጋጣሚዎች ብዙ የቁርአን አንቀጾችና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲሶች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ ዓሊ (ዐ.ሰ) ወሊያቸው (አለቃ፣ መሪ፣ አዛዥ.....) እንደሆነ ሙስሊሞችን ያስታወሳሉ። ከነዚህ የቁርአን አንቀዶች በጣም ታዋቂው የሚከተለው ነው።

إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ اللَّهُ وَرَسُولُهُ وَالَّذِينَ آمَنُوا الَّذِينَ يُقِيمُونَ الصَّلَاةَ

وَيُؤْتُونَ الزَّكَاةَ وَهُمْ رَاكِعُونَ﴿٥٥﴾

«***በእርግጥ የናንተ (ወልይ) አላህ፣ መልዕክተኛውና እነዛ ያመኑ፣ ሶላትን ያቋቋሙና አሏህን ለመገዛት አጐንብሰው (ሩኩዕ ውስጥ ሆነው) ዘካት የሚሰጡ ናቸው።***» (ቁርአን 5:55)

የሙስሊም ምሁራን ሱኒም ሆነ ሺዓ በአንድነት እላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ኢማም ዓሊይን (ዐ.ሰ) በተመለከተ እንደወረደ ይስማሙበታል።

አንቀጹ ለአማኞች ሦስት ወሊዮች ብቻ እንዳሉ በግልጽ ያስቀምጣል። በአንደኛ ደረጃ አላህ፣ ከዚያ ደግሞ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ዓሊ (ከአሥራ አንዱ ተከታታይ ኢማሞች ጋር) እንደሆኑ ያስቀምጣል።

አቡ ዘር አል-ግፋሪ እንደሚነግረን ከዕለታት አንድ ቀን ከነቢዩ ጋር ይሰግድ እንደነበረና ወደ ነቢዩ መስጊድ የመጣ አንድ ለማኝ ነበር። ለዚህ ለማኝ ማንም ምላሽ አልሰጠውም ነበር። በዚህን ጊዜ ለማኙ እጆቹን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጐ እንዲህ አለ።

«*አላህ ሆይ! እነሆ ወደ ነቢዩ መስጊድ መጥቼ ማንም ምንም እንዳልሰጠኝ ምስክር ሁነኝ።*»

ዓሊይ በዚህን ጊዜ በሩኩዕ ውስጥ ነበር። ቀለበት የነበራትን ትንሽ ጣቱን ወደ ለማኙ አመለከተ። ለማኙም ወደ ዓሊይ መጣና ቀለበቷን ከጣቱ አውልቆ ወሰዳት።

ይህ ክስተት የተፈጸመው ነቢዩ ባሉበት ነበር። በዚህን ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፊታቸውን ወደ ሰማይ አነሱና የሚከተለውን ዱአዕ አደረጉ። «*ጌታዬ ሆይ! ወንድሜ ሙሳ ልቡን ታሰፋለት ዘንድ ጠየቀህ። ተልዕኮው ቀላል እንዲሆንለት እንድታደርግለትም ለመነህ። ሰዎች መልዕክቱን በሚገባ ይረዱት ዘንድም የምላሱ መተሳሰር እንዲወገደለትም ጠየቀህ። ከቤተሰቡ የሆነውን ወንድሙን ሃሩንን ረዳቱ እንድታደርግለትና እንደራሱው እንዲሆን ጠየቀህ። አንተም ለሙሴ «በወንድምህ አማካኝነት ክንድህን እናበረታለን ከዚህ ወዲያ ማንም አይደርስባችሁም» አልከው። አላህ ሆይ! እኔ ሙሐመድ ነኝ። የላቀ ደረጃም አጐናጸፍከኝ። ደረቴን አስፋልኝ፣ ተልዕኮና ሃላፊነቴንም ቀላል*

*አድርግልኝ፣ ከቤተሰቤ ወንድሜ ዓሊይን እንደራሴዬ አድርገህ ሹምልኝ፣ በጥንካሬዬ አጋዥ አድርግልኝ፡፡»*

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንን ዱአዕ አድርገው እንኳን አልጨረሱም ጅብሪል እላይ የተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ይዞ ሲመጣ፡፡ *(አል-ጠበሪ፡- አል-ተፍሲር ቅጽ 6፡ ገጽ 186)፣ አል-ሱዩጢ፡- አል-ዱር አል-መንሱር፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 293-4፣ አል-ራዚ፡- አል-ተፍሲር አል-ኣቢር፣ ቅጽ 12፡ ገጽ 26፣ አል-ዘመክሽሪ፡- አል-ተፍሲር (አል-ከሻፍ)፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 649፣ አል-ጀሳስ፡- አህካሙል ቁርአን፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 542-3፣ አል-ኻዘን፡- አል-ተፍሲር፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 68)*

እዚህ ቦታ ላይ ያሉትን የሐዲስ ማጣቀሻዎች ለመዘርዘር ቦታው አይደለም፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ ሀዲሶችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ ይህ የቁርአን አያህና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዱአዕ በአንድነትም ሆነ በተናጠል የሚያሳዩት ዓሊይ (ዐ.ሰ) ከነቢዩ በኋላ የሙስሊሞች መሪና አለቃ ሆኖ መመረጡን ነው፡፡

### የገዲር ኹም ግልጽ አዋጅ

ቀደም ሲል የተጠቀሱት ድንጋጌዎችና አዋጆች ለገዲር ኹም ግልጽ አዋጅ እንደ ቅድመ ሁኔታ ሊታዩ ይችላሉ፡፡

ይህ የገዲር ኹም ክስተት በሁለቱም መዝሀቦች (ሱኒና ሺዓ) የታሪክ ጸሐፍያንና ምሁራን ብዙ የተባለበት ጉዳይ ነው፡፡ ቀጥሎ ዓሊ (ዐ.ሰ) የነቢዩ ወራሽና ተተኪ ይሆን ዘንድ በግልጽ ለማወጅ ስለተዘጋጀው ታላቅ ጉባኤ በአጭሩ እናነሳለን፡፡

ገዲር ኹም የተሰኘው ቦታ የሚገኘው በመካና መዲና መካከል ጁሃፋ የሚባል ክልል ውስጥ ነው፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻውን ሀጅ አድርገው ወደ ቤታቸው በመመለስ ላይ ሳሉ ጅብሪል አስቸኳይ የሆነ ትዕዛዝ ከአላህ ይዞ መጣ፡-

يَا أَيُّهَا الرَّسُولُ بَلِّغْ مَا أُنْزِلَ إِلَيْكَ مِنْ رَبِّكَ وَإِنْ لَمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُ وَاللَّهُ يَعْصِمُكَ مِنَ النَّاسِ

«***አንተ መልዕክተኛ ሆይ! ከጌታህ የተወረደልህን (መልዕክት) አድርስ! ይህንን ባታደርግ (የጌታህን) መልዕክት አላደረስክም፡፡ አሏህ ከሰዎች (ክፉ ሐሳብ) ይጠብቀሃል፡፡***» (ቁርአን 5፡67)

በዚህን ጊዜ ቅዱሱ ነቢይ ጉዞአቸውን በቅጽበት ገቱና ቀድመው የሄዱ ሰዎች በሙሉ ወደኋላቸው እንዲመለሱና ወደ ኋላ የቀሩ ደግሞ እስኪደርሱ ድረስ እንዲጠበቁ አደረጉ፡፡

ሁሉም ተጓዦች ቦታው ከደረሱ በኋላ የግመል ኮርቻዎችን በማነባበር ከፍ ያለ መድረክ ተሠራ፡፡ እሾህና ስብርባሪ ነገሮች ከአካባቢው ተጠረጉ፡፡ ከዚያም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) መድረኩ ላይ ወጡና ረዥም ንግግር አደረጉ፡፡
«ሕዝቦች ሆይ! በደንብ አድምጡኝ፡፡ ጅብሪል ብዙ ጊዜ ከአዛኙ ከጌታ ትዕዛዝ ይዞ ወደኔ እንደወረደና እዚህ ቦታ ላይ ቆሜ እያንዳንዱን ሰው፣ ነጭና ጥቁር፣ ዓሊይ የአቢ ጧሊብ ልጅ ወንድሜና የኔ ዋሲ (ተተኪ/ወራሽ) እንደሆነና ከኔ በኋላ ኢማም (መሪያችሁ) እንደሆነ እንድነግራችሁ ታዝዣላሁ፡፡ ዓሊ ከኔ ጋር ያለው ቦታ፣ ከኔ በኋላ ነቢይ ያለመኖሩ በስተቀር፣ ሐሩን ለሙሳ ያለው ቦታ ያህል ነው፡፡ ከአላህና ከኔ ቀጥሎ ያለ መሪያችሁና አዛዣችሁ ነው፡፡

እናንተ ህዝቦች ሆይ! ልብ በሉ! አላህ ኢማማችሁና ገዢአችሁ አድርጐ መርጦታል፡፡ ለሱ መታዘዝ በሁሉም ላይ ግዴታ ነው፡፡ ለአንሷሮችም ሆነ ለሙሃጅሮችና ለተከታዮቻቸው በሙሉ፣ ለገጠር ነዋሪዎችም ሆነ ለከተማ ነዋሪዎችና ዘላኖች፣ ለአረብና አረብ ያልሆኑ፣ ለነፃ ሰዎችም ሆነ ለባሮች፣ ለወጣትም ሆነ ለሽማግሌ፣ ለትልቅም ለትንሽ፣ ለነጭም ሆነ ለጥቁር፣ የሁሉም መሪና ትዕዛዙን መቀበል ግዴታ መሆኑን እወቁ፡፡ ትዕዛዙ መከበር አለበት፡፡ ቃሉን መስማትና መታዘዝ በአንድ አላህ ላመነ ሰው ሁሉ

ግዴታ ነው። ለርሱ የማይታዘዝና ያፈነገጠ የተረገመ ነው። እሱን የሚከተልና የሚታዘዝ የተባረከ ነው። በርሱ የሚያምን ሁሉ እውነተኛ አማኝ ነው።

ሕዝቦች ሆይ! በእንዲህ ዓይነት ስብስብ ፊት ለመቆም ይህ የመጨረሻዬ ነው። ስለዚህ ስሙኝ! ለጌታችሁ ትዕዛዝ እጅ ስጡ። አላህ እሱ ጌታችሁና አምላካችሁ ነው። ከአላህ በኋላ ከፊታችሁ የቆመው መልዕክተኛው ሙሐመድ ወሊያችሁ (መሪያችሁ) ነው። ከኔ በኋላ ደግሞ ዓሊይ በአሏህ ትዕዛዝ መሠረት ወሊያችሁና ኢማማችሁ ነው። ከዚያም በኋላ ከዓሊ ከሚወለዱት ዝርያዎቹ ኢማማህ (መሪነቱ) ይቀጥላል። አላህንና ነቢዩን የምትገናኙበት ቀን እስኪደርስ ድረስ በዚህ መልኩ ይቀጥላል።

ሰዎች ሆይ! የአላህ ቃል የሆነውን ቁርአን በደንብ አስተውሉ! አስተንትኑ! አያዎቹ በደንብ ይግባችሁ! ግልጽ በሆኑት አናቅጽ ላይ ተወያዩ። አሻሚና ግልጽ ባልሆኑ አንቀጾች ውስጥ አትግቡ። በአላህ እምልላችኋለሁ ማስጠንቀቂያዎቹን በትክክል የሚነግራችሁና ትርጉማቸውን በደንብ የሚተነትንላችሁ ከዚህ እጁን ፊት ለፊቴ ከፍ አድርጌ የማሳያችሁ ሰው (ዓሊይ) በስተቀር ሌላ ማንም ሰው አታገኙም። እናም እላችኋለሁ እኔ «ወሊይ» የሆንኩት ማንኛውም ሰው ዓሊይ «ወሊዩ» ነው። እሱም

የአቡ ጧሊብ ልጅ፣ ወንድሜና ዋሲ (ተተኪዬ/ወራሼ/ምትኬ) ዓሊይ ነው፡፡ ዊላያነቱ (መሪነቱ) በላቀውና በኃያሉ አላህ ትዕዛዝ መሠረት ግዴታ ተደርጓል፡፡»

በዚህ ንግግር ውስጥ ሌሎችም ኢማሞች በአጭሩ ተወስተዋል፡፡ በሌሎች ሐዲሶች ደግሞ በተብራራ ሁኔታ ተገልጸዋል፡፡

ለምሳሌ በአንድ አጋጣሚ ላይ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ለኢማም ሁሴን የሚከተለውን ብለዋል፡-

«አንተ ኢማም፣ የኢማም ልጅና የኢማም ወንድም ነህ፡፡ ከአንተ የዘር ሐረግ የሚገኙ ዘጠኝ ኢማሞች ወደፊት ይኖራሉ፡፡ ከነዚህ ኢማሞች ዘጠነኛው የነሱ ቃእም (የሚነሳ) ነው፡፡»

*(አል-ቁንዱዚ፡- የናቢዑል መወደህ፡ ገጽ 168፣ አምርስታሪ፡- አርጀሁል መጣሊብ፡ ገጽ 448)*

በአጠቃላይ ሲታይ ይህ ጉዳይ አንድ ተራ ሰው እንኳን መረዳት እንደሚችለው እጅግ ክብደት የተሰጠው ነገር እንደሆነና ለእስላም አጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ ጉዳይ በመሆኑ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ የመጣውን ትዕዛዝ ለማድረስ አስፈላጊውን ዘግጅት ሁሉ እንዳደረጉ በግልጽ የተቀመጠ ነው፡፡

ለዚህም ነው በሚንቀሳቀሰው የበረሃ የፀሐይ ንዳድ ውስጥ መድረክ ተሠርቶ ለሰዓታት የቆየ ንግግር በማድረግ መልዕክቱን በታላቅ አንክሮ ማስተላለፍ የተፈለገው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የሳቸው መጨረሻ (በሞት የመለየት) ጊዜ መቃረቡን ከተናገሩ በኋላ የነበረባቸውን ኀላፊነትና ግዴታ በብቃት ስለመወጣታቸው ዕድምተኞችን ለምስክርነት እንዲህም ብለው ጠየቋቸው፡፡

«*እናንተ በራሳችሁ ላይ ካላችሁ ሥልጣንና መብት የበለጠ በናንተ ላይ መብትና ስልጣን አለኝ ወይስ የለኝም?*»
በዚህን ጊዜ ሁሉም በአንድነት በእርግጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በነርሱ የበለጠ መብት እንዳላቸው ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡ በዚህን ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡-

«*እኔ ወልይ የሆንኩት ማንም ሰው ዓሊይም ወሊዩ ነው፡፡*»
በመጨረሻም ለዓሊይ የሚከተለውን ዱአዕ አደረጉ፡-
«*አላህ ሆይ ዓሊይን የወደደ ሁሉ ውደድ፣ ለዓሊይ ጠላቱ የሆነን ሁሉ አንተ ጠላቱ ሁን፣ ዓሊይን በረዳ አንተ ረዳት ሁንለት፣ ዓሊይን የከዳ ሰው አንተ ክዳው (ዓሊይን ከመርዳት ያፈነገጠ እርዳታህን ንፈገው)*»

*ሥነ-ሥርዓቱ* እንዳበቃ የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ወረደ፡-

الْيَوْمَ أَكْمَلْتُ لَكُمْ دِينَكُمْ وَأَتْمَمْتُ عَلَيْكُمْ نِعْمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ الْإِسْلَامَ دِينًا

«*በዛሬው ዕለት ሃይማኖታችሁን ለናንተ ምሉዕ አደረኩላችሁ ፀጋዬንም በናንተ ላይ አሟላሁላችሁ ኢስላምንም ኃይማኖታችሁ አድርጌ አረጋገጥኩላችሁ፡፡*»
**(ቁርአን - 5:3)**

ይህ ከሰማይ የወረደው ንግግር ዓሊይ ኢማም ሆኖ በአላህ በመመረጡ የሃይማኖት ምሉዕነት፣ የአላህ ፀጋ መሟላትና ኢስላም እንደ ኃይማኖት በአላህ ማረጋገጫ ማግኘቱ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡

ይህ ታላቅ ዜና ከሰማይ እንደመጣ አማኞቹ በየተራ እየተነሱ ነቢዩ ባሉለት ለዓሊ የእንኳን ደስ አለህ መልዕክትና ምስክርነታቸውን ሰጡ፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ብዙ ስንኞች ተቋጥረዋል፣ በርካታ ግጥም ተገጥሟል፡፡ እነዚህ ክስተቶች በሙሉ በሐዲስ መጽሐፍት ተመዝግበው ይገኛሉ፡፡ ቀጠል በማድረግ ዝርዝሩን ለማቅረብ ሙከራ እናደርጋለን፡፡

**የገዲር ሐዲስ ሙተዋትር (ሰንሰለቱ ሳይቆረጥ በበርካታ ዘገባዎች የተገኘ መሆኑ**)

ትክክለኛነታቸው ከተመሰከረላቸው የሱኒ መጽሐፍት የተወሰዱ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የነቢዩን ኹጥባ /ንግግር/ በሚመለከት የተጻፉ ቅንጭቦች እንደሚከተለው ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

«በመካከላችሁ ሁለት እጅግ ውድ የሆኑ ነገሮችን ትቼላችኋለሁ፡፡

1. የአላህ መጽሐፍ (ቁርአን)

2. የቤተሰቤ አባል (አህሉል ቤይት) የሆነ ዝርያዎቼ (ኢትረት)

እነዚህ ሁለቱ ኸውሰር (በጀነት ውስጥ ያለ ምንጭ) ላይ ከኔ ጋር እስኪገናኙ ድረስ በፍጹም አይለያዩም፡፡ እውነት እላችኋለሁ የኔ «ዋሊይ» አላህ ነው፡፡ እኔ ዳግሞ ለአማኞች «ዋሊይ» ነኝ፡፡»

ከዚያም የዓሊይን እጅ ያዙና፡-

*«እኔ ወሊይ ለሆንኩት ሁሉ ዓሊይ «ወሊይ» ነው፡፡»*

እነዚህ ሁለት ሐዲሶች «ሐዲስ አል-ሰቀሌይን» (የሁለቱ ውድ/የከበሩ ነገሮች ሐዲስ) እና የዊላያህ (የዓሊይ ነቢዩን ተክቶ መምራት) ሐዲስ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሁለቱ ሀዲሶች በአንድነትም በተናጠልም በመቶዎች በሚቆጠሩ የሀዲስ መሁራን ተዘግበዋል፣ ተወርተዋል፡፡

ነዋብ ሲዲቅ ሐሰን ኻን ሐዲስ አል-ሰቀላይንና ሐዲስ አል-ዊላያን አስመልክቶ የሚከተለውን ብሏል፡፡

አል-ሐኪም አቡ ሰዒድ እንደሚለው የሁለቱ የከበሩ ነገሮች ሐዲስና «*እኔ ወሊይ ለሆንኩት ሁሉ ዓሊይ ወሊይ ነው፡፡*» የሚለው ሐዲስ ሙተዋትር ነው፡፡ ምክንያቱም በርካታ ቁጥር ያላቸው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ስላወሩትና ስለዘገቡት ለትክክለኛነቱ ምንም ጥርጣሬ ሊኖር አይችልም፡፡ እነዚህን ሁለቱ ሀዲሶች ሙሐመድ ኢብን ጀሪር በሰባ አምስት (75) የተለያዩ ሰነዶች (ሰንሰለተ ሀዲስ) ከመዘገቡ ባሻገር «ኪታቡል ዊላያህ» የተሰኘ ራሱን የቻለ ወጥ መጽሐፍ ጽፈዋል፡፡ እንዲሁም ሰነዱን በተመለከተ አል-ሃፊዝ አል-ተዝሂቢ ራሱን የቻለ አንድ መጽሐፍ ጽፈዋል፡ ሀዲሱንም «ሙተዋትር» በሚሰኙ ሀዲሶች ጐራ ውስጥ በቀደምትነት አስቀምጠዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አቡል አባስ ኢብን ዑቅደህ የገዲር ኩምን ሀዲስ አንድ መቶ ሀምሳ (150) ሰንሰለተ-ሀዲስ (አስናድ) እንዳወሩትና በዚሁ ጉዳይ አንድ ሙሉ መጽሐፍ ጽፈዋል፡፡፡

*(ሲዲቅ ሐሰን ኻን፡- መንሀጁል ውሱል፡ ገጽ 13)*

አንዳንድ ፀሓፊዎች ግን የገዲር ኹምን ክስተት በተመለከተ ውዥንብር ለመፍጠርና ጥርጣሬን ለማሳደር ጥረት አድርገዋል፡፡

ነገር ግን ሐዲሱ መተዋትር መሆኑን አበክሮ መናገር ያስፈልጋል፡፡ ታዋቂው የእስላም ምሁር አላማ አል-አሚኒ በታዋቂው መጽሐፋቸው አል-ገዲር በመጀመሪያው ቅጽ ላይ ሙሉ ማጣቀሻዎችን ጨምሮ ይህንን ሀዲስ ያወሩትን የአንድ መቶ አሥር (110) ታዋቂ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሀቦችን ስም ዝርዝር አስፍረዋል፡፡ ቀጥሎ እንዲያው ለምሳሌ ይሆን ዘንድ በመጀመሪያው የአረብኛ ፊደል አሊፍ ሥር ያሉትን ብቻ ለዋቢነት እንጥቀስ፡፡ የሞቱበት ጊዜ በዓመተ-ሂጅራ በቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል፡፡

1. አቡ ሌይላ አል-አንሷሪ (37)
2. አቡ ዘይነብ ኢብን ዓውፍ አል-አንሷሪ
3. አቡ ፈድለህ አል-አንሷሪ (38)
4. አቡ ቁዳማህ አል-–አንሷሪ
5. አቡ ዐምራህ ኢብን ዐምር ኢብን ሙሃስን አል-አንሷሪ
6. አቡል ሀይሰም ኢብን አል-ጠህያን
7. አቡ ራፊዕ አል-ቂብጢ (የነቢዩ ባሪያ)
8. አቡ ሱዌይብ ኹዋሊድ (ወይም ኻሊድ) ኢብን ኻሊድ አል- ሁሰሊ
9. ዑስማን ኢብን ዘይድ ኢብን ሀሪሳህ (54)
10. ኡበይ ኢብን ከዕብ አል-አንሷሪ (30 ወይም 32)
11. አስዐድ ኢብን ዙራረህ አል-አንሷሪ

12. አስማእ ቢንት ዑመይስ
13. ኡሙ ሰለማህ (የቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ/ ባለቤት)
14. ኡሙ ሀኒእ ቢንት አቢ ጧሊብ
15. አቡ ሐምዛ  አነስ ኢብን ማሊክ አል-አንሷሪ
16. አቡ በክር ኢብን አቢ ቁሃፋህ
17. አቡ ሁሬይረህ

*(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፣ ቅጽ 1 ገጽ 14-8)*

በተጨማሪም ከ84 የማያንሱ ታቢኢን (የሰሃቦች ተከታዮች) እላይ ከተጠቀሱት ሰሃቦች ይህንን ሀዲስ አውርተዋል፡፡ በአሊፍ (ኤ) ፊደል ሥር የተሰጡትን በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፡-

1. አቡ ረሺድ አል-ሁብራኒ አል-ሻሚ
2. አቡ ሰለማህ ኢብን ዐብድረህማን ኢብን ዐውፍ
3. አቡ ሱለይማን አል-ሙአዝን
4. አቡ ሷሊህ አል-ሰማን፣ ዘክዋን አል-መደኒ
5. አቡ ዑንፈዋናህ አል-መዘኒ
6. አቡ ዐብድረሂም አል-ክንዲ
7. አቡል ቃስም፣ አስበግ ኢብን ኑባታህ አል-ተሚሚ
8. አቡ ለይላ አል-ክንዲ
9. ኢያስ ኢብን ኑደይር

*(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፡ ገጽ 62-63)*

የሀዲስ ባለሙያዎች ይህንን ሀዲስ በሁሉም ዘመናት በመጽሐፎቻቸው ዘግበዋል። ለምሳሌ በሁለተኛው ምዕተ ዓመተ ሀጅራ ይህንን ሀዲስ የዘገቡ ጸሐፊዎችና ምሁራን የሚከተሉት ናቸው፡-

1. አቡ ሙሐመድ ዐምር ኢብን ዲናር አል-ጁማሂ አል-መኪ (115 ወይም 116)
2. አቡ በክር መሐመድ ኢብን ሙስሊም ኢብን ዑበይድላህ አል-ቁሬይሺ አል-ዙህሪ (124)
3. ዐብዱልረህማን ኢብን ቃሲም ኢብን ሙሐመድ ኢብን አቢ በክር አል-ተይሚ አል-መደኒ (126)
4. በክር ኢብን ሰዋዳህ ኢብን ሱማማህ፣ አቡ ቱማማህ ኢል-በሰሪ (128)
5. አብዱላህ ኢብን አቢ ነጂህ፣ የሳር አል-ሰቀፊ፣ አቡየሳር አል-መኪ (131)
6. አል-ሀፊዝ ሙጊረህ ኢብን ሙካስም፣ አቡ ሒሻም አል-ዳቢ አል-ኹፊ (133)
7. አቡ አብዱል ረሂም ኻሊድ ኢብን ዘይድ አል-ጁማሂ አል-ሚስሪ (139)
8. ሐሰን ኢብን አል-ሐከም አል-ነኸኢ አል-ኩፊ (140)
9. ኢድሪስ ኢብን የዚድ፣ አቡ አብድላህ አል-ዐውዲ አል-ኩፊ

10. ያህያ ኢብን ሰዒድ ኢብን ሀያን አል-ተይሚ አል-ኩፊ

11. አል-ሐፊዝ አብዱልመሊክ ኢብን አቢ ሱለይማን አል-አርዘሚ አል-ኩፊ (145)

12. ዐውፍ ኢብን አቢ ጀሚላህ አል-ዐብዲ አል-ሀጀሪ አል-በስሪ (146)

13. ዑበይድላህ ኢብን ዑመር ኢብን ሐፍስ ኢብን ዓሲም ኢብን ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ አል-ዐዳዊ አል-መደኒ (187)

14. ኑዐይም ኢብንል ሃኪም አል-መደይኒ (148)

15. ጠልሃ ኢብን ያህያ ኢብን ጠልሃ ኢብን ዑበይድለህ አል-ተይሚ አል-ኩፊ (148)

16. አቡ ሙሐመድ ከሲር ኢብን ዘይድ አል-አስላሚ (150)

17. አል-ሀፊዝ ሙሐመድ ኢብን ኢስሃቅ አል-መዳኒ (151 ወይም 152)

18. አል-ሀፊዝ ሙዐመር ኢብን ረሺድ፣ አቡ ዑርዋ አል-አዝዲ አል-በስሪ (153 ወይም 154)

19. አል-ሀፊዝ ሚእሳር ኢብን ኪዳም ኢብን ዛሂር አል-ሂላሊ አል-ረዋሲ አል-ኩፊ (153 ወይም 154)

20. አቡ ዒሳ ሐከም ኢብን አባን አል-ዐዳኒ (154 ወይም 155)

21. አብድላህ ኢብን ሸውሳብ አል-በልኺ አል-በስሪ (157)
22. አል-ሀፊዝ ሹዕባህ ኢብን አል-ሀጃጅ፣ አቡ ቢስታም አል-ዋሲጢ (160)
23. አል-ሀፊዝ አቡል አላእ፣ ካሚል ኢብን አል-ዐላእ አል-ተሚሚ አል-ኩፊ (160)
24. አል-ሀፊዝ ሱፍያን ኢብን ሰዒድ አል-ሰውሪ፣ አቡ አብድላህ አል-ኩፊ (161)
25. አል-ሀፊዝ እስራኤል ኢብን ዩኑስ ኢብን አቢ ኢስሀቅ አል-ሰቢዒ አቡ ዩሱፍ (161)
26. ጃዕፈር ኢብን ዚያድ አል-ኩፊ አል-አህመር (165 ወይም 167)
27. ሙስሊም ኢብን ሰሊም አል-ነህዲ፣ አቡ ፈርማህ አል-ኩፊ
28. አል-ሀፊዝ ቀይስ ኢብን አል-ረቢዒ፣ አቡ ሙሐመድ አል-አሰዲ አል-ኩፊ (165)
29. አል-ሀፊዝ ሀማድ ኢብን ሰለማህ፣ አቡ ሰለማህ አል-በሰሪ (174)
30. አል-ሀፊዝ አብደላህ ኢብን ለሂዐህ፣ አቡ አብድረህማን አል-ሚስሪ (174)
31. አል-ሀፊዝ አቡ ዑዋነህ አል-ወድዳህ ኢብን አብድላህ አል-የሽኩሪ አል-ዋሲቲ አል-በዘዝ (175 ወይም 176)

32. አል-ቃዲ ሸሪክ ኢብን አብድላህ፣ አቡ አብድላህ አል-ነኸዒ አል-ኩፊ (177)
33. አል-ሀፊዝ አብድላህ (ወይም ዑበይድልህ) ኢብን ዑበይዱረህማን (ወይም አብዱረህማን) አል-ኩፊ፣ አቡ አብድረህማን አል-አሽጃዒ (182)
34. ኑህ ኢብነ ቀይስ፣ አቡ ረውህ አል-ሁደኒ አል-በስሪ (183)
35. አል-ሙጠሊብ ኢብን ዚያድ ኢብን አቢ ዙሐይር አል-ኩፊ፣ አቡ ጠሊብ (185)
36. አል-ቃዲ ሐሰን ኢብን ኢበራሂም አል-ዓናዚ፣ አቡ ሐሺም (186)
37. አል-ሀፊዝ ጀሪር ኢብን አብድልሀሚድ፣ አቡ አብድላህ አድዳቢ አል-ኩፊ አል-ራዚ (188)
38. አል-ፈድል ኢብን ሙሳ፣ አቡ አብድላህ አል-መርወዚ አል-ስናኒ (193)
39. አል-ሀፊዝ ሙሐመድ ኢብን ጃዕፈር አል-መዳኒ አል-በስሪ (193)
40. አል-ሀፊዝ ኢስማዒል ኢብን ዑሊያህ፣ አቡ ብሽር ኢብን ኢብራሂም አል-አሰዲ (193)
41. አል-ሀፊዝ ሙሐመድ ኢብን ኢብራሂም፣ አቡ ዐምር ኢብን አቢ ዐድይ አል-ሱለሚ አል-በስሪ (194)

42. አል-ሀይዝ ሙሐመድ ኢብን ኻዚም፣ አቢ ሙዓዊያህ አል-ተሚሚ አል-ደሪር (195)

43. አል-ሀፊዝ ሙሐመድ ኢብን ፉደይል፣ አቡ አብድረህማን አል-ኩፊ (195)

44. አል-ሀፊዝ አል-ወኪዕ ኢብን አል-ጀራሀ አል-ሩዐሲ አል-ኩፊ (196)

45. አል-ሀፊዝ ሱፍያን ኢብን ዑየይነህ፣ አቡ ሙሐመድ አል-ሂላሊ አል-ኩፊ (198)

46. አል-ሀፊዝ አብድላህ ኢብን ኑመይር፣ አቡ ሂሻም አል-ሀመዳኒ አል-ኸሪፍ (199)

47. አል-ሀፊዝ ሀነሽ ኢብን አል-ሀሪስ ኢብን ለቂጥ አል-ነኸዒ አል-ኩፊ

48. አቡ ሙሐመድ ሙሳ ኢብን ያዕቁብ አል-ዘማኢ አል-መዳኒ

49. አል-አዕላ ኢብን ሰሊም አል-አታር አል-ኩፊ

50. አል-አዝረቅ ኢብን ዓሊይ ኢብን ሙስሊም አል-ሀነፊ አብዱል ጀህም አል-ኩፊ

51. ሀኒእ ኢብን አዩብ አል-ሀናፊ አል-ኩፊ

52. ፉዳይል ኢብን መርዙቅ አል-አገር አል-ሩዐሲ አል-ኩፊ (160)

53. አቡ ሐምዛ ሰዕድ ኢብን ዑበይዳህ አል-ሱለሚ አል-ኩፊ

54. ሙሳ ኢብን ሙስሊም አል-ሂዛሚ አል-ሸይባኒ፣ አቡ ዒሳ አል-ኩፊ አል-ተሃን (ሙሳ አል-ሰጊር)

55. የዕቁብ ኢብን ጃዕፈር ኢብን አቢ ከሲር አል-አንሷሪ አል-መዳኒ

56. ዑስማን ኢብን ሰዕድ ኢብን ሙረህ አል-ቁሬይሺ፣ አቡ አብድላህ (አቡ ዓሊይ) አል-ኩፊ

*(አል-አሚኒ አል-ገዲር። ገጽ 73-81)*

ስለዚህ ይህ ሀዲስ በበርካታ የሀዲስ ዘጋቢዎች (ሩዋት) በየዘመኑ እየተወራ መተዋትር እንደሆነ ይዘልቃል ማለት ነው።

በሀዲስ መጽሐፍታቸው ውስጥ ይህንን ሀዲስ የዘገቡትን ምሁራንን በተመለከተ አል-አላማህ አሚኒ የ360 ምሁራንን ስም እንደዘረዘሩ መጥቀሱ ብቻ በቂ ነው ብዬ አምናለሁ።

አንዳንድ ሰዎች የዚህን ሐዲስ ሰነድ (የፍሰቱ ስንሰለት) በተመለከተ ውዥንብር ለመፍጠር ሙከራ አድርገዋል። ማንኛውም የሀዲስ ተማሪ እንደሚያውቀው አንድ ሐዲስ ሙተዋትር (የሀዲሱ ፍሰተ-ሰንሰለቱ ሳይቋረጥ በተለያዩ አቅጣጫ በተሳሳይ መልኩ ከተወራ) ከሆነ የእያንዳንዱ ግለሰብ አስናድ ማየት የግድ አይደለም።

ቢሆንም የዚህን ውዥንብር መሠረተ-ቢስነት ለማሳየት የታዋቂ ሐዲስ ባለሙያዎችን (መሐድሱን) ሐሳብ ቀጥሎ በአጭሩ አቀርባለሁ።

**የገዲር ሐዲስ ሰነዶች (አስናድ)**

*ሀ/* **አል-***ሀፊዝ* **አቡ ዒሳ አል-***ተሚሲ* **(279** *ሂጅራ***) ሰሂህ በተባለው** *ሥራቸው* **(ከ6 ሰሂሆች አንዱ የሆነ) የሚከተለውን ብለዋል፡፡**

«*ይህ ሀዲስ ጥሩ (ሐሰን) እና ትክክለኛ (ሰሂህ) ነው፡፡*»
*(አል-ተሚሲ. አል-ሰሂህ፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 298)*

**ለ/ አል-***ሀፊዝ* **አቡ ጃዕፈር አል-ጠሃዊ (321** *ሂጅራ***)** «*ሙሽክሉል* **አሳር» በተባለ** *ሥራቸው* **ውስጥ እንዲህ ብለዋል፡፡**

«*ይህ ሐዲስ ሰነዱ ትክክለኛና ሐዲሱን ያወሩትን ሰዎችን በሚመለከት ምንም ወቀሳና ትችት ያልቀረበበት ነው፡፡*»
*(አል-ጠሃዊ፡- ሙሽክሉል አሳር፡ ቅጽ 2፡ ገጽ 308)*

*ሐ/* **አቡ አብድላህ አል-ሐኪም አል-***ኒሳቡሪ* **(405** *ሂጅራ***)** «*ሙስተድረክ*» **በተባለው** *መጽሐፋቸው* **ውስጥ ይህንን ሀዲስ በተለያዩ ሰነዶች ተርከዋል፣ ይህ ሐዲስ ሰሂህ ነው ብለዋል፡፡** *(አል-ሐኪም፡- አል-ሙስተድረክ፡ ቅጽ 3፡ ገጽ 109-10)*

*መ/* **አቡ** *ሙሐመድ* **አህመድ ኢብን** *ሙሐመድ* **አል-ዓሰሚ የሚከተለውን ብለዋል፡፡**

«*ይህ ሐዲስ በህዝቡ ተቀባይነት ያገኘና መርሆዎችን ያገናዘበ ነው፡፡*» *(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፡ ቅጽ 1፡ ገጽ 295)*

በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጥሎ የቀረቡት የሀዲስ ምሁራን (በመቶዎች ከሚቆጠሩ እነዚህ ምሁራን በጥቂቱ) ሐዲሱ ሰሂህ እንደሆነ ጠቅሰዋል፡፡ እነሱም፡-

1. አቡ አብድላህ አል-መሐመሊ አል-በግዳዲ «አማሊ» በተሰኘ ሥራቸው ውስጥ
2. ኢብን ዓብድልበር አል-ቁርጡቢ «አል-ኢስቲዓብ» ውስጥ
3. ኢብነል መጋዚሊ አል-ሻፊዒ በ «አል-መናቂብ» ውስጥ
4. ሲብጥ አል-ጀውዚ በ «ተዝረቱል ኽዋሰል ኡመህ» ውስጥ
5. አቡል ፈረጅ ኢብን አል-ጀውዚ በ «አል-መናቂብ» ውስጥ
6. አቡ ሐሚድ አል-ጋዛሊ በ «ሲሩል ዓለማይን» ውስጥ
7. ኢብነ አቢል ሐዲድ አል-ሙዕተዝሊ «ሸርሁል ነህጁል በለጋህ» ውስጥ
8. አቡ አብድላህ አል-ገንጂ አል-ሻፊዒ በ «ኪፋያቱ ጣሊብ» ውስጥ
9. አቡ መካሪም ዓላኡል ዲን አል-ሲምናኒ በ «ኡርወቱ ውስቃ» ውስጥ

10. ኢብን ሐጀር አል-ዓስቀላኒ በ «ተህዘቡል ተህቢብ» ውስጥ
11. ኢብን ኸሲር አል-ድመሽቂ በ «ታሪክ» ውስጥ
12. ጀላሉዲን አል-ሱዩጡ
13. አል-ቀሰጠላኒ በ «አል--መዋሂቡል ለዱኒያህ» ውስጥ
14. ኢብን አል-ሐጀር አል-መኪ በ «አል-ሰዋእቁል ሙህሪቀህ» ውስጥ
15. አብዱልሀቅ አል-ዳህላዊ በ «ሸርዑል ሚሽካት» ውስጥ 5 ሌሎች ብዛት ያላቸዉ ምሁራን፡፡

*(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር ቅጽ 1፡ ገጽ 294-313)*

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን እላይ የተዘረዘሩት ስሞች በሙሉ የሱኒ ምሁራን መሆናቸውንና በሱኒ የሐዲስ ቃላት አጠቃቀም አንድ ሐዲስ «ሰሂህ» (ትክክለኛ) የሚባለው ዓድል መሆናቸው የተመሰከረላቸውና ልዩ የማስታወስ ችሎታ ባላቸው የሐዲስ ተራኪዎች የሐዲሱ ትረካ ፍሰት ሳይቋረጥ ሲወራ ወይም ሲዘገብና ምንም እንከን ያልታየበትና ያልተለመደ (ሸዝ) ያልሆነ ከሆነ ነው፡፡

*(ሱብሂ አል-ሳሊህ፡- ዑሉሙል ሀዲስ ወ ሙስጠለሃቱሁ፣ ገጽ 145)*

እላይ የተጠቀሱት መስፈርቶች በሐዲሱ ሰነድ ውስጥ ከተገኙና ነገር ግን የአንዱ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ

ተራኪዎች የማስታወስ ችሎታቸው ለሰሂህ ሐዲስ ከሚፈለገው በታች ከሆነ ሐዲሱ «ሐሰን» (ጥሩ) ተብሎ ይሰየማል። *(ገጽ 156)*

ስለዚህ የሱኒ ምሁራን የገዲር ሐዲስ ተራኪዎች (ዘጋቢዎች) «ሰሂህ» ነው ሲሉ ተራኪዎቹ ዓድል መሆናቸው የተመሰከረላቸዉና (በእምነታቸውም ሆነ በተግባራቸው እንከን ያልታየባቸዉ)፣ ፍጹም የሆነ የማስታወስ ችሎታ ያላቸው፣ እንዲሁም ሐዲሱ እንከን የሌለውና ያልተላመደ (እንግዳ) ያልሆነ ማለታቸው ነው።

## የ «መውላ» አጠቃላይ ትርጉም

ሱኒዎች የገዲርን ሀዲስ ትክክለኛነት ማስተባበል ወይም መካድ ስላልቻሉ የሀዲሱን ቦታና አስፈላጊነት በቃላት ጫወታ ለማዳከም ይጥራሉ። ይህም በሀዲሱ ውሰጥ «መውላ» የሚለው ቃል «ወዳጅ/ጓደኛ» ማለት ነው ብለው ይተረጉማሉ። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማወጅ የፈለጉትም፡- «*እኔ ወዳጅ የሆንኩት ሁሉ አላህ ወዳጁ ነው*» የሚል ነው ብለው ይናገራሉ።

ነገር ግን በዕለቱ ገዲር ከነበሩ ሰዎች ውስጥ አንድም ሰው ቃሉን በዚህ መልኩ የተረዳ የለም። ታዋቂው የነቢዩ

(ሰ.ዐ.ወ) ገጣሚ ሐሰን ኢብን ሳቢት በዕለቱ ስንኝ ቋጥሮ በታዳሚው ፊት እንደሚከተለው አንብቦ ነበር፡፡

فقال له قم يا علی فاننی        رضيتک من بعدی إماما وهاديا

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ለዓሊይ አሉት፣ ተተኪ ሊያደርጉት የምስራች ሊነግሩት «ዓሊ ሆይ! ተነስና ቁም!» ብለው አዘዙ፡፡ «ኢማምና መሪ ሳደርግህ ወደድኩኝ» ብለው ተናዘዙ፡፡

የሹመቱን ሥነ-ሥርዓት ከተከታተሉት ታዳሚዎች ውስጥ አንዱ የሆነው ኡመር ኢብን ኸጣብ ለዓሊይ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክት ያደረሱት በዚህ መልኩ ነበር፡፡

هنيئا لک يا ابن أبی طالب ، أصبحت وأمسيت مولی کل

مؤمن ومؤمنة

*«የአቡ ጧሊብ ልጅ ሆይ! እንኳን ደስ ያለህ በዛሬው ዕለት የሁለም ወንድና ሴት አማኞች መውላ ለመሆን በቃህ፡፡»*
«መውላ» የሚለው ቃል ትርጉም «ወዳጅ» ከሆነ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክቱ ለምን አስፈለገ? ኡመር *«በዛሬው ዕለት (በአንድ ቀን ውስጥ) የሁሉም መውላ መሆን በቃህ»* ሲል ዓሊይ ከዛ በፊት የሁሉም አማኞች ጠላት ነበር ማለት ነው?

ኢማም ዓሊይ (ዐ.ሰ) ራሱ ለሙዓዊያህ እንዲህ ብሎ ጽፈዋል፡-

*«...የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በአንተ ላይ ስልጣን ያለኝ መሆኑን በዕለተ ገዲር ኹም አረጋግጠውልኛል፡፡»*
***(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 340)***

በተጨማሪም ብዙ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሀቦች በግጥማቸው ውስጥ «መውላ» የሚለውን ቃል «ኢማም/መሪ/ገዢ» የሚል ትርጉም ባለው አገባብ ተጠቅመዋል፡፡

ስፍር ቁጥር የሌላቸው የቁርአን፣ የአረብኛ ቋንቋ ሰዋሰውና የሥነ-ጽሁፍ ምሁራን «መውላ» የሚለውን ቃል «አውላ» በሚለው ቃል ተርጉመዋል፡፡ «አውላ» ማለት ደግሞ፡ «በላጭ፣ ብዙ የሚገባው፣ የበለጠ ትክክለኛ፣ በጣም ተገቢ የሆነ» እንደማለት ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ የሚከተሉትን ምሁራን ለአማኝነት መዘርዘር ይቻላል፡፡

- አል-ኸጢብ አል-ጠብሪዚ፡ ሚሽካቱል ሙሳቢህ፡ ገጽ **557**፣
- ሚር ኸዋድ፡ ሀቢቡል ሲየር፣ ቅጽ **1**፣ የግርጌ መስታወሻ **3**፡ ገጽ **144**
- አል-ጠበሪ፡- አል-ዊለያህ
- አል-ራዚ፡- አል-ተፍሲሩል ከቢር፣ ቅጽ **12**፡ ገጽ **49-50**
- አህመድ፡- አል-ሙስነድ፣ ቅጽ **4**፡ ገጽ **281**

- ኢብን አቢ ሼይባህ፡- አል-ሙስነፍ
- አቡ ያዕላ፡- አል-ሙስነድ
- አህመድ ኢብን ዑቅባህ፡- አል-ዊላያህና ሌሎች

*በተጨማሪም ለበለጠ ዝርዝር አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፡ ቅጽ 1፡ ገጽ፡ 270 - 283 ይመልከቱ፡፡*

1. **ኢብን አባስ፡- (አል-ዱሩል መንሱር፣ ቅጽ 5፡ ገጽ 355)**
2. **አል-ከልቢ (በ አል-ራዚ፡- ተፍሲሩል ከቢር ቅጽ 29፡ ገጽ 227፣ አል-አሉሲ፡- ሩሁል መዓኒ፣ ቅጽ 27፡ ገጽ 178፡ ውስጥ እንደተጠቀሰ)**
3. **አል-ፈራ (በ አል-ራዚና አል-አሉሲ ውስጥ በተመሳሳይ ቅጽ ላይ የተጠቀሰ)**
4. **አቡ ዑበይዳህ ሙዓመር ኢብን ሙሰና አል-በስሪ (አል-ራዚ፣ አል- አሽረፍ አል-ጁራኒ፡- ሸርሁል መዋቅፍ፣ ቅጽ 3፡ ገጽ 271)**
5. **አል-አኸፈሽ አል-አውሰት (በኒዘያቱል ሁቁል ውስጥ)**
6. **አል-ቡኻሪ (በአል-ሰሂህ፣ ቅጽ 7፡ ገጽ 240)**
7. **ኢብን ቁጠይባህ (በ አል-ቁረተይን፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 164)**
8. **አቡል አባስ ሰዕለብ (በአል-አዛኒ፡- ሸርሁል ሰብዓህ አል-ሙዕሊቀህ ውስጥ)**
9. **አል-ጠበሪ (ተፍሲር፡ ቅጽ 9፡ ገጽ 117)**
10. **አል-ዋሂዲ (አል-ወሲት)**
11. **አል-ሰዕለቢ (አል-ከሻፍ ወል በያን)**

12. **አል-ዘመኽሸሪ (አል-ከሻፍ፡ ቅጽ 2፡ ገጽ 435)**

13. **አል-በይደዊ (ተፍሲር፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 497)**

14. **አል-ነሰፊ (ተፍሲር፡ ቅጽ 4፡ ገጽ 229)**

15. **አል-ኻዚን አል-በግዳዲ (ተፍሲር፡ ቅጽ 4፡ ገጽ 229)**

16. **ሙሒቡል ዲን አፈንዲ (ተንዚሁል አያት)**

***(አል-አሚኒ፦ አል-ገዲር፡ ገጽ 344-350 ለዝርዝር ይመልከቱ)***

**የ«መውላ» ዐውዳዊ ትርጉም**

እስቲ አሁን ደግሞ «መውላ» የሚለው ቃል ከሐዲሱ ዐውድ (ቃሉ በሐዲሱ ውስጥ ያለው አገባብ ቦታና ሁኔታ) ሊገኝ የሚገባ ትርጉምን እንመርምር፡፡ አንድ ቃል ከአንድ በላይ ትርጉም የሚኖረው ከሆነ ትክክለኛ ትርጉሙን የማግኘት ዋነኛው ዘዴ ተዛማጅ ትርጉሙንና አገባቡን ወይም ዐውደ ትርጉሙን በማስተዋል ነው፡፡

በሐዲሱ ውሰጥ ከቃሉ ጋር የሚዘመዱ ብዙ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን ከአገባቡ የምንረዳው ብቸኛው ትርጉም «መሪ/ገዢ» የሚለውን ትርጉም በግልጽ እንደሚያስቀምጥ ለመረዳት አያዳግትም፡፡

ከነዚህ ተዛማጅ አባባሎች በጥቂቱ ለመግለጽ እንደሚከተለው ሙከራ ተደርጓል፡፡

**አንደኛ፡-** ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአዋጁ *መግቢያ* ላይ *ታዳሚውን* የጠየቁት ጥያቄ፡- «*አለስቱ አውላ ቢኩም ሚን አንፉሲኩም?*» «*እናንተ በራሳችሁ ላይ ካላችሁት መብት ወይም ስልጣን እኔ በናንተ ላይ መብት የለኝምን?*»
*ዕድምተኞቹም* አሉ፡- «*አዎ! በእርግጥ አዎ!*»
ቀጠል በማድረግ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን አወጁ፡-

من كنت مولاه فهذا على مولاه

«*እኔ «መውላ» የሆንኩት ማንኛውም ሰው ይህ ዓሊይም «መውላው» ነው*»
*ያለምንም* ጥርጥር በዚህ አዋጅ ውስጥ «*መውላ*» የሚለው *ቃል* ««***አውላ ቢኩም***» *እናንተ በራሳችሁ ላይ ካላችሁ ስልጣን የበለጠ እና በናንተ ላይ ሰልጣን/መብት የለኝም ወይ?*» ከሚለው ሐረግ *ጋር* ተመሳሳይ ትርጉም ይኖረዋል።

ቢያንስ 64 የሱኒ ሙሐዲሶች የመግቢያውን ጥያቄ ዘግበዋል። ከነዚህ ምሁራን ውስጥ አህመድ ኢብን ሀንበል፣ ኢብን ማጀህ፣ አል-ነሳኢ እና አል-ቲርሚዚ ይነኙበታል።

*(አል-አሚኒ፡- አል-ገዲር፡ ገጽ 370-371)*

**ሁለተኛ፡-** ከአዋጁ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያደረጉት ዱአዕ፡-

اللهم وال من والاه وعاد من عاداه وانصر من نصره
واخذل من خذله

«*አላህ ሆይ! ዓሊይን የወደደ ሰው ውደደው፣ ለዓሊይ ጠላት ለሆነ ሰው አንተ ጠላቱ ሁነው፣ የሚረዳውን ሰው እርዳው፣ የሚክደውን ሰው ክዳው።*»

ይህን ዱአዕ (ፀሎት) የሚያሳየው በዛን ዕለት ዓሊይ የተሰጠው ኃላፊነት አንዳንዱን ሰው ጠላቱ ሌላውን ደግሞ ወዳጁ እንደሚያደርግና ኃላፊነቱን ለመወጣት ደግሞ አጋዦችና ተባባሪዎች እንደሚያስፈልጉት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ኃላፊነት ደግሞ በመሪነትና በአመራር ቦታ ላይ ለሚሆን ሰው እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

«ወዳጅነትን» ለመመስረት የአጋሮች/ረዳቶች አስፈላጊነት ምን ይሆን? ወዳጅነትን ለመፍጠር ረዳት አስፈልጎ ያውቃል?

**ሦስተኛ፡-** ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለዕድምተኞቹ ያስታወቁት የአላህ ጥሪ፡-
«*በቅርቡ በአላህ ሳልጠራ አልቀርምና እኔም ለጥሪው ምላሽ እሰጣለሁ፡፡*»

ይህ ደግሞ በግልጽ የሚያሳየው ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሞት በኋላ ለሙስሊሙ መሪ የሚሆን ሰው ለመሾም ቅድሚያ ሆኔታውን እያዘጋጁ መሆኑን ነው፡፡

**አራተኛ፡-** የሰሃቦቹ ለዓሊይ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክት መናገርና ደስታቸውን መግለጽ የአዋጁን ትክክለኛ ትርጉም ለመጠርጠርና ውዥንብር ለመፍጠር ያለውን ክፍተት በሙሉ ይዘጋሉ፡፡

**አምስተኛ፡-** ክስተቱ፣ ቦታና ጊዜው

እስቲ አስቡ! ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በጠራራ ፀሐይ በእኩለ ቀን፣ በድካም የዛሉትን ከመቶ ሺህ በላይ የሚገመቱ መንገደኞችን ጉዞአቸውን እንዲገቱ ሲያደርጉና አሸዋው በሚለበልበው የአረቢያ በረሃ ውስጥ በእሾሃማ ቦታ ላይ እንዲኮለኮሉ ሲያደርጉና የግመል ኮርቻ በማነባበር ከፍ ያለ መድረክ ሲዘጋጅ፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ እስቲ ደግሞ አስቡት ነቢዩ ረዥም የሆነ ንግግር ካደረጉ በኋላ፣ ከዚህ ሁሉ ዝግጅት በኋላ በመጨረሻ፣ «እኔን የሚወደኝ ሰው አሊይን መውደድ አለበት» ወይም «እኔ ወዳጅ የሆንኩት ሰው ሁሉ ዓሊይም ወዳጁ ነው» በማለት ሲያውጁ፡፡

ለመሆኑ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ለጤነኛ አዕምሮ ይዋጣል? በጭራሽ! ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች በዚህ በማይመስል ጨቅላ በሆነ ባህሪ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለመውቀስ ሲጣጣሩ ይስተዋላሉ፡፡

«መውላ» የሚለው ቃል ትርጉሙ «ወዳጅ» ከሆነ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክቱ ለምን አስፈለገ? ኡመር በዛሬው ዕለት (በአንድ ቀን/ ውስጥ/ የሁሉም መውላ ለመሆን በቃህ ሲል ዓሊይ ከዛ በፊት የሁሉም አማኞች ጠላት ነበር ማለት ነው?

ኢማም ዓሊይ (ዐ.ሰ) ራሱ ለሙዓዊያህ እንዲህ ብሎ ጽፏል፡-

*«...የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) በአንተ ላይ ስልጣን ያለኝ መሆኑን በዕለተ ገዲር ኹም አረጋግጠውልኛል፡፡»*

*(አል-አሚኒ፡ አል-ገዲር፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 340)*

በተጨማሪም ብዙ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች ግጥማቸው ውስጥ «መውላ» የሚለውን ቃል ኢማም (መሪ) ገኘ የወል ትርጉም ባለው አገባብ ተጠቅመዋል፡፡

ስፍር ቁጥር የሌላቸው የቁርአን፣ የአረብኛ ቋንቋ ሰዋሰውና የሥነ-ጽሑፍ ምሁራን «መውላ» የሚለውን ቃል «አውላ» በሚለው ቃል ተርጉመዋል፡፡ «አውላ» ማለት ደግሞ «በላጭ፣ ብዙ የሚገባው፣ የበለጠ ትክክለኛ፣ በጣም ተገቢ የሆነ» እንደማለት ነው፡፡

**ዓሊ (ዐ.ሰ) የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «አካል»**

የዓሊይ ኢብን አቢ ጧሊብን ኢማምነት ወይም መሪ መሆንን በተመለከተ በርካታ የቁርአን አናቅጽ አሉ፡፡ ሁሉንም እዚህ ቦታ ላይ መዘርዘር የማይቻል ነው፡፡ ነገር ግን የ«ሙባህላ»ን ክስተት መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ «ሙባህላ» ማለት ሁለት ቡድኖች በአንድ ጉዳይ ላይ ሳይስማሙ ሲቀርና እውነታው ሲገለጽ ሐቁን ከመቀበል ይልቅ አንዱ ቡድን ሲክድ፣ ከሁለቱ ቡድኖች በካሃዲው ወይም ውሸታሙ ላይ እርግማን ይወርድ ዘንድ በአሏህ ፊት የመረጋገም ሥርዓት ነው:: የሙባሃላ ክስተት የተከሰተው በ9ኛው ሂጅራ ነበር፡፡

በዚህ ወቅት (9ኛው ህጅሪያ) 14 አባላት ያሉት የክርስቲያኖች ልዑካን ቡድን ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ለማግኘት ነጅራን ከተባለ ቦታ ይመጣሉ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)ን እንዳገኙ፡- «*እየሱስን (ዒሳ) በተመለከተ ያለህ ሐሳብ ምንድን ነው?*» ብለው ጠየቁ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለው መለሱ፡- «*ዛሬ ዕረፍት ውሰዱና ከዚያ በኋላ ምላሼን ታገኛላችሁ*» አሏቸው፡፡

በሚቀጥለው ቀን ኢየሱስን (ዒሳ) ከሦስተኛው ሱራ ሦስት የቁርአን አንቀጾች ተገለጡ፡፡

ክርስቲያኖቹ (ነሷራዎች) ግን ለጠየቁት ጥያቄ በቁርአን የተሰጠውን መልስ አስተባብለው በቀድሞ አቋማቸው

(እምነታቸው) ሲፀኑ፣ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን የቁርአን አያህ ቀሩ (በቃል አነበቡ)፡፡ (ቁርአን 3፡ 59-61)፡፡

فَمَنْ حَاجَّكَ فِيهِ مِنْ بَعْدِ مَا جَاءَكَ مِنَ الْعِلْمِ فَقُلْ تَعَالَوْا نَدْعُ

أَبْنَاءَنَا وَأَبْنَاءَكُمْ وَنِسَاءَنَا وَنِسَاءَكُمْ وَأَنْفُسَنَا وَأَنْفُسَكُمْ ثُمَّ نَبْتَهِلْ

فَنَجْعَلْ لَعْنَتَ اللَّهِ عَلَى الْكَاذِبِينَ﴿٦١﴾

«*(እውነቱን የሚገልጽ) እውቀት ወደ አንተ ከመጣ በኋላ እሱን (ዒሳ) በተመለከተ ከአንተ ጋር ለሚከራከሩት እንዲህ በላቸው፡-*»

«*ኑ፣ ልጆቻችንና ልጆቻችሁን፣ ሴቶቻችንና ሴቶቻችሁን፣ እራሳችንና እራሳችሁን ጠርተን (በጌታ ፊት) ዝቅ ብለን ዱአዕ (ፀሎት) እናድርግና በአስተባባዮቹ (የዋሉት) ላይ (እርግማን ይወርድ ዘንድ) በአላህ ፊት እንረጋገም፡፡*»» (ቁርአን 3:61)

በሚቀጥለው ቀን በአንድ ወገን ክርስቲያኖቹ ሲገኙ በሌላው ወገን ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሴንን በዕቅፍ ይዘው፣ ሐሰንን እጁን ይዘውት ከጉናቸው እየተራመደ፣ ከቤታቸው ወጡ፡፡ ከኋላቸው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ ፋጡማና ከርሷ ኋላ ደግሞ ዓሊይ ይገኛል፡፡

ክርስቲያኖቹ እነዛ አምስቱን ንጹህ ነፍሶች ሲያዩ ከተወጠነው ሙባሃላ (መረጋገም) ታቅበው ከነቢዩ ጋር ወደ ስምምነት ለመምጣት ተገደዱ፡፡

በዚህ አንቀጽ ውስጥ እንደ ጃቢር ኢብን አብድላህ አል-አንሳሪ «ልጆች» የሚለው ቃል ኢማም ሐሰንና ኢማም ሁሴንን የሚመለከት ሲሆን «ሴቶች» የሚለው ደግሞ ፋጡማን የሚመለከት ነው፡፡ «እራሳችን» (አንፉሰና) የሚለው ደግሞ ቅዱሱን ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እና ዓሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) ይወክላል፡፡ ስለዚህ በሙባሀላ አንቀጽ ውስጥ ዓሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ (ዐ.ሰ) እንደ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «አካል» ተቆጥሯል ማለት ነው:: *ቅጽ 2፡ ገጽ 38፣ አል-ዋሂዲ፡- አስባቡ ኑዙል፡ ገጽ 40፣ አል-ሱዩጢ አል-ዱል መንሱር*

ይህ የሚያመለክተው ደግሞ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የበላይነትን መሻት በህግ የተከለከለ እንደሆነ ሁሉ በዓሊይ ላይም የበላይነትን መፈለግ (ከነቢዩ አካል መሆኑ እየታወቀ) ክልክል ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሆነው በአላህ ቃል መሠረት ነው፡፡ በዓሊይ ላይ የበላይነትን መቀዳጀት የፈለገ ማንም ሰው በመሠረቱ በነቢዩ ላይም የበላይነትን እንደመፈለግ ማለት ነው፡፡

***ሀዲሶች***

በገዲር ኹም ከተደረገው አዋጅ በኋላ የዓሊይ ኢብን አቢ ጧሊብን ኸሊፋነትና ኢማምነትን እውነታ ለማረጋገጥ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ ባይታይም የተወሰኑ ሐዲሶችን ለእማኝነት መጠቃቀስ አይከፋም በሚል ህሳቤ የሚከተሉት ሐዲሶች ቀርበዋል፡፡

በሐዲሱ ሰቀለይን ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የማከተለውን ብለዋል፡-

*«ሁለት ከባባድ ነገሮችን በመካከላችሁ ትቼላችኋለሁ፡፡ እነዚህም የአላህ መጽሐፍ (ቁርአን) እና የኔ አህሉል ቤይት (ቤተሰቤ) ናቸው፡፡ ሁለቱን አጥብቃችሁ ከያዛችሁ፣ ሁለቱን መከተልና መታዘዝ እስካልተዋችሁ እስካልከዳችሁ ድረስ በፍጹም የተሳሳተ መንገድ አትሄዱም፡፡ እነዚህ ሁለቱ ደግሞ በፍጹም አይለያዩም፣ በከውሰር ላይ እኔን እስኪገናኙ ድረስ»*

አሁን ደግሞ ዓሊይ (ዐ.ሰ) ከአህሉል በይት አንዱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ (አህሉል በይት) መሪና ሀላፊ መሆኑን ሁሉም እጅ ይሰጣል፡፡ ስለዚህ ለሱ መታዘዝ ግዴታ ስለመሆኑ በሁሉም የኢስላም መዝሐቦች አጠቃላይ ተቀባይነት ባላቸው ሐዲሶች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ (ይህ

ሐዲስ በአብዛኛው የሐዲስ መጽሐፊት ውስጥ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፡- *አል-ቲርሚዚ፡- አል-ሰሂህ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 308፣ ኢብንል አሲር፡- ኡሱዱል ጋበህ፣ ቅጽ 2፡ ገጽ 12፡ አል-ሱዩጢ፡- አል-ዱሩል መንሱር፣ ቅጽ 6፡ ገጽ 7፡ አል-መተቂ አል-ህንዲ፡ ከንዙስ ኡማል (ሃይደርባድ 1312 ሂጅራ/ ገጽ 48 ይመልከቱ)፡፡*

በተጨማሪም ደግሞ «ሀዲስ አል-መንዝለህ» (የደረጃ) ቦታ ሀዲስ በመባል የሚታወቅ ሀዲስ አለ፡፡ በተቡክ ዘመቻ ወቅት (በረጀብ) (7ኛው የጨረቃ ወር) 9ኛው ሂጅሪያ/ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊይን (ዐ.ሰ) በመዲና ላይ ወክለው ከዘመቻው አስቀሩት፡፡ በዚህን ጊዜ ዓሊይ በድንጋጤና በቁጭት ተውጦ፡-

«*ወደ ኋላ እያስቀሩኝ ነው?*» ብሎ ጠየቀ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለው መለሱለት፡-

«*ዓሊይ ሆይ! ከኔ በኋላ ነቢይ ያለመኖሩ በስተቀር አንተ ከእኔ አንፃር ያለህ ቦታ ሐሩን ከሙሳ (ሙሴ) አንፃር ካለው ቦታ ጋር አንድ መሆኑ አያስደስትህም?*»

በዚህ ሐዲስ ውስጥ ነብዩ የገለጹት ሙሳ የአላህ ትዕዛዛት ለመቀበል ከህዝቡ ተለይቶ ሲሄድ ሐሩን የህዝቡን ጉዳይና ደህንነት እንዲከታተል ወደ ኋላ ትቶት እንደሄደ ሁሉ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ለተቡክ ዘመቻ ሲሄዱ ዓሊይ መዲና ላይ

ሆኖ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሌሉበት የኢስላምን ጉዳይ እዲከታተል መወከላቸውን ነው፡፡

*(ኢብን ማጀህ፡- አል-ሱነን፣ ገጽ 12፣ አህመድ፡- አል-መስነድ ቅጽ 2፣ ገጽ 174፣ አል-ነሳኢ፡- አል-ኸሳኢስ፣ ገጽ 15-16 አል-ጠሃዊ፡- ሚሽካቱል አሳር: ቅጽ 2: ገጽ 309፣ አል-ሙሂብ አል-ጠበሪ፡- ዘካኢሩል ዑቅባህ: ገጽ 63)*

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የሱራህ አል-በራአ (9ኛው ሱራ) አንቀጾችን በመካ ሰዎች ላይ መቅራትና መልዕክቱን የማስተላለፍ ክስተት ነው፡፡ በመጀመሪያ አቡ በክር በመካ ጣዖት አምላኪዎች ፊት አንቀዶችን ለማሳወቅ ተልከው ነበር፡፡ በኋላ ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዓሊይ ሱራውን (የቁርአኑን ምዕራፍ) ከአቡ በክር ተቀብሎ እራሱ መካ ላይ እንዲያስተዋውቅ አደረጉ፡፡

አቡ በክር መካ ለመድረስ ግማሽ መንገድ እንደቀራቸው እንዲመለሱ ተደረገ፡፡ በዚህን ጊዜ አቡ በክር ሱራውን ለመካ ሰዎች እንዳያዳርስ የሚከለክል የቁርአን አንቀጽ ወይም ትዕዛዛት ወርዶ እንደሆነ ጠየቁ፡፡ ከዚያም ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት መለሱ፡-

«ጅብሪል (ገብርኤል) ወደኔ መጥቶ ይህንን መልዕክት አንተ ራስህ ወይም ከአንተ የሆነ ሰው ካልሆነ በስተቀር ሌላ ማንም ሰው ማስተላለፍ የለበትም፡፡»

*(አል-ሱዩጢ፡- አል-ዱሩል መንሱር፣ ቅጽ 6፣ ገጽ 209፣ አል-ጠበሪ፡ አል-ተፍሲር፡ ቅጽ 10፡ ገጽ 47፡ አል-ነሰኢ፡ አል-ኸሳኢስ፡ ገጽ 20)*

ቀጥሎ የተጠቀሰው ሐዲስም ከዚህ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድንጋጌዎች መወሰድ ያለበትን መመሪያ አስመልክቶ ግልጽ ማስረጃ የሚሆን ነው፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

«ዓሊይ ከእውነት/ሐቅ ጋር ነው፣ እውነትም/ሐቅ ከዓሊይ ጋር ነው፡፡ ዓሊ በዞረበት ሁሉ እውነትም ይከተለዋል /አብሮ ይዞራል፡፡»

*(አል-ኸጢብ አል-ኸዋርዝሚ፡- አል-መናቅብ ገጽ 56፣ አል-ሐማዊ ፈራኢዱል ሲምተይን ቅጽ 1፡ ገጽ 176፣ አል-ኸጢብ አል-በግዳዲ፡- ታሪክ በግዳድ፣ ቅጽ 14፡ ገጽ 321)*

ሌላው ሐዲስ ደግሞ ሀዲስ አል-ኑር (የብርሃን ሀዲስ) የተሰኘ ነው፡፡ ሰይድ ዓሊ ሐመዳኒ መወዳቱል ቁርባ በተባለው ሥራቸው ውስጥ ሰልማን አል-ፋሪሲን ዋቢ በማድረግ እንደጻፉት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናግረዋል፡፡

*«እኔና ዓሊይ አዳም ከመፈጠሩ ከአራት ሺህ አመት በፊት ከአንድ ብርሃን ነው የተፈጠርነው። ከዚያም አዳም በተፈጠረ ጊዜ ያ ብርሃን በአዳም የጀርባ አጥንት አንድ ቦታ ተሰጥቶ ነበር። በመሆኑም የኋላ ኋላ በአብዱል ሙጠሊብ ጀርባ ላይ እስከተለያየን ድረስ ያንን ቦታ ይዘን ቆየን። ስለዚህ ነቢይነት በኔ ውስጥ ኸሊፋነት ደግሞ በዓሊይ ውስጥ አለ።»*

በሪያዱል ፈደኢል ውስጥ የዚህ ሐዲስ የመጨረሻው አባባል በሚከተለው መልኩ ተጽፎ ይገኛል።

*«ከዚያም እኔን ነቢይ አደረገኝ፣ ዓሊይን ደግሞ ዋሲ (ተተኪ/ኸሊፋ) አደረገ።» (በ መፋቲሁል መጣሊብ፡ ገጽ 396 እና በአል-ገንጂ፡- ኪፋያቱ ጣሊብ፣ ገጽ 176 ላይ እንደተጠቀሰው)*

**ዑሉል አምር ከሀጢአት የፀዱ (መዕሱም) መሆን አለባቸው**

አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል።

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا أَطِيعُوا اللَّهَ وَأَطِيعُوا الرَّسُولَ وَأُولِي الْأَمْرِ مِنْكُمْ فَإِنْ تَنَازَعْتُمْ فِي شَيْءٍ فَرُدُّوهُ إِلَى اللَّهِ وَالرَّسُولِ إِنْ كُنْتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ ذَٰلِكَ خَيْرٌ وَأَحْسَنُ تَأْوِيلًا ﴿٥٩﴾

«*እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ታዘዙ፣ መልዕክተኛውንና እነዚያን ከናንተ ስልጣን የተሰጣቸውንም (ኡሉል አምር) ታዘዙ፡፡ በአንድ ጉዳይ በተከራከራችሁ ጊዜ ወደ አላህና መልዕክተኛው መልሱ፡፡ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ፡፡ ይህ የተሻለና መጨረሻው ያማረ ነው፡፡*»

**(ቁርአን 4:59)**

ይህ አያህ (አንቀጽ) ሙስሊሞችን ለሁለት ዓይነት መታዘዝ ያስገድዳል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ለአላህ መታዘዝ፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለመልዕክተኛውና ለኡሉል አምር (እነዚያ ከናንተ ውስጥ የስልጣን ባለቤትነት የተቸራቸው) መታዘዝ ናቸው፡፡

የዐረፍተ–ነገሩ ቅደም ተከተል የሚያሳያው ለኡሉል አምር መታዘዝ ለመልዕክተኛው የመታዘዝን ያህል ግዴታ መሆኑን ነው፡፡

ይህ ደግሞ በቀላሉ የሚያመለክተው የኡሉል አምር ችሎታና ሁኔታ ከመልዕክተኛው ጋር ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ እንደሱ ባይኖሩ አላህ በዚህ አያህ አንድ ላይ አጣምሮ ባልገለጸ ነበር፡፡

አሉል አምር ማን እንደሆኑ ከመወሰን በፊት መልዕክተኛውን መታዘዝን በሚመለከት ያለውን ትዕዛዝ፣ የትዕዛዙን ሁሉ አቀፍና አስገዳጅ መሆንና የአላህ መልዕክተኛ ስልጣንና ኃላፊነት ምን ያህል ግዙፍና ከባድ እንደሆነ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

«***በአላህ ፈቃድ እንዲታዘዙት እንጂ አንዳችም መልዕክተኛ አልላክንም***»

ነቢያትና መልዕክተኞች የተላኩት እንድንታዘዛቸውና እንድንከተላቸዉ ነው፡፡ ተከታዮቹ በምን መታዘዝ እንዳለባቸው እንደሌለባቸው ለመወሰን የነቢዩን እያንዳንዱን ተግባር መከታተልና መፈተሽ አይጠበቅባቸውም ነበር፡፡ ይህ ደግሞ ነቢያቱና መልዕክተኞቹ ከስህተትና ከሀጢአት የፀዱ እንደነበሩ በግልጽ ያሳያል፡፡ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ አላህ ህዝቡ ያለምንም ቅደመ–ሁኔታ እንዲታዘዙዋቸው አያዝም ነበር፡፡

አላህ ነቡዩን እንድንታዘዝ በበርካታ የቁርአን አያዎች አዞናል፡፡

«***እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ታዘዙ፣ መልዕክተኛውንም ታዘዙ፡፡***» *(ቁርአን፡- 47:33፣ በተጨማሪም፡ 3:32፣ 132፣ 5:92፣ 8:1፣20,46፣ 24:54፣ 58:13፣ 64:12 ይመልከቱ)፡፡*
በሌላም ቦታ አላህ እንዲህ ይላል፡፡

«***...አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝ...***»

***(ቁርአን-4:13፣ እንዲሁም 4:69፣ 24:52፣ 33:71፣ 48:18 ይመልከቱ)***
በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ
«***መልዕክተኛውን የሚታዘዝ በእርግጥ አላህን ይታዘዛል፡፡***»
**(ቁርአን-4:80)**

በነዚህ አያዎችና በሌሎች በርካታ የቁርአን አንቀጾች ውስጥ አላህን መታዘዝ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገልጿል፡፡ ነቢያቱ መዕሱም (ከስህተትና ሀጢአት የተጠበቁ - እንከለ የለሽ) ባይሆኑ ኑሮ እንዲህ ዓይነቱ ትዕዛዝ የማይቻል ነበር፡፡ እስቲ አሁን ደግሞ የሚከተለውን አንቀጽ አስተውል፡

«***እነዚያን ከሐጢአተኞችና ከማያመሰግኑት የሆኑትን አትታዘዛቸው፡፡***» **(ቁርአን-76:26)**

ነገሩ ግልጽና አጭር ነው፡፡ ነቢያትን መታዘዝ ግዴታና ተገቢ ነው፡፡ ኀጢአተኞችን ደግሞ መታዘዝ ደግሞ ክልክል ነው፡፡

የዚህ መደምደሚያ አንድና አንድ ብቻ ነው፡፡ ይህም ነቢያት ሐጢአተኞችና መጥፎ ሰሪዎች እንዳልነበሩ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ከሀጢአትና ከስህተት የፀዱ እንከን የለሾች (መዕሱም) ነበሩ ማለት ነው፡፡

እንበልና አንድ ነብይ ሰዎችን ወደ ስህተት ወይም ጥፋት (ሐጢአት) የሚመራ ቢሆን እስቲ ምን ዓይነት የማይመስል ነገር እንደሚከሰት እናስተውል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ ለጥፋት የተዳረጉት ተከታዮች ለአላህ ቁጣ ይዳረጋሉ ማለት ነው፡፡ የነቢዩን ትዕዛዝ አክብረው ድርጊቱን ከፈፀሙ አላህ የከለከለውን ነገር ስለሰሩ ይኮነናሉ፡፡ በሌላው መልኩ ደግሞ የነቢዩን ትዕዛዝ ካልተቀበሉ ነቢዩን እንዲታዘዙ ከአላህ የታዘዘውን መመሪያ በመጣስ አሁንም ሊኮነኑ ነው፡፡ ስለዚህ መዕሱም ያልሆነ ነቢይ ለህዝቡ ውርደትን እንጂ ሌላ ፋይዳ ሊያስገኝ አይችልም ማለት ነው፡፡

በተለይ ደግሞ የእስላምን ቅዱስ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ስንመለከት አላህ እንዲህ እያለ ይነግረናል፡-

«***ነቢዩ የሚሰጣችሁን (የሚያዛችሁን) ማንኛውም ነገር ተቀበሉ፣ ከሚከለክላችሁ ማንኛውም ነገር ደግሞ ታቀቡ፡፡***»
**(ቁርአን 59:7)**

**ይህ ማለት ደግሞ የነቢዩ መፍቀድና መከልከል ምንጊዜም ከአላህ ፈቃድ ጋር የሚስማማና አላህ የወደደው ውሳኔ ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቅዱስ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) መዕሱም መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡**

**የመዕሱም ያልሆነን ሰው ትዕዛዝ ማንም ሰው እርግጠኛ ሆኖ መቀበል አይችልም፡፡**
**በሌላ የቁርአን አንቀፅ ደግሞ፡-**

«***በላቸው «አላህን የምትወዱ ከሆነ ተከተሉኝ፡፡ (ይህን ካደረጋችሁ) አላህ ይወዳችኋል፤ ሀጢአታችሁንም ይቅር ይላችኋል»፡፡***»
**(ቁርአን 3:31)**

**ከዚህ የምንረዳው የአላህ ውዴታ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ከመከተል ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነው፡፡ የሁለቱም ወገን ውዴታ (ፍቅር) በዚህ ውስጥ ተካቷል፡፡**

አላህን የምትወዱ ከሆነ ነቢዩን ተከተሉ፡፡ ነቢዩን ከተከተላችሁ አላህ ይወዳችኋል፡፡ ይህ ታዲያ ነቢዩ ከማንኛውም ወቀሳ የፀዱና የነጹ መሆናቸውን አያረጋግጥም? ተግባራቸው (ድርጊታቸው) ብቻ ሳይሆን ቃላቸውም በአላህ ትእዛዝ ነበሩ፡፡
አላህ በተከበረው ቁርአን እንዲህ ይላል፡-

«***ከራሱ ፍላጎት አንዳችም የሚናገረው ነገር የለም፣ ከአላህ በተወረደለት ወህይ («መለኮታዊ መገለጥ») ካልሆነ በስተቀር፡፡***»
**(ቁርአን 53:3-4)**

እዚህ ላይ የመጨረሻውን የእንከን–የለሽነት (መዕሱም የመሆን) ጣራ እናገኛለን፡፡
ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የቁርአን አንቀፆች ባሻገር ስለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚያወሱ ሌሎች በርካታ የቁርአን አያህ (አንቀፆች) አሉ፡፡

«***…ከነርሱ የሆነ ነቢይ የርሱን (የአላህን) ቃላት በነርሱ ላይ የሚያነብ የሆነ፣ የሚያጠራቸው የሆነ መፅሀፍና ጥበብን የሚያስተምራቸው፡፡***»
***(ቁርአን 62:2፣ በተጨማሪም 2:129፣ 3:164 ይመልከቱ)***

አንድ ነቢይ ለራሱ ንፁህ ሳይሆን (ይቅር ይበለን!) ሌሎችን ከሃጢአትና ወቀሳ እንዴት ሊያጠራ ይችላል?
አንድ ሰው ለራሱ ክፉና ደጉን የሚለይበት እውቀትና ጥበብ ሳይኖረው ሌሎችን ጥበብ ሊያስተምር እንዴት ይችላል? ይባስ ብሎ ደሞ ለራሱ ከመጥፎ ነገር (እኩይ ተግባር) የመቆጠብ ኃይል ሳይኖረው ሌሎችን እንዴት ሊገስፅ ይችላል?

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡን የአላህ መፅሀፍ የማስተማር ሃላፊነት ነበረባቸው፡፡ ይህ ማለት የአላህን ትእዛዝ ያውቁ ነበር ማለት ነው፡፡ ህዝቡን የማጥራት ጥበብ የማስተማር ድርሻ የነቢዩ ነበር፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ለራሳቸው ንፅህናና ጥበብ ነበራቸው ማለት ነው፡፡ እንዲህ በማለት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባህሪ ፍፁም እንደሆነ ቁርአን መስክሯል፡፡

«***በርግጥ አንተ እጅግ በጣም መልካም የሆነ ፀባይ ላይ ነህ፡፡***»
**(ቁርአን 68:4)**

ለስህተትና ለጥፋት የመጋለጥ እድል ያለው ሰው በዚህ መልኩ ሊገለፅ አይችልም፡፡ ይህ ደረጃ አይገባውምም፡፡ በዚህ መልኩ ሊወደስም አይችልም፡፡
እነዚህ አንቀፆች በሙሉ በግልፅ ሁለት ነገሮችን ያሳያሉ፡፡

**አንደኛ፡-** ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) በምእመናኑ ላይ ያላቸው ስልጣን በምንም መልኩ ያልተገደበና ሁሉን አቀፍ መሆኑን፣ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላለፉ ማንኛውም ትእዛዝ፣ በየትም ቦታና ወቅት፣ በማንኛውም ሁኔታ ያለምንም ቅድመ–ሁኔታ መታዘዝ፣ መቀበልና መተግበር እንደነበረበት ያመለክታል።

**ሁለተኛ፡-** ይህ ሰማያዊ ስልጣን የተሰጣቸው እንከን-የለሽ (መዕሱም) ስለሆኑ መሆኑን። ከማናቸውም ስህተትና ሀጢአት ነፃ ባይሆኑ ኖሮ አላህ ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲታዘዙ አያዝም ነበር።

በዚህ ቁርኣን አንቀፅ ውስጥ «ኡሉል አምር»ም በሙስሊሙ ላይ ተመሳሳይ ስልጣን እንዲኖራቸው ተደርጓል። ምክንያቱም መልእክተኛም ሆነ ኡሉል አምር «ታዘዙ» (አጢኡ) በሚለው ቃል በአንድነት ተጠቅሰዋል። ይህ ደግሞ በግልፅ የሚያሳየው ኡሉል አምርን መታዘዝ መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ) ከመታዘዝ ጋር ተመሳሳይ ቦታ እንዳላቸው ነው።

አሚሩል ሙእሚኒን ዓሊይ (ዐ.ሰ) የሚከተለውን እንደተናገሩ ተዘግቧል፡-

«የአላህን ትእዛዝ የማይቀበል (የማይታዘዝ) ሰው ትእዛዙን መቀበል (መታዘዝ) አይገባም፡፡ እውነት እላችኋለሁ መታዘዝ ለአላህ፣ ለነቢዩና ስልጣን ለተሰጣቸው ብቻ ነው፡፡ አላህ ህዝቡ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲታዘዙ ትእዛዝ ያስተላለፈው ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እንከን የለሽና ንፁህ ስለነበሩና ህዝቡን አላህን ባለመታዘዝ የማያዙ ስለነበሩ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አላህ ህዝቡን ስልጣን የተሰጣቸውን መሪዎችን (ኡሉል አምር) እንዲታዘዙ ያዘዛቸው ኡሉል አምርም እንከን-የለሾችና ንፁሃን በመሆናቸውና ህዝቡን አላህ ወደማይወደው ተግባር ስለማይመሩ ነው፡፡

*(አል-ሰዱቅ - ዐለሉል ሸራኢዕ፣ ቅፅ 1፡ ገፅ 123)*

## ኡሉል አምር ማለት የሙስሊም መሪዎች ማለት ነውን?

አብዛኛዎቹ የሱኒ ወንድሞቻችን «ኡሉል አምር» (ከናንተ የመሪነት ስልጣን የተሰጣቸው) የሚለውን ሀረግ ሙስሊም መሪዎችን ያመለክታል በማለት ለመተርጎም ሲዳዱ ይስተዋላሉ፡፡ ይህ ትርጓሜ ግን ምንም አይነት ምክንያታዊ የሆነ መሰረት የለውም፡፡ ታሪክን በመጠምዘዝ ላይ ብቻ የተመሰረተ ማስረጃ ቢስ ትርጓሜ ነው፡፡

አብዛኛው የሙስሊሙ ማህበረሰብ ለአምባገነን ነገስታትና መሪዎች ሎሌና አገልጋይ ሆኖ ለረጅም ጊዜ ቆይትዋል፡፡ እነዚህን መንግስታት ስልጣን ላይ ለማቆየት ደግሞ ኢስላምንና ቁርአንን በተደጋጋሚ ለስልጣናቸው በሚስማማ መልኩ ሲተረጉሙና ሲያስተረጉሙ ዘመናትን አስቆጥረዋል፡፡

እንደማንኛውም ሌላው ማህበረሰብ የሙስሊሙ ታሪክም ኢ-ፍትሃዊ፣ ዋልጌና ጨቋኝ በሆኑ የመሪዎች ስሞች የተሞላና ኢስላምን ለዘመናት ጥላሸት በመቀባት የጋን መብራት ሆኖ የኖረበት ታሪክ ነው ያለው፡፡

እንዲህ አይነቶቹ መሪዎች ምንጊዜም ነበሩ ለወደፊትም ይኖራሉ፡፡ እነዚሁ መሪዎች በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ «ኡሉል አምር» ናቸው ተብለው ይነገራሉ፡፡

አላህ እንዲህ አይነቶቹን ነገስታትና መሪዎች እንድንታዘዝ ቢያዘን ኑሮ ለሙስሊሞች አስቸጋሪና የማይመስል ሁኔታ ይፈጠር ነበር፡፡ የእንደዚህ አይነቱ የመንግስት መሪ ተከታዮች ምንም ሰሩ ምን ለአላህ ቁጣ ይዳረጋሉ፡፡ ለምን ቢባል «ሀጢያተኞችን አትታዘዙ» የሚለውን የአላህ ትእዛዝ በማስተላለፋቸው፡፡ ለነዚሁ መሪዎች ካልታዘዙ ደግሞ አሁንም «ለሙስሊም መሪዎች ታዘዙ» የሚለውን የአላህ

ትእዛዝ በመተላለፍ ለጥፋት ይዳረጋሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ይህንን አይነት ትርጓሜ ከተቀበልን ሙስሊሞች መእሱም ላልሆኑ መሪዎች ቢታዘዙም ባይታዘዙም ለዘለአለም ውርደት ይዳረጋሉ ማለት ነው፡፡

በዚህ ላይ የተለያዩ እምነትና አቋም ያላቸው የሙስሊም መሪዎች አሉ፡፡ ሻፊዒዎች፣ ወሃብዮች፣ ማሊኪዎች፣ ሐነፊዎች፣ እንዲሁም ሺዓዎችና ኢባዲያዎች አሉ፡፡ በዚህ ትርጓሜ መሰረት ለምሳሌ በኢባዲ መንግስት ስር የሚተዳደሩ የሱኒ ሙስሊሞች (ለምሳሌ ኡማን) የኢባዲ መንገድ ተከታዮች መሆን አለባቸው ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ደግሞ በኢራን ውስጥ በሺዓ አስተዳደር ስር ያሉ ሙስሊሞች የሺዓን መሪ መከተል ሊኖርባቸው ነው ማለት ነው፡፡

እነዚህ ሰዎች ይህንን የተጭበረበረ አተረጓጎማቸውን የማታ ማታ ወደ ምክንያታዊ አገላለጽ የማምጣት ድፍረቱ ይኖራቸው ይሆን?

እውቁ የሱኒ የቁርኣን ተንታኝ (ሙፈሲር) ፈክሩዲን አል-ራዚ ተፍሲጀሩል ከቢር በተባለው ስራቸው ውስጥ ይህ አንቀፅ ኡሉል አምር እንከን የለሽ (መእሱም) መሆን እንዳለባቸው እንደሚያረጋግጥ ደምድመዋል፡፡ አላህ ሰዎች ኡሉል አምርን ያለምንም ቅድመ–ሁኔታ መታዘዝ እንዳለባቸው ማዘዙ መእሱም መሆን አስፈላጊ መሆኑን

እንደሚያረጋግጥ አስቀምጠዋል፡፡ ምክንያቱም ለመሪዎች የመሳሳት ወይም ጥፋት የመስራት እድል ካላቸው ተከታዮቹ በአንድ ጉዳይ ላይ የመታዘዝም የያለመታዘዝም ሁኔታ ይገጥማቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የማይቻል ነገር ነው፡፡ ከዚያ አንባቢዎቹን ከአህሉል በይት ዞር ለማድረግ የሙስሊሙ ኡማህ (ህዝብ) በአጠቃላይ መእሱም ነው የሚል መርህ (ቲዮሪ) ፈጠረ፡፡

ይህኛው አተረጓጎም ደግሞ ለየት ያለ ነው፡፡ ሌላ ማንም የሙስሊም ምሁር ይህንን ቲዮሪ ጠቅሶ አያውቅም፡፡ ቲዮሪውም መሰረት ያደረገው አንድም ሀዲስ የለም፡፡ ፈኽሩ አል-ራዚ እያንዳንዱ ሙስሊም በግለሰብ ደረጃ መእሱም እንዳልሆነ አምኖ የግለሰቦቹ ድምር (አጠቃላይ ህዝቡ) ግን «መእሱም» እንደሆኑ ማመኑ እጅግ በጣም ይደንቃል፡፡ አንድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ እንኳን 200 ላሞች ሲደመር ሁለት መቶ ላሞች አንድ ላይ 400 ላሞች እንጂ 1 ፈረስ መሆን እንደማይችል ጠንቅቆ ያውቃል፡፡

በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ያሉ ብዙ የአእምሮ በሽተኖች አንድ ላይ ቢሰበሰቡ አንድ ጤነኛ ሰው ይወጣቸዋል ብሎ ማመን ፈልጎ ይሆን?

የምስራቃውያኑ ገጣሚ ኢቅበል ላሆሪ እንዲህ ይላል፡-
«*የሁለት መቶ አህዮች ጭንቅላት የአንድን ሰው ሀሳብ ሊያመነጭ አይችልም፡፡*»

በእርግጥ ይህ ሰው ባለው ጥልቅ እውቀት ኡሉል አምር እንከን-የለሽ (መዕሱም) መሆናቸውን ለማረጋገጥ በቅቷል፡፡ ነገር ግን በጭፍን አስተሳሰብ ብቻ ሙስሊሙ ኡማህ በአጠቃላይ መዕሱም እንደሆነ ለማስረዳት ተገደዋል፡፡

በተጨማሪም የቁርአኑ አያህ 'ሚንኩም' (ከናንተ የሆኑ) የሚለውን ሐረግ እንዳካተተ ቆም ብለው ሳያስቡ ቀርተዋል፡፡ ቃሉ የሚያመለክተው ግን «ኡሉል ዓምር» የተባሉት ከሙስሊሙ ኡማ ክፍል (አካል) እንጂ ሙስሊሙን ህዝብ በአጠቃላይ አይደለም፡፡ ሙስሊሙ ህዝብ በሙሉ መታዘዝ ካለበት ታዲያ ለማዘዙ ማን ቀረ? ማነው አዛዡ፣ ማነው ታዛዡ?

(ምንም እንኳ ለሌሎች ሰዎች ሀሳብ ትልቅ ከበሬታ ቢኖረንም፣ በተለይም ደግሞ የሱኒ ወንድሞቻችንን ሀሳብ ብናከብርም በዚህ አውድ ግን ፀሀፊው የአል-ራዚን ሀሳብ በተጠቀሱት ምሳሌዎች ለመተቸት የተገደደ መሆኑን ለመግለፅ ይወዳል፡፡ ለነገሩ ይህ የአል-ራዚ ሀሳብና አስተሳሰብ የሁሉም ሱኒ ወንድሞች ሀሳብ ነው ብለን አናምንም፡፡)

**የኡሉል አምር ትክክለኛ ፍቺ/ትርጉም**

እስቲ አሁን ደግሞ እላይ ወደተጠቀሰው የቁርኣን አያህ ትክክለኛ ትርጉም እንመለስ፡፡

ኢማም ጃዕፈር ሰዲቅ (ዐ.ሰ) ይህ የቁርኣን አያህ የወረደው ዓሊይ ኢብን አቡ ጧሊብ፣ ሐሰንና ሁሴይንን (ዐ.ሰ) አስመልክቶ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ይህንን የሰማ አንድ ሰው ኢማሙን እንዲህ ብሎ ጠየቀ፡-

*«ሰዎች «አላህ የአሊይንና የቤተሰቦቹን ስም በቁርኣን ውስጥ ለምን አልገለፀም» ይላሉ፡፡»*

ኢማሙ ሲመልሱ፡-

*«እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡- ሶላትን በተመለከተ ትእዛዝ መጣ እንጂ ሶስት ረከዓ ይሁን አራት አላህ አልገለፀም፡፡ ዝርዝር ጉዳዩን የነገሩን የአላህ መልእክተኛ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ዘካን በተመለከተ ትእዛዝ መጣ እንጂ ከእያንዳንዱ 40 ድርሀም 1 ድርሃም መሆኑ አልተገለፀም፡፡ ይህንን የገለጹልን የአላህ መልዕክተኛ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሀጅን በሚመለከት ትእዛዝ ቢመጣም አላህ ካእባን ሰባት ጊዜ ዙሩ (ጠዋፍ አድርጉ) ብሎ አልተናገረም፡፡ የአላህ መልክተኛ ናቸው ግልፅ ያደረጉት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አላህ «አላህን ታዘዙ፣ ነቢዩንና ከናንተ የሆኑ ስልጣን የተሰጣቸውንም ታዘዙ» የሚል ትእዛዝ*

*አወረደ። ይህ ትእዛዝ ደግሞ ዓሊይ፣ ሀሰንና ሁሴይንን በተመለከተ ነው።*»

የዚህን የቁርአን አንቀፅ ትንታኔ በተመለከተ የጃቢር ኢብን አብድላህ አል-አንሳሪ ሀዲስ ተጠቃሽ ነው። ይህ አያህ በወረደ ጊዜ ጃቢር ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ጠየቃቸው፡-

«*አላህንና ነቢዩን እናውቃለን! ግን እነዚህ ከኛ የሆኑ ስልጣን የተሰጣቸውና እነሱን መታዘዝ አላህና ነቢዩን ከመታዘዝ ጋር ተቆራኝቶ የተገለጹ እነማን ናቸው?*»

ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት መለሱ፡-
«*እነዚህ የኔ ተተኪ (ኸሊፋዎቼ) እና ከኔ በኋላ የሙስሊሙ መሪዎች ናቸው። የመጀመሪያው ዓሊ፣ ከዚያ ደግሞ ሀሰን፣ ከዚያ ሁሴይን፣ ከዚያ ዓሊ (የሁሴን ልጅ)፣ ከዚያ በተውራት አል-ባቂር በመባል የሚታወቅ የዓሊ ልጅ የሆነው ሙሀመድ። ጃቢር ሆይ! አንተ ከርሱ ጋር ትገናኛለህ፣ ስታገኘው ሰላምታዬን ንገርልኝ። እሱ ደግሞ በልጁ በጃእፈር አል-ሳዲቅ ይተካል። ከዚያ ደግሞ የጃእፈር ልጅ ሙሳ፣ ቀጥሎ የሙሳ ልጅ ዓሊ፣ ቀጥሎ የዓሊ ልጅ ሙሐመድ፣ በመቀጠልም የዓሊ ልጅ ሀሰን ይተካል። ሀሰን ደግሞ ስሙና መጠሪያው ከኔ ስም ጋር በሚመሳሰለው*

*በልጁ ይተካል። እሱ በመሬት ላይ የአላህ ማስረጃ (ሁጀቱላህ) ና በቂየቱላህ (በሰዎች መካከል እምነት ቀጣይነት እንዲኖረው አላህ ያስቀረው) ይሆናል። ዓለምን በሙሉ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ይቆጣጠራል። ከተከታዮቹ ዓይኖች (እይታ) ለረዥም ጊዜ ስለሚሰወር የእሱ ኢማምነት አላህን እምነታቸውን በሞከራቸው ልቦች ውስጥ ብቻ ይቀራል፡፡*»

ጃቢር እንዲህ ብሎ ጠየቀ፦

«*የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ተከታዮቹ ከመሰወሩ ይጠበቃሉ?*»

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲመልሱ፦

«*አዎ! በነቢይነት በላከኝ አላህ እምላለሁ። ተከታዮቹ በብርሃኑ ይመራሉ። በመሰወሩ ጊዜም ከዊላያው (መሪነቱ) ይጠቀማሉ። ልክ ሰዎች ፀሐይ በደመና ስር በተደበቀች ጊዜ እንኳ እንደሚጠቀሟት ማለት ነው። ጃቢር ሆይ! ይህ ከተደበቀው የአላህ ሚስጢር ነው። ከተከበረው የአላህ እውቀት ነው። ስለዚህ ማወቅ ከሚገባቸው ሰዎች በስተቀር ጠብቀው፡፡*»

*(አል-ኸዛዝ - ኪፋየቱል አሳር፦ ገፅ 53)*

ይህ ሀዲስ የተወሰደው ከሺዓ ምንጮች ነው፡፡ የሱኒ ሐዲሶች እምብዛም ዝርዝር ጉዳይ የላቸውም፡፡ ይሁን እንጂ አስራ ሁለቱ ኢማሞችን በተመለከተ ብዙ የሱኒ ሀዲሶች አሉ፡፡ በሚቀጥለው ምእራፍ ውስጥ ይጠቃቀሳሉ፡፡

እንግዲህ አሁን «እነዛ ስልጣን የተሰጣቸው» ማን እንደሆኑ ስለአወቅን ጨቋኝና ኢ-ፍትሃዊ የሆኑ መሪዎችን መታዘዝ በተመለከተ ጥያቄ እንደማይነሳ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ የቁርአን አንቀጽ ሙስሊሞች ጨቋኝ፣ ኢ-ፍትሃዊ፣ መሐይም፣ ራስ ወዳድና በቅሌት ውስጥ የተዘፈቁ መሪዎችን እንዲታዘዙ አልታዘዙም፡፡ ሙስሊሞች የታዘዙት የተጠቀሱትን አስራ ሁለቱን ኢማሞች ናቸው፡፡ ሁሉም ኢማሞች ደግሞ ከሀጢአት የፀዱ፣ ከመጥፎ አስተሳሰብና ተግባር ነፃ የሆኑ ናቸው፡፡

እነሱን መታዘዝ በፈለገው መንገድ አደጋ/ኪሳራ የለውም፡፡ እንዲያውም ከሁሉም አደጋዎችና ኪሳራዎች ይጠብቃቸዋል፡፡ ምክንያቱም ከአላህ ፈቃድ ውጭ በሆነ ነገር ትእዛዝ አያስተላልፉም፡፡ የሰውን ልጅ በፍቅር፣ በፍትህና በእኩልነት ያያሉ፣ ይመራሉ፡፡

### አስራ ሁለት ኸሊፋዎች ወይም ኢማሞች

አስራ ሁለቱን ኸሊፋዎች/ኢማሞች በተመለከተ የአል-ሀፊዝ ሱለይማን ኢብን ኢብራሂም አል-ቁንዱዚ አል-ሐነፊን የናቢዑል መወደህ 77ኛው ምእራፍ ብዙ ክፍሎች ማየት ይመከራል፡፡ በበርካታ መጽሀፍት ውስጥ አል-ቡኻሪ፣ ሙስሊም፣ አቡ ዳውድና አል-ቲርሚዚን ጨምሮ በሁሉም ዘንድ የታወቀ አንድ ሀዲስ ይጠቀሳል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

«አስራ ሁለት ኢማሞች ይነሳሉ፤ ሁሉም ከቁረይሽ ይሆናሉ፡፡» ጸሀፊው በርካታ ሀዲሶችን ይጠቅሳሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ሀዲስ እንኳ እንደተናገሩ ይጠቅሳሉ፡- «እኔ፣ ዓሊይ፣ ሐሰን፣ ሁሴንና ዘጠኝ የሁሴን ዝርያዎች ከእንከን ሁሉ የፀዱና ከሀጢአት ነፃ የሆንን ነን፡፡»

በተጨማሪም ፀሐፊው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ለሁሴን እንደተናገሩ ዘግበዋል፡-

«አንተ አለቃ ነህ፣ የአለቃ ወንድም ነህ፡፡ አንተ ኢማም ነህ፤ የኢማም ልጅ ነህ፤ የኢማም ወንድም ነህ፡፡ አንተ የአላህ ማስረጃ (ሁጃህ) ነህ፤ የማስረጃ ልጅ፣ የማስረጃ

ወንድምና የዘጠኝ ማስረጃዎች አባት ነህ፡፡ ዘጠነኛውም አል-መህዲ ይሆናል፡፡»

እነዚህን የመሰሉ በርካታ ሀዲሶችን ከጠቃቀሱ በኋላ ጸሀፊው የሚከተለውን ጽፈዋል፡-
«ከነቢዩ በኋላ የሚነሱ ኸሊፋዎች አስራ ሁለት መሆናቸውን በተመለከተ ግልጽ ማስረጃዎች ከተለያዩ በርካታ የሐዲስ ፍሰት ሰንሰለት (አስናድ) እንዳሉ ብዙ ምሁራን መስክረዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከዘመናት የጊዜ ጉዞና ከታሪክ ክስተቶች መረዳት እንደተቻለው በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተጠቀሱት አስራ ሁለቱ ኢማሞች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ (አህሉል ቤይት) ና ከነሱ የዘር ሀረግ እንደሆኑ በግልፅ ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም፡-

– ሐዲሱ የነቢዩ ሰሃባ የሆኑት አራቱ ኸሊፋዎች ሊሆን አይችልም፡፡ ከአስራ ሁለት ያነሱ በመሆናቸው፡፡

– ከኡመያ ጎሳ (በኒ ኡመያ) የሆኑ ኸሊፋዎችም ሊሆኑ አይችሉም፡፡

1. እነሱ ደግሞ ከአስራ ሁለት በላይ ነበሩ

2. ከዑመር ኢብን አብድልዓዚዝ በስተቀር ሁሉም ኢ-ፍትሃዊና ጨቋኝ ነበሩ፡፡

3. ከበኒ ሓሺም ጎሳ አልነበሩም፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ግን በሀዲሳቸው «ሁላቸውም ከበኒ ሓሺም ናቸው» በማለት ተናግረዋል፡፡

– የአባሲያዎች ሥርወ-መንግስት ኸሊፋዎችንም ሊያመለክት አይችልም፡፡ ምክንያቱም፡-

ሀ) እነሱም ከአስራ ሁለት በላይ ነበሩ፣

ለ) የአላህን ቃልና የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሓዲስ የተላለፈውን መመሪያ ጥሰው ነበር፡፡ ይህም ማለት፡ «***ለቅርብ ዘመዶቼ ፍቅር እንዲኖራችሁ ብቻ እንጂ ሌላ ምንዳ (አጅር) አልጠይቃችሁም***» (ቁርአን፡ 42/23) የሚለውን የቁርኣን አንቀጽም ሆነ «ሀዲሱል ክሳእ» (የካባው ሀዲስ) በመባል የሚታወቀውን የነቢዩ ሀዲስ በመጣስ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰብ አባላት (አህሉል ቤይት) እያሳደዱ እስከ መግደል የደረሱበት ጊዜ የነበረበት ኸሊፋዎች ነበሩ፡፡»

ስለዚህ የዚህ ሀዲስ ብቸኛው ትርጓሜ መሆን ያለበት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቤተሰቦች (ከአህሉል ቤይት) ከነሱ የዘር ሀረግ የሆኑ አስራ ሁለቱ ኢማሞች እንጂ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከተናገሩትም ሆነ ከታሪክ አጋጣሚ ሌላ ገለፃ ሊኖረው እንደማይችል ግልጽ የሆነ ጉዳይ ነው ማለት ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት እነዚህ ኢማሞች በጊዜአቸው ተወዳዳሪ የማይገኝላቸው በእውቀት የተካኑ፣ አቻ የማይገኝላቸው አላህን ፈሪና ጻድቃን እንዲሁም በዘመናቸው ማህበረሰብ

ውስጥ ከፍተኛ እውቅና ያላቸው፣ በቤተሰባቸው የዘር ሀረግ ውስጥ የመጨረሻውን ከፍታ ቦታ የያዙ፣ በስነ-ምግባራቸው የመልካም ስብእና ተምሳሌት ጣራ የሆኑና በአላህ ዘንድ እጅግ በጣም ከፍተኛ ክብር የነበራቸው ሲሆኑ እውቀታችን ያገኙት ደግሞ በአባታቸው አማካይነት ከአያታቸው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የወረሱና አላህ በቀጥታ ያስተማራቸው በዓለም ታሪክ ወደር ያልተገኘላቸው ፍጡራን በመሆናቸው ነው፡፡

*(አል ቁንዱዛ-ዓናቢዑል መወዳህ፣ ገፅ 444-447)*

**ስለ አሥራ ሁለቱ ኢማሞች በጥቂቱ/በአጭሩ**

**የመጀመሪያው ኢማም፡-**

*አሚሩል ሙእሚኒን አቡል ሐሰን ዓሊይ አል-ሙርተዳ ኢብን አቡ ጧሊብ፡-*

**ከነቢዩ የነቢይነት ዘመን በፊት በ10 ዓመት በረጀብ 13 (600 ዓ.ክ) በካዕባ ውስጥ ተወለዱ፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሰፈር (ሁለተኛው የጨረቃ አቆጣጠር ወር) 28፣ 11ኛው ሂጅራ (632 ዓ.ክ) ከዚህ ዓመት በሞት እንደተለዩ ዓሊይ ኢማም ሆነ፡፡ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) በኩፋ (ኢራቅ) መስጂድ ውስጥ የፈጅር (ሱብሂ) ሶላት በመስገድ ላይ እንዳሉ በተመረዘ የአብዱራህማን ኢብን ሙልጃም ሰይፍ ክፉኛ ከቆሰሉ**

**ከሁለት ቀናት በኋላ በረመዳን 21፣40 ሂጅራ (661 ዓ.ክ) ከዚህ ዓመት በሞት ተለዩ። በአል- ነጃፍ አል- ሸረፍ (ኢራቅ) ውስጥ ተቀበሩ።**

**ሁለተኛው ኢማም**

***አቡ ሙሐመድ አል-ሐሰን አል-ሙጅተባ ኢብን ዓሊይ (ዐ.ሰ)፦***

**በረመዳን 15፣ 3ኛው ሂጅራያ (625 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በ7ኛው ወይም በ28ኛው የሰፈር ወር፣ 50ኛው ሂጅራ (670 ዓ.ክ) ተመርዘው በመዲና ሞቱ።**

**ሦስተኛው ኢማም**

***ሰይዱ ሹሀዳእ (የሰማዕታት አለቃ) አቡ አብደላህ አል-ሁሴን ኢብን ዓሊይ (ዐ.ሰ)፦***

**በሸእባን (8ኛው የጨረቃ አቆጣጠር ወር) 3፣ 4ኛው ሂጅራ (626 ዓ.ክ) በመዲና ተወለዱ። ከልጆቻቸው ከሰሃቦቻቸውና ዘመዶቻቸው ጋር በ10ኛው ሙሐረም፣ 61ኛ ሂጅራ (680ዓ.ክ) በከርበላ (ኢራቅ) ሸሂድ (ሰማዕት) ሆኑ።**
**ሁሴንና ታላቅ ወንድሙ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ልጅ ፋጢማህ ዘህራ ልጆች ነበሩ።**

**አራተኛው ኢማም፡-**

***አቡ ሙሐመድ ዓሊ ዘይኑል ዓቢዲን ኢብን አል-ሁሴይን (ዐ.ሰ)፡-***

**በ5ኛው ሸዕባን፣ 38 ሂጅራ (659 ዓ.ክ) ተወልደው በ25ኛው ሙሐረም 94 ሂጅራ (712 ዓ.ክ) ወይም በ95 ሂጅራ (713 ዓ.ክ) ተመርዘው ሞቱ፡፡**

**አምስተኛው ኢማም፡-**

***አቡ ጃዕፋር ሙሐመድ አል-ባቂር ኢብን ዘይኑል ዓቢዲን (ዐ.ሰ)፡-***

**በረጀብ 1፣ 57ኛው ሂጅራ (677 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በዙል ሂጃህ (12ኛው የጨረቃ አቆጣጠር ወር) 7፣ 11ኛው ሂጅራ (733 ዓ.ክ) ተመርዘው እዛው መዲና ሞቱ፡፡**

**ስድስተኛው ኢማም፡-**

***አቡ አብደላህ ጃእፋር አል-ሳዲቅ ኢብን ሙሀመድ አል-ባቂር (ዐ.ሰ)፡-***

**በ17ኛው ረቢኡል አወል (3ኛው የአረብኛ ወር) 83 ሂጅራ (702 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በ25ኛው ሸዋል (አስረኛው ወር) 148 ሂጅራ (765 ዓ.ክ) ተመርዘው እዛው በመዲና ሞቱ፡፡**

**ሰባተኛው ኢማም፡-**

*አቡ ሐሰን አል--አወል ሙሳ አል-ካዚም ኢብን ጃዕፈር አል-ሰዲቅ (ዐ.ሰ)፡-*

**ከመዲና 7 ማይል ርቃ በምትገኝ አብዋ በሚባል ቦታ በ7ኛው ሰፈር፣ 129 ሂጅራ (746 ዓ.ክ) ተወልደው በ25ኛው ረጀብ 183 ሂጅራ (799 ዓ.ክ) ተመርዘው ሞቱ። የሞቱት በሐሩን አል-ረሺድ (አምስተኛው የአባሲያዎች ኸሊፋ) እስር ቤት ውስጥ ባግዳድ ላይ የሞቱ ሲሆን የተቀበሩት በባግዳድ በስተሰሜን አስር ኪሎ ሜትር ርቆ በሚገኝ አል- ካዚሚያ (በቀድሞ አጠራር መቃብር ቁረይሽ (የቁረይሽ መቃብር) በሚሰኝ ቦታ ነው።**

**ስምንተኛው ኢማም፡-**

*አቡል ሐሰን አል-ሳኒ - ዓሊይ አል-ሪዳ ኢብን ሙሳ አል-ካዚም (ዐ.ሰ)፡-*

**በ11ኛው ዙልቃኢዳ (11ኛው የአረብኛ ወር) 148 ሂጅራ (765 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በ17ኛው ሰፈር 203 ሂጅራ (818 ዓ.ክ) መሽሁድ (ኹራስን-ኢራን) በሚባል ቦታ በመርዝ ሞቱ።**

**ዘጠነኛው ኢማም፦**

***አቡ ጃዕፋር አል-ሳኒ ሙሐመድ አል-ተቂ አል-ጃዋድ ኢብን ዓሊ አል-ሪዳ (ዐ.ሰ)፦***

**በ10ኛው ረጀብ 195 ሂጅራ (811 ዓ.ክ) መዲና ተወልደው፣ በ30ኛው ዙልቃዒዳ፣ 220 ሂጅራ (835 ዓ.ክ) ባግዳድ ላይ በመርዝ ተገድለው፣ አያታቸው አጠገብ በአል-ኻዚሚያ ተቀበሩ፡፡**

**አሥረኛው ኢማም፦**

***አቡል ሐሰን አል-ሳሊስ-ዓሊ አል-ነቂ አል-ሀዲ ኢብን ሙሐመድ አል-ተቂ (ዐ.ሰ)፦***

**በ5ኛው ረጀብ፣ 212 ሂጅራ (827 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በ3ኛው ረጀብ፡ 254 ሂጅራ (868 ዓ.ክ) በሰመራህ (ኢራቅ) ውስጥ ተመርዘው ሞቱ፡፡**

**አስራ አንደኛው ኢማም፦**

***አቡ ሙሐመድ አል-ሐሰን አል-ዓስከሪ ኢብን ዓሊ አል-ነቂ (ዐ.ሰ)፦***

**በ8ኛው ረቢዑሳኒ (4ኛው የአረብኛ ወር) 232 ሂጅራ (846 ዓ.ክ) በመዲና ተወልደው በ8ኛው ረቢዓል አወል፣ 260 ሂጅራ (874 ዓ.ክ) በሰመራህ በመርዙ ሞቱ፡፡**

**አሥራ ሁለተኛው ኢማም፡-**

***አቡል ቃሲም ሙሐመድ አል-ሓዲ ኢብን አል-ሐሰን አል-ዓስከሪ (ዐ.ሰ)፡-***

**በ5ኛው ሻዕባን፣ 255 ሂጅራ (869 ዓ.ክ) በሰመራህ ተወለዱ፡፡ እሳቸው የአሁኑ ዘመን ኢማማችን ናቸው፡፡ በ260 ሂጅራ (874 ዓ.ክ) ከተሰወሩ በኋላ እስከ 329 ሂጅራ 944 በዚህ ሁኔታ ቆዩ (ትንሹ/አጭሩ መሰወር)፡፡ ከዚያ በኋላ እስከ አሁኑ ዘመን የቆየ በትልቁ መሰወር ሁኔታ ውስጥ ናቸው፡፡ አላህ በፈቀደላቸው ጊዜ የአላህን መንግስት በምድር ላይ በማቋቋም በኢ-ፍትሃዊነትና ጭቆና የተሞላችውን ምድር በፍትህና በእኩልነት ለመሙላት ይነሳሉ፡፡ አስራ ሁለተኛው ኢማም፣ አል-ቃእም፣ (የሚነሳው)፣ አል-ሁጃህ (ማስረጃው)፣ ሰሂብ አል-ዘመን (የዘመናችን አለቃ/መሪ)፣ ሳሂብ አል-አምር (የሰማያዊው ስልጣን ባለቤት) ናቸው፡፡**

# ክፍል ሦስት

# ኢማማህ በሱኒዎች ዕይታ

**ኸሊፋነት (ኺላፈህ) በሱኒ ዕይታ**

በአሁኑ ጊዜ አብዛኛዎቹ ሱኒዎች ዓሻእሪዎች ናቸው፡፡ እነሱና ሙእተዚላዎችንም ጨምሮ የኢማማህ (ኸሊፋህ) አስተዳደር ተቋም አስፈላጊ እንደሆነና ኸሊፋን መምረጥ በሰዎች ላይ ግዴታ እንደሆነ ያምናሉ፡፡

በሙእተዚላዎች አስተሳሰብ መሰረት ግዴታነቱ የሚመሰረተው በ «ዕቅል» (ምክንያት) ሲሆን አሻእሪዎች ደግሞ በባህል (ሐዲስ) ላይ የተመሰረተ ነው ብለው ያስባሉ፡፡

አል-ነሰፊ አል-ዓቃእድ በተሰኘው ስራቸው ውስጥ የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

«ሙስሊሞች ያለ ኢማም መኖር አይችሉም፡፡ ውሳኔዎቻቸውን ለማጽናት ለማስተግበር፣ የወንጀለኛ መቅጫ ህግጋትን ለማስተግበር፣ ድንበሮቻቸውን ለመጠበቅ፣ የመከላከያ ኃይሎቻቸውን ለማስታጠቅ፣ ቀረጥና ዘካን ለማሰባሰብ፣ ወሮበሎችን፣ ሌቦችንና ቦዘኔዎችን ለመቆጣጠር፣ የዐርብ (ጁምዓ) ና የኢድ (የበኣላት) ፀሎቶችን ለመከወን፣ በሰዎች መካከል የሚፈጠሩ ቅሬታዎችንና ጥሎች ለማስወገድ፣ በህግ ነክ

አቤቱታዎች ላይ መረጃዎችን ለማሰባሰብ፣ ለጋብቻ የደረሱ ረዳትና ወኪል አልባ የሆኑትን ለመዳርና በምርኮ የተገኙ ንብረቶችን ለማከፋፈል ኢማም ያስፈልጋቸዋል፡፡»

*(አል-ተፍተዛኒ-ሸርህ ዓቃእድ አል-ነፊሰህ፡- ገፅ 185)*

ሱኒዎች ምድራዊ መሪን ሲፈልጉ ሺዓዎች ደግሞ በምድር ላይ የአላህን መንግስት የሚያቋቁምና በምድር ላይ የተንሰራፉ እኩይ ነገሮችን ወደ ፍፃሜ የሚያመጣ ኢማም ይፈልጋሉ፡፡

*(ሚለር W.M - የአል-ባቡል ሀዲ ዓሸር-ማስታወሻዎች ትርጉም፡- ገፅ 98)*

በዚሁ መሰረት ሱኒዎች የኸሊፋን ምርጫ በተመለከተ የሚከተሉትን አራት መጠሪያዎች ያስቀምጣሉ፡-

*ሀ)* እጅማዕ፡- ይህ ማለት በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ከፍተኛ ቦታ ላይ ያሉ ተሰሚነት ያላቸው ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ ስምምነት ላይ መድረስ እንደማለት ነው፡፡ የነቢዩ ተከታይ የሆኑ የሁሉም ሰዎች ስምምነትም ሆነ ስልጣንና ተሰሚነት ያላቸው ሰዎችም ቢሆኑ በህዝቡ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሰዎች ስምምነት አስፈላጊ አይደለም፡፡ በሌላ አገላለፅ በጥቂት ሰዎች ስምምነት ሊሆን የሚችል ነው ማለት ነው፡፡

ለ) ቀድሞ በነበረው ኸሊፋ መመረጥ

ሐ) ሹራ (ጉባዔ) - በኮሚቴ የሚደረግ ምርጫ

መ) ወታደራዊ ኃይል፡- ይህ ማለት በወታደራዊ ኃይል (በትግል) ስልጣንን መቆናጠጥ  የሚችል ማንም አካል ኸሊፋ መሆን ይችላል ማለት ነው፡፡

የ«ሸርህል መቃሊድ» ፀሐፊ በገለጹት መሰረት አንድ ኢማም ሲሞትና አስፈላጊውን መስፈርት አሟላለሁ ብሎ የሚያስብ ሰው ቦታው ይገባኛል ካለ ህዝቡ ድምጽ ባይሰጠውና ቃል ኪዳን ባይገባ እንኳን ስልጣኑ ህዝብን የመጫንና ዝም የማሰኘት ኃይል ካለው ኸሊፋነቱ (ኢማምነቱ) ተቀባይነት ያገኛል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ እነዚህ መስፈርቶች እስከተሟሉ ድረስ አዲሱ ኢማም አላዋቂና ሥነ-ምግባር የጎደለው ቢሆን እንኳን ኢማም መሆን ይችላል፡፡

በተመሳሳይ ሁናቴ አንድ መሪ (ኢማም) ወይም ኸሊፋ በኃይል የበላይነት የመሪነቱን ስልጣን ከተቆናጠጠ በኋላ ሌላ በኃይል ስልጣኑን መረከብ የሚችል አካል ከተገኘ ቀድሞ የነበረው ኸሊፋ ከስልጣን ይወገድና አሸናፊው የኢማምነቱን ቦታ ይይዛል፡፡

**ኸሊፋ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች**

ሱኒዎች ለኸሊፋነት ማብቃት የሚችሉ አስር መስፈርቶችን ያስቀምጣሉ፡-

1. ሙስሊም መሆን
2. ለአቅመ-አዳም መድረስ
3. ወንድ መሆን
4. ጤነኛ አዕምሮ ያለው መሆን
5. ጀግና መሆን
6. ነፃ መሆን (ባሪያ ያልሆነ)
7. (በአካል) መገኘት የሚችል፣ ያልተሰወረ ወይም ያልተደበቀ
8. ጦርነቶችን መካሄድ የሚችል ውጊያ-ነክ ታክቲኮችን የሚያውቅ
9. ፍትሃዊ የሆነ (ዓድል የሆነ)
10. ኃይማኖታዊና ህጋዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ዳኝነትና ፍርድ መስጠት የሚችል - ሙጅተሂድ የሆነ

*(አል- ተፍተዛኒ፡- ሸርሁል መቃሲድል ጣሊቢን፣ ቅጽ 2፣ ገፅ 272፡፡ በተጨማሪም አል-ሀፊዝ ዓሊ ሙሀመድና አሚሩዲን፡- ፉልኩነጃት ፊል ኢማማህ ወል ሰላት፣ ቅጽ 1፣ ገፅ 203)*

የመጨረሻዎቹ ሁለት መስፈርቶች እንኳ ለይስሙላ ብቻ ያሉ መሆናቸውን ታሪክ በግልጽ ይመሰክራል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው መሀይምና ምግባረ ብልሹ የሆነ ሰው እንኳን ኸሊፋ (መሪ) መሆን እንደሚችል አይተናል፡፡ ስለዚህ «ፍትሃዊ መሆን» ና «ኃይማኖታዊ እውቀት» የሚሉ መስፈርቶች መሰረተ-ቢስና ለሽፋን ብቻ የተቀመጡ መሆናቸውን መረዳት አያዳግትም፡፡

ሱኒዎች «ኢስማህ» (እንከን-የለሽነት) መሪ (ኢማም) ወይም ኸሊፋ ለመሆን የግድ (አስፈላጊ) አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ ለዚህም እንደማስረጃ የሚያቀርቡት አቡ በክር በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃባዎች ፊት መድረክ ላይ ሆነው የተናገሩትን የሚከተለውን ንግግር ነው፡-

*«ህዝቦች ሆይ! ምንም እንኳን ከናንተ የተሻልኩ ባልሆንም በናንተ ላይ መሪ እንድሆን ተደርጌአለሁ፡፡ ኃላፊነቴን በሚገባ የምወጣ ከሆነ እርዱኝ፡፡ ካጠፋሁና ከተሳሳትኩ ደግሞ አርሙኝ፡፡ ሰይጣን በየጊዜው ወደኔ እንደሚመጣ ማወቅ አለባችሁ፡፡ ስለዚህ ከተበሳጨሁና ከተናደድኩ ከኔ ራቁ፡፡»*

*(አል-ሱዩጢ-ታሪኩል ኹለፋእ፣ ገጽ 71)*

በተጨማሪም አል-ተፍተዛኒ - «ሸርሁል ዐቃእድ አል-ነፊሰህ» በሚሰኘው ስራቸው ውስጥ የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

*«አንድ መሪ (ኢማም) ምግባረ-ብልሹና ጨቋኝ በመሆኑ የተነሳ ከኢማምነት ስልጣኑ ሊወገድ አይገባም፡፡»*

## የአቡ በክር ወደ ስልጣን መውጣት

ቀደም ሲል የተጠቀሱት መስፈርቶችና መመሪያዎች የተገኙት ከቁርአን አንቀጽ ወይም ሐዲስ ሳይሆን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሞት በኋላ ከተከሰቱ ክስተቶችና ድርጊቶች የተወሰዱ ናቸው፡፡

በሱኒዎች አስተሳሰብ መሰረት የመጀመሪያዎቹ አራት ኸሊፋዎች «አል-ኹለፋእ አል-ራሺዲን» (በሐቅ የተመሩ ኸሊፋዎች) በመባል ይታወቃሉ፡፡ ቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ልክ እንደሞቱ አንሷር (ረዳቶች) በመባል የሚታወቁ የመዲና ሙስሊሞች በበኒ ሰዒዳህ መጠለያ (መሰብሰብያ) ውስጥ ተሰበሰቡ፡፡

የ «ጊያሱ ሉጋት» ደራሲ እንደፃፉት ይህ የበኒ ሰዒዳህ መጠለያ አረቦች እኩይ ተግባር ለመፈፀም ሲያስቡ የሚሰበሰቡበት ሚስጢራዊ ቦታ ነበር፡፡

*(ጊያሱልዲን-ጊያሱል ሉጋት፣ ገፅ 228)*

በዚህን ጊዜ በጊዜው ህመምተኛ የነበረው ሳዕድ ኢብን ዑባድህ ወደ የክብር ወንበር ከተመራ በኋላ እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ ኸሊፋ ሆኖ ይመረጥ ዘንድም ኩታ ተከናንቦ ነበር፡፡ ከዚህ በኋላ ሰዓድ የአንሷሮችን ገድልና መልካም ጎኖች እየዘረዘረ ንግግር በማድረግ የኸሊፋነቱን ቦታ ሌላ ወገን ሳይቀድማቸው መያዝ እንዳለባቸው አሳሰበ፡፡ አንሷሮችም ሳዕድ እራሱ ኸሊፋቸው እንዲሆን እንደሚፈልጉ ገለፁ፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ጥያቄዎችን ለውይይት ማቅረብ ጀመሩ፡፡ እንዲህ ብለውም መጠየቅ ጀመሩ፡፡

«*የቁሬይሽ ሙሐጅሮች (ከመካ የተሰደዱ) ይህንን ሐሳባችንን ቢቃወሙና ከራሳቸው ወገን ተመሳሳይ ጥያቄ ቢያቀርቡ ምን ምላሽ እንሰጣቸዋለን?*»

አንዱ ቡድን እንዲህ ሲል መለሰ፡-

«*ከነሱ ወገን አንድ መሪ ከኛም ወገን አንድ መሪ እንዲሆን እንነግራቸዋለን፡፡*»

ሰዕድ፡- «*የመጀመሪያው ድክመታችሁ እዚህ ላይ ነው፡፡*»

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ሰው ለዑመር ኢብንል ኸጣብ ስለ ስብሰባው ወሬ አቀበለው፡- እንዲህም አለው፡-

«*የመሪነትን ክብር መጎናፀፍ የምትሻ ከሆነና የሚሰጠውን ውሳኔ ለመቀልበስ አስቸጋሪና የማይሞከር ከመሆኑ በፊት ሳታመነታና ሳትዘገይ ሰቂፋ መድረስ አለብህ፡፡*»

ይህንን መረጃ እንዳገኙ ዑመር አቡ በክርን አስከትሎ በፍጥነት ወደ ሰቂፋ ነጎደ፡፡ አቡ ዑበይዳህ ኢብን አል-ጀራህም ተከተላቸው፡፡ አል-ጠበሪ፣ ኢብንል አሲር፣ ኢብን ቁተይባህና ሌሎችም በሐዲስ ዘገባቸው ይህንን ሁኔታ ሲተርኩ እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡፡

ሰቂፋህ እንደደረሱ አቡ በክር፣ ዑመርና አቡ ዑበይዳህ ገና በወጉ እንኳን ሳይቀመጡ ሳቢት ኢብን ቀይስ ተነሳና የአንሷሮችን ገድልና መልካም ስም እየቆጠረና እያወደሰ ከቆየ በኋላ የኺላፈህ ወንበር መስጠት ያለበት ከአንሷር ለሆነ ሰው መሆን እንዳለበት ሐሳብ አቀረበ፡፡

ከጊዜ በኋላ ዑመር የሚከተለውን እንደተናገረ ይነገራል፡-
«የአንሷሮቹ ተናጋሪ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ ቀደም ብዬ ባሰብኩባቸው አስፈላጊ ነጥቦች ላይ ንግግር ለማድረግ ሙከራ አደረግኩ፡፡ ነገር ግን አቡ በክር ዝም እንድል ማስጠንቀቂያ ሰጠኝ፡፡ ስለዚህ ዝም አልኩኝ፡፡ አቡ በክር ከኔ ያሰብኩትን ነገር በሙሉ መናገር ብቻ ሳይሆን በተሻለ ሁኔታ ገለጸላቸው፡፡"

*(አልጠበሪ - አል-ታሪክ፣ ቅፅ 4፣ ገፅ 1820፣ ኢብንል አሲር - አል-ካሚል - አርታኢ C.J ቶርንበርግ ሌይዳን፣ 1897፣ ቅፅ 2፣ ገፅ 325ff፣ ኢብን ቁተይባህ - አል-ኢማማህ ወል ሲያሰህ፣ ካይሮ፣ 1387 ሂጅራ (1967 ዓ.ክ) ቅፅ1፣ ገፅ 18ff)*

«ረውደቱ አስሰፋ» በሚሰኝ ኪታብ ውስጥ እንደተጠቀሰው አቡ በክር በሰቂፋ ለተሰበሰቡት ሰዎች ቀጥሎ ያለውን ንግግር አድርገዋል፡-

«*የአንሷር ጀመዓ (ቡድን) ሆይ! መልካም ስማችሁን፣ ዝናችሁንና ገድላችሁን እኛም እንመሰክራለን። እስላምን ለማስፋፋትና ለማሳደግ ያደረጋችሁትን ተጋድሎና መስዋዕትም የምንዘነጋው አይደለንም። ነገር ግን ቁሬይሽ በአረብ ውስጥ ያለውን ክብርና ሞገስ ሌላ ማንም ጎሳ የለውም። በመሆኑም አረቦች ለቁሬይሽ ካልሆነ በቀር ሌላ ለማንም እጅ አይሰጡም።*»

*(ሚር ኸዋንድ-ረውደቱ አስሰፋ፣ ቅፅ 2፡ ገፅ 221)*

በተጨማሪም በ «ሲራህ አል-ሀለቢያህ» ውስጥ የሚከተለውን ተጨማሪ ሐሳብ እናገኛለን፡-

«ነገር ግን እንደሚታወቀው እኛ ሙሃጅሮች እስላምን በመቀበል የመጀመሪያዎቹ ነበርን። የእስላም ነቢይም (ሰ.ዐ.ወ) ከኛ ጎሳ ነበሩ። እኛ የመልክተኛው ዘመዶች ስለሆንን የኸሊፋነት ቦታው የሚገባን እኛ ነን። በመሆኑም የመሪነቱ ስልጣን ከኛ ውስጥ ሆኖ የሚኒስትሩን ቦታ እናንተ ብትይዙ የተሻለ ይሆናል። እናንተን ሳናማክር የምንተገብረው ነገር አይኖርም።»

*(አል-ሀለቢ - አል-ሲራህ፣ ቅፅ 3፣ገፅ 357)*

ሞቅ ያለ ክርክር ተጀመረ፡፡ ጭቅጭቁ እየተባባሰ ሲሄድ ዑመር በጩኸት እንዲህ አለ፡-

«*በአላህ ይሁንብኝ! ከዚህ በኋላ የሚቃወመንን ሰው እገድለዋሁ፡፡*» በዚህን ጊዜ አል-ሁባብ ኢብንል ሙንዝር ኢብን ዘይድ የሚባል ከኸዝረጅ ጎሳ የሆነ የአንሷር ሰው ዑመር ለመጋፈጥ ተነስቶ እንዲህ አለ፡-
«*በአላህ እምላለሁ! ማንም ሰው በኛ ላይ ኸሊፋ ሆኖ እንዲገዛን አንፈቅድም፡፡ አንድ መሪ ከናንተ ወገን ይምጣ ሌላ አንድ ደግሞ ከኛ ወገን ይሁን፡፡*»

በዚህን ጊዜ አቡ በክር እንዲህ አሉ፡-

«*ይህማ በጭራሽ ሊሆን አይችልም፡፡ የመሪነቱን ቦታ መያዝ መብቱ የኛ ነው፡፡ የናንተ ደግሞ የሚኒስትርነቱን ቦታ መያዝ ነው፡፡*»

በዚህን ወቅት አል-ሀቡብ ተነስቶ እንዲህ አለ፡-

«*አንሷሮች ሆይ! እነዚህ ሰዎች ለሚሉት ነገር እጃችሁን አትስጡ! በአቋማችሁ ፅኑ! ጠንክር በሉ! በአላህ እምላለሁ! ከዚህ በኋላ ሊቃወመኝ የሚዳዳው ሰው ካለ በዚህ ሰይፍ ነው አፍንጫውን የምቆርጠው፡፡*»

ከዚያም ዑመር እንዲህ ሲል አስታወሰ፡-

«*በአላህ እምላለሁ! በኺላፊህ ውስጥ ሁለትሾች (ጥንድ) አይመከርም፡፡ በአንድ ግዛት ውስጥ ሁለት ነገስታት ሊኖሩ አይችሉም፡፡ አረቦች የናንተን መሪነት አይቀበሉም፡፡ ምክንያቱም መልዕክተኛው (ነቢዩ) ከናንተ ጎሳ አልነበሩም፡፡*»

አል-ጠበሪና ኢብንል አሲር እንዳተቱት በዑመርና በአል-ሁባብ መካከል ረዘም ያለ የቃላት ምልልስ ነበር፡፡ ከዚያም ዑመር አል-ሁባብን «*አላህ ያጥፋህ (ይግደልህ)!*» ብሎ ሲረግመው (ሲሰድበው) አል-ሁባብም መልሶ «*አላህ ይግደልህ!*» በማለት ዑመርን ረገመው፡፡ በዚህን ጊዜ ዑመር ተስፈንጥሮ በመነሳት የሰዕድ ኢብን ዑባዳህን ጭንቅላት ይዞ እንዲህ አለው፡-

«*እያንዳንዷን አጥንትህንና መገጣጠሚያህን መሰባበር እንፈልጋለን!*»
በዚህን ጊዜ ሰዕድ በዛቻው እጅግ ተናዶ ዘሎ የዑመርን ፂም ጨምድዶ ያዘ፡፡
ዑመርም እንዲህ አለው፡-
«*አንዲቷን ፀጉር ብቻ እንኳን ብትመዝ፣ የአንተዎቹ ሁሉም እንደማይተርፉ ታየዋለህ፡፡*»

ይህ በእንዲህ እንዳለ አቡበክር ዑመር እንዲረጋጋና ሥርዓት እንዲላበስ ተማፀኑ፡፡ ዑመር ከሰዕድ ፊቱን አዞረ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰዕድ እንዲህ እያለ ነበር፡-

«*በአላህ እምላለሁ! ለመቆም ብቻ የሚያስችለኝ ትንሽ ኃይል ቢኖረኝ ኖሮ ከእያንዳንዱ መዲና ጥግ አንበሳ ሲያገሳ ትሰሙና በየጉድጓዱ ውስጥ ትደበቁ ነበር፡፡ በአላህ ይሁንብኝ! እናንተ ከነሱ ውስጥ ተከታይ እንጂ መሪ ሆናችሁ የማታውቁ ወደ ሆኑት ሕዝቦች ደግሞ እንድትቀላቀሉ እናደርጋችሁ ነበር፡፡*»

ኢብን ቁተይባህ እንደሚያስቀምጡት ደግሞ፡- የአውስ ጎሳ አለቃ የነበረው በሺር ኢብን ሰዕድ አንሷሮች የኸዥረጅ ጎሳ አለቃ ከነበረው ሰዕድ ኢብን ኡባዳህ ጋር በመስማማት ከኂላው እንደተሰለፉ ባየ ጊዜ በቅናት ተነሳስቶ የቁሬይሽ ሙሃጅሮችን እንደሚደግፍ ቆሞ ተናገረ፡፡

በዚህ ኃይለኛ ግርግር ውስጥ እንዳሉ ዑመር በድንገት ለአቡ በክር እንዲህ አላቸው፡-

«በይዓ *(ቃልኪዳን/ድምፅ) እንድሰጥህ እጅህን ዘርጋ!*»

አቡ በክር፡- «*የለም የለም! አንተ እጅህን ዘርጋና እኔ ቃልኪዳኔን (በይዓ) ልስጥ፡፡ ምክንያቱም አንተ ከኔ የተሻለ ጠንካራ ለቦታው የምትበቃ ነህ፡፡*»

ዑመር የአቡ በክርን እጅ ወስዶ በይዓ እያደረገ እንዲህ ይል ነበር፡-

«*የኔ ጥንካሬ ከአንተ ትሩፋትና ወደ እስልምና ቀድሞ መግባት ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ምንም አይደለም፡፡ ጥቅም አለው የምንል ከሆነም ደግሞ የኔና የአንተ ጥንካሬ አንድ ላይ ሲቀናጅ የኸሊፋውን ቦታ በተሳካ መልክ ይመራል ማለት ነው፡፡*»

በሺር ኢብን ሰዓድም በዚሁ ተስማማ፡፡ ኸዝረጆች በሺር ላይ ጮሁ፡፡ ይህን ያደረገው በሰዕድ ኢብን ዑባዳህ ላይ በቅናት ተነሳስቶ መሆኑን በምሬት ነገሩት፡፡ ከዚያም የአረስ ሰዎች እርስ በርሳቸው መነጋገር ያዙ፡፡ ያንን ቀን ሰዕድ ኢብን ዑባደህ ኸሊፋ ሆኖ ቢመረጥ ኖሮ ኸዝረጆች ሁሌ በአረሶች ላይ የበላይነት እንዳላቸው እየተሰማቸው ይኖሩ ነበር፣ ከአውስ ማንም ሰው ያንን ክብር አያገኝም እያሉ ይነጋገሩ ነበር፡፡ ስለዚህም የአውሳ ጎሳ ሰዎች ሁሉም ለአቡ በክር ድምፅ ሰጡ፡፡

ከኸዝረጅ ሰዎች አንዱ ሰይፉን መዝዞ አወጣ፡፡ ነገር ግን ሌሎች ተረባርበው አስጣሉት፡፡

በዚሁ ጭቅጭቅና ንትርክ ወቅት በሌላ በኩል ዓሊይና ጓደኞቹ የተቀደሰውን የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሬሳ በማጠብና ለቀብር *ሥነ-ሥርዓት* የሚደረጉትን ነገሮች በማሟላት ተጠምደው ነበር፡፡ ይህ በተጠናቀቀ ጊዜ አቡ በክር የኸሊፋነቱን ቦታ በተጠቀሰው መልኩ ተቆናጥጧል፡፡

ኢብን ቁተይባህ እንዲህ በማለት ፅፈዋል፡-

«አቡ በክር የኸሊፋነቱን ቦታ ልክ እንደያዙ ዓሊይ እየተጎተተ ወደሱ (አቡ በክር) ተወሰደ፡፡ በዚህ ወቅት ዓሊይ በተደጋጋሚ፡- «*እኔ የአላህ ባሪያና የአላህ መልዕክተኛ ወንድም ነኝ፡*» እያለ ይናገር ነበር፡፡ ከዚያም ዓሊ ለአቡ በክር በይዓ እንዲያደርግ (ድምፅ እንዲሰጥ) ታዘዘ፡፡ በዚህን ጊዜ ዓሊይ የሚከተለውን ተናገረ፡-

«*ከናንተ ከሁላችሁም ይልቅ የኸሊፋነት ቦታው ይገባኛል፡፡ ለናንተ ለመታዘዝ ቃል አልገባም፡፡ ይልቁንስ እናንተ እኔን ለመታዘዝ ቃል መግባት አለባችሁ፡፡ ከአላህ መልእክተኛ ጋር ዝምድና እንዳላችሁ በመጥቀስና ይህንኑን መሰረት በማድረግ አንሷሮች ቃል እንዲገቡ (ድምፅ እንዲሰጡ)*

*አደረጋችሁ። የኸሊፋነቱን ቦታ ከኛ ከነቢዩ ቤተሰቦች (አህሉል ቤይት) እየነጠቃችሁ ነው። እናንተ ከአንሷሮች ይልቅ የኸሊፋነቱን ቦታ ለመያዝ መብት እንዳላችሁ ያሳወቃችሁት ከነቢዩ ጋር ያላችሁን ዝምድና እንደምክንያት አቀረባችሁ አይደለም እንዴ? በዚህም ምክንያት ስልጣኑን አሳልፈው ሰጧችሁ፣ እናንተም የመሪነቱን ቦታ ወሰዳችሁ። ስለዚህ እናንተ ለአንሷሮች ያቀረባችሁትን ምክንያት እኔም ያንኑ ምክንያት ወደናንተ አቀርባለሁ። በሕይወትም ሆነ በሞት ከማንኛውም በላይ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የምንቀርብ እኛ ነን። ለምክንያታችሁ ታማኝ ከሆናችሁ ፍትሃዊ ሆናችኋል። ይህ ካልሆነ ግን እያወቃችሁ ወደ ጭቆናና አምባገነንነት ገብታችኋል።*»

በዚህን ጊዜ ዑመር እንዲህ አለ፦

«*ቃልኪዳን ካልገባህ (በይዓ ካላደረግክ) አትለቀቅም።*» ቀጠል በማድረግ ዓሊ (ዐ.ሰ) የሚከተለውን በጩኸት ተናገረ፦

«*ግቱ በእጅህ እስካለ ድረስ የቻልከውን ያህል እለብ። ዛሬ በደንብ አበረታታ፣ መሰረቱን አጠንክር፣ ነገ ለአንተ አሳልፎ ይሰጠሀልና። ዑመር ሆይ! ትዕዛዝህን*

*አልቀበልም፡፡ ለሱ ለመታዘዝ ቃል አልገባም፣ ድምጼም አልሰጥም፡፡*»

በመጨረሻም አቡ በክር እንዲህ አለ፡-

«*ዓሊ ሆይ! ቃልህን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆንክ አላስገድድህም፡፡*»»

**አጭር ዳሰሳ**

ቀደም ሲል የተጠቀሱት አብዛኞቹ ክስተቶች ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

1. በነበረው የአረቦች ባህል መሰረት አንድ ሰው (በጥቂት ቡድኖችም ቢሆን) የጎሳ አለቃ ተደርጎ ከተሾመ ሌሎች የተቀሩት ሰዎች መቃወም አይወዱም ነበር፡፡ ወደዱም ጠሉም የመቀበል ተለምዶ ነበራቸው፡፡ ይህ ባህል በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት አባስ ጭንቅላት ውስጥ ነበር፡፡ ለዚህም ነው ለዓሊይ እንዲህ ያለው፡-

   «እጅህን ስጠኝና ቃል ኪዳን ልግባልህ (በይዓ ላድርግ)፡፡ ምክንያቱም አንዴ እንደዚህ ከተደረገ በኋላ ማንም ሰው ሊያስቀርና ወደ ኋላ እንዲመለስ ሊጠይቅ አይችልም፡፡ ይህንኑን ባህል በመመርኮዝ ነው ሰዕድ አንሷሮች ማንም ሳይቀድማቸው የኸሊፋነቱን ወንበር እንዲቆናጠጡ በጥድፍያ ሰቂፋ በመሰብሰብ ምክሩን የለገሰው፡፡ ለዚህም

ነው ይህ ሁኔታ በፍጥነት ለዑመር ተነግሮት «ስቂፋ ላይ የሚደረገውን ውሳኔ ለመቀልበስ አስቸጋሪና የማይቻል ከመሆኑ በፊት ሳይዘገይ በቦታው እንዲገኝ» የተደረገው። እንግዲህ በዚህ ምክንያት ነው አንዴ የተወሰኑ ሰዎች አቡ በክርን እንደ ኸሊፋ ከተቀበሉ በኋላ አብዛኛው የመዲና ሰዎች ቢወዱም ባይወዱም ለመቀበል የተገደዱት።

2. ዓሊይ ይህንን ባህል ጠንቅቆ ያውቅ ነበር። ለምንድነው ታድያ ከአጎቱ አባስ ቃል ኪዳን (በይዓ) ይቀበል ዘንድ እጅህን ዘርጋልኝ ሲባል እምቢ ያለው። ለምን ለዓባስ «ከኔ ሌላ ማን ነው ለእንዲህ ዓይነቱ ቃል ኪዳን (በይዓ) ጥሪ ማድረግ የሚችል» አላለውም?

*(ኢብን ቁተይባህ - አል-ኢማማህ ወል ሲያሰህ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 4፣ አል-ማወርዲ - አል-አህካሙል ሱልጣንያህ፡ ገጽ 7)*

ይህ የሆነበት ምክንያት ዓሊይ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኺላፋህ የጎሳ አለቃነት እንዳልሆነ ስለሚያውቅ ነበር። ይህ ጉዳይ ከአላህ የተሰጠ ኃላፊነት እንጂ በሰዎች ምርጫ የሆነ አልነበረም። በአላህ ትዕዛዝ መሰረት በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አማካኝነት በግልጽ ለኢማምነት ስለተመረጠ የህዝቡን ድምጽ ለማግኘት ቅስቀሳ ማድረግ አይጠበቅበትም ነበር። በሰዎች ድምጽና ቃልኪዳን ላይ የተመሰረተ ሹመት አልነበረምና። ሰዎች ኢማማህ በሰዎች በይዓ ላይ የተመሰረተ ነው ብለው እንዲያስቡ ማድረግ አልፈለገም።

ህዝቡ በገዲር-ኹም ላይ የታወጀውን አዋጅ መሰረት አድርገው ወደሱ ከመጡ እሰየው፡፡ ይህንን ካላደረጉ ደግሞ የሰዎቹ ጥፋት እንጂ የሱ አይደለም፡፡

3. እስቲ አሁን ደግሞ ወደ ሰቂፋ ክስተቶች እንመለስ፡፡

በቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) የህይወት ዘመን የነቢዩ መስጊድ የኢስላማዊ እንቅስቃሴዎች ማዕከል ነበረች፡፡

የጦርነትና የሰላም ውሳኔዎች፣ የውክልናና የሹመት ቅበላ እንዲሁም የመረጃና ኃይማኖታዊ መልእክቶች የሚተላለፉት በዚሁ ማእከል ነበር፡፡ ፍትህና ፍርድ ነክ ነገሮችም የሚታዩት በዚሁ መስጊድ ውስጥ ነበር፡፡ የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ዜና እንደተሰማ ሙስሊሞች የተሰበሰቡትም በዚሁ መስጅድ ውስጥ ነበር፡፡

ታዲያ የሰዕድ ኢብን ዑባዳህ ቡድኖች ከመዲና 3 ማይል ገደማ ርቆ ወደሚገኘውና መልካም ስም የሌለው ሰቂፋ ውስጥ ለመሰብሰብ የወሰኑት ለምን ይሆን!? አብዛኛው ሰው ሳይሰማ ኸሊፋውን በማጭበርበር በድብቅ ለሰዕድ ለመስጠት አልነበረምን?

የጋዲርኹምን አዋጅና የአረብ ጎሳዎችን ልማድ (ባህል) በአንክሮ ስናይ ሌላ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ አይሆንም ለማለት ይቻላል፡፡

4. ዑመርና አቡ በክር ስለ ሰቂፋው ስብሰባ ሲሰሙ በመስጂዱ ውስጥ ነበሩ፡፡ አብዛኛው ሙስሊሞችንም እዛው መስጅድ ነበሩ፡፡ ስለ ስብሰባው ለሌላ ሰው ለምን አልተናገሩም፡፡ ሁለቱ ከአቡ ዑባይዳህ ጋር በድብቅ/በምስጢር ለምን ወጡ? ዓሊና በኒ ሓሺም በመስጅዱና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ውስጥ ስለነበሩና የስብሰባውን አሻጥር እንዲያውቁ ዑመርና አቡ በክር ስለፈለጉ ነው እንዴ? ወይስ ዓሊ የሰቂፋን ስብሰባ ዜና ቢሰማና ምናልባት እቦታው ለመገኘት ወስኖ ቢሄድ መቼም እሱ ባለበት ሌላ ሰው የመሪነቱን ቦታ ለማጽናት ስለማይችል ለእሱ (ለዓሊይ) ይሳካለታል ብለው ፈርተው ይሆን?

5. አቡ በክር ሙሓጅሮች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጎሳ መሆናቸውን ምክንያት በማድረግ መልካም ጎናቸውንና ገድላቸው እየዘረዘረ ሲያሞጋግስ ከሙሀጅሮች የበለጠ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚቀርቡ የሆኑ የነቢዩ ስጋና ደም ያላቸው የቤተሰቡ አባላት የነበሩ ሰዎች እንዳሉ አላወቀም ነበር?

ይኸው ሁኔታ ነበር ዓሊይ የሚከተለውን እንዲናገር ያደረገው፡-

احتجوا بالشجرة وأضاعوا الثمرة

*«በዛፉ (ጎሳ) ጥንካሬ ተመኩ ፍሬውን (የነቢዩን ቤተሰብ) ግን አጠፉ፡፡» (አል-ረዲ (አርታኢ) -ነህጁል በላጋህ (የሱብሂ አል-ሳሊህ እትም) ቤይሩት፡ ገጽ 98)*

ይህንን ክስተት ስሜታዊ ሳንሆን ሚዛናዊ ሆነን ስናየው «ምርጫ» ብለን ልንጠራው አንችልም፡፡ ምክንያቱም መራጮቹ (በአረቢያ ውስጥ የተበታተኑት ሙስሊሞች፣ ቢያንስ ደግሞ አጠቃላይ የመዲና ሙስሊሞች) ምርጫው የትና መቼ እንደሚደረግ ማወቁ ይቅርና ምርጫ ስለመኖሩ እንኳን የሚያቁት ነገር አልነበረም፡፡ መራጮች ይቅርና በኋላ ለተመራጭነት የበቁ ዕጩዎች እንኳን የሚያውቁት ነገር አልነበረም፡፡

መራጮች ይቅርና በኋላ ለተመራጭነት የበቁ ዕጩዎች እንኳን በሰቂፋ ይደረግ የነበረውን ጉዳይ አያውቁም ነበር፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ሁለት ነጥቦች አሁንም የኢማማ ዓሊይን አባባል ያስታውሱናል፡-

فإن كنت بالشورى ملكت أمورهم

فكيف بهذا والمشيرون غيب

وإن كنت بالقربى حججت خصيمهم

فغيرك أولى بالنبي وأقرب

*«በሙስሊሞች ጉዳይ ላይ የስልጣን ባለቤትነትን የተጎናጸፍከው በምክክር ጉባኤ ከሆነ አማካሪዎቹ በሌሉበት ሁኔታ እንዴት ሊሆን ቻለ? ተቃናቃኞችህንም ያሸነፍከው በስጋ ዝምድና ከሆነ ለነቢይነቱ ከአንተ ባላይ መብት ያለውና ለጉዳዩ የቀረበ አለ፡፡»*

***(አል-ረዲ - ነህጁል በለጋህ፣ ጥቅስ 190፡ ገፅ 502-3)***

**የአሊ ንግግር በአል-ሸሪፍ አል-ረዲ - ጥቅስ ቁጥር 190 እንደሚከተለው ተጽፏል፡-**

*«እንዴት ይገርማል!? ኸሊፋ በነቢዩ ባለሟል (ሶሃባ) መሆን እንጂ የነቢዩ ባለሟል ከመሆን ባሻገር ከነቢዩ ጋር በስጋ ዝምድና በመተሳሰር መሆን አለመቻሉ!»*

**የሚገርመው ነገር ግን በሱብሂ አል-ሳሊህ ዕትምና በሙሐመድ ዓብዱህ እትም (ቤይሩት 1973) «ነገር ግን የነቢዩ ሶሃባ (ባለሟል) በመሆን» የሚለው አባባል**

መውጣቱ (መቅረቱ) ነው። ለተሟላና ለትክክለኛው አባባል የኢብን አቢል ሀዲድ ሸርህ (ካይሮ 1959) ቅጽ 18፡ ገጽ 16 ይመልከቱ)

አሁንም «ምርጫ» ልንለው አንችልም ምክንያቱም አብዛኛው የነብዩ ታዋቂ ሶሃባዎች ስለ ክስተቱ ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም።

ዓሊ፣ ዓባስ፣ ኡስማን፣ ጠልሃ፣ አል-ዙበይር፣ ሰዕድ፣ ኢብን አቢ ወቃስ፣ ሰልማን ፋርሲ፣ አቡ ዘር አል-ግፋሪ፣ አማር ኢብን ያሲር፣ ሚቅዳድ፣ አብዱልራህማን ኢብን ዐውፍ፣ ከነዚህ ሁሉ ማንንም አላማከሩም - እንዲያውም ምንም አልተነገራቸውም። ኸሊፋውን በተመለከተ ሊቀርብ የሚችል ምክንያት ካለ የሚከተለው ብቻ ነው።

«የሰቂፋህ ክስተት ህጋዊነት ምንም ይሁን ምን አቡ በክር የኸሊፋነቱን ቦታ ለመያዝና የመሪነቱን በትር በጁ ለማድረግ ስለበቃ (በጎሳው ባህል መሰረት) «ህጋዊ» ከሊፋ ነበር ማለት ነው።

በቀላል ቋንቋ አቡ በክር ለተፈለገው ስልጣን ለመብቃት ስለተሳካለት «ህጋዊ» ኸሊፋ ለመሆን በቃ ማለት ነው። ስለዚህ ይህንን ክስተት እንዲያወድሱ ለዓመታት ትምህርት

የተሰጣቸው ሙስሊሞች ስልጣን የመያዝ ብቸኛው አማራጭ «ሀይል» መሆኑን እንዲያምኑ ትምህርት ሲሰጣቸው ቆይቷል፡፡ አንዴ መንበረ ስልጣንን መጨበጥ ከተቻለ ሁሉም ነገር ይስተካከላል፡፡ የግዛቱ ህጋዊ መሪ ትሆናለህ፡፡

በመጨረሻም የራሱ ኸሊፋነት ፈጣሪ የነበረውን የዑመርን ንግግር መጥቀስ አለብኝ፡-

« «ዑመር ሲሞት ለእከሌና ለእከሌ ድምጽ እሰጣለሁ (በይዓ አደርጋለሁ)» የሚል ሰው እንዳለ ተነግሮኛል፡፡ ማንም ሰው እንዲህ እንዳይሳሳት፡፡ ምንም እንኳን የአቡ በክር መመረጥ በድንገት ቢሆንም የኋላ ኋላ ጥሩ ሆነ፡፡ የአቡ በክር ጉዳይ እንዲህ ስለሆነ ብቻ ደግሞ ስህተት እንዳይፈጠር የአቡ በክር በድንገት ቢሆንም አላህ ከጥፋቱ ጠበቀን፡፡
አሁን ግን ማንም ሰው ይህንኑን እደግማለሁ የሚል ካለ ማንቁርቱን ነው የምቆርጥለት፡፡»

***(አል-ቡኻሪ - አል-ሰሂህ (ኪታቡል ሙሃሪቢን) ካይሮ (ቀኑ ያልተጠቀሰ) ቅጽ 8፡ ገጽ 210፣ አል- ጠበሪ - አል-ታሪክ፣ ቅጽ 4፡ ገጽ 1821)***

**የዑመር መመረጥ**

አብዛኛው የሱኒ መዝሐብ ተከታዮች በሰቂፋ የተከሰተው ክስተት «የኢስላም ዲሞክራሲያዊ መንፈስ» መገለጫ ነው ብለው ያምናሉ። በዚህ አስተሳሰብ እይታ «ዲሞክራሲያዊ ምርጫ» የሚባለውን ነገር መጠበቁ ምክንያታዊ ሊባል ይችላል። በሰቂፋ ዐውድ ያለው ትርጉም ምንም ይሁን ምን እንዲህ ዓይነቱ ምርጫ ለኢስላማዊ ኺላፍ መሰረት እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷል። ነገር ግን ይህ ሊሆን አይችልም።

ለዑመር የኸሊፋነት ስልጣን መቆናጠጥ አቡ በክር ብቸኛው የዑመር ባለውለታ ነው። ህዝቡ የመምረጥ መብት ቢሰጠው ኖሮ ዑመር በጭራሽ ዕድሉን አያገኝም ነበር። በሕዝቡ ውሰጥ የሚታወቀው ልበ ደንዳና፣ ዋልጌና ጨካኝ (ፊዘን ገሊዝ አል-ቀልብ)
ለዚህም ነው አቡ በክር ተተኪውን የመረጠው - ዑመርን።

አል-ጠበሪ የሚከተለውን ጽፈዋል፡-

«አቡ በክር ሊሞት ሲል ኡስማንን አስጠራና የመጨረሻ ኑዛዜውን ቃል በቃል ለማጻፍ ተሰናዳ። ይኸውም የሹመት ደብዳቤ ይፅፍ ዘንድ ለኡስማን ነገረው፡-

«*እጅግ በጣም ሩህሩህና አዛኝ በሆነው በአላህ ስም፡፡ ይህ ከዓብደላህ ኢብን አሊ ቁሃፋህ (የአቡበከር ሙሉ ስም) ለህዝቡ የተላለፈ ትእዛዝ ነው፡፡ ይኸውም....*» ይህን ካለ በኋላ እራሱን ሳተ፡፡ ከዚያም ኡስማን እንዲህ በማለት ጨመረ፡- «*እነሆ ዑመርን በናንተ ላይ ተተኪዬ (ኸሊፋ) አድርጌ መርጫለሁ (ሹሜአለሁ)፡፡*» ከዚያም አቡ በክር አንሰራርቶ ነቃ አለ፡፡ ቀጥሎም ኡስማን የፃፈውን እንዲያነብለት ጠየቀ፡፡ ኡስማንም አነበበለት፡፡ አቡ በክርም በደስታ «አላሁ አክበር» (አላህ ታላቅ ነው) ካለ በኋላ የሚከተለውን ተናገረ፡-

«*በዚህ ሁኔታ ብሞት ኖሮ በህዝቡ መካከል አለመግባባት ይፈጠራል ብለህ የፈራህ ይመስለኛል፡፡*»

ኡስማን፡- «*አዎ*» ብሎ መለሰ፡፡ ከዚያም አቡ በክር፡-

«*አላህ በኢስላምና በሙስሊሞች ስም ጀዛህን ይክፈልህ፡፡*» »

*(አል-ጠበሪ፡- አል-ታሪክ፣ ገጽ 2138-9)*

በዚህ ሁኔታ ትእዛዙ ተጽፎ አለቀና በህዝቡ ፊት እንዲነበብ ተደረገ፡፡ ኢብን አቢል ሀዲድ አል-ሙዕተዚሊ በጻፉት መሰረት ደግሞ አቡ በክር አዕምሮውን ሰቶ ካንሰራራ በኋላ ጸሀፊው የጻፈውን እንዲያነብለት ሲጠይቅና ተነቦ የዑመርን ስም ሲሰማ ጸሐፊውን «*ይሄን እንዴት ጻፍክ?*» ብሎ ጠየቀው፡፡ ጸሐፊውም «*እሱንማ ልታልፈው አትችልም*» አለው፡፡ በዚህን ጊዜ አቡ በክር «*አዎን ልክ ነህ*» አለው፡፡

*(ኢብን አቢል ሀዲድ፡- ሸርህ፣ ቅጽ 1 ገጽ 163-5)*
ከዚያም አቡ በክር ትንሽ ቆይቶ ህይወቱ አለፈ፡፡

ዑመር በዚህ መልኩ (ምርጫ) የኸሊፋነቱን ቦታ አገኘ፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው ከሶስት ወይም አምስት ቀን በፊት የተከሰተውን አሳዛኝ ክስተት ቆም ብለን ማስታወስ እንደሚገባን እንረዳለን ማለት ነው፡፡

በሰሂህ ሙስሊም ውስጥ የኢብን ዓባስ ሐዲስ እንዲህ ይነበባል፡-
«ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው ከሶስት ቀናት በፊት ኡመር ኢብን አል-ኸጣብን ጨምሮ ብዙ ሰሃባዎች ከነቢዩ ጎን ተኮልኩለው ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናገሩ፡-

«*እስቲ በኑዛዜ መልክ አንድ ነገር ልጻፍላችሁ፡፡ ከኔ በኋላ ወደ ጥመትና የተሳሳተ ጎዳና እንዳትገቡ ይጠቅማችሁ ዘንድ ይጻፍላችሁ፡፡*»
በዚህን ጊዜ ኡመር እንዲህ አለ፡-
«*ነቢዩ በቅዠት እየቀባጠረ ነው፡፡ የአላህ ቁርኣን (ኪታብ) ይበቃናል፡፡*» የዑመር አነጋገር በአካባቢው በነበሩ ሰዎች መካከል ትልቅ ሁከት ፈጠረ፡፡ ገሚሱ ለደህንነታችን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሰጡት ትዕዛዝ መፈጸም አለበት፡፡ ያሰቡትን ነገር

ይፃፉልን ሲሉ ገሚሱ ደግሞ ዑመርን ወገኑ። በዚህ ሁኔታ ሁከቱና ብጥብጡ እየጋለ ሲሄድ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) «*ሂዱልኝ ከዚህ!*» ብለው በቁጣ ተናገሩ።

*(ሙስሊም - አል-ሰሂህ (ኪታቡል ወሲያህ) ባቡ ታሪኩል ወሲያህ፣ ቅጽ 5፣ ገጽ 75-6፣ አል-ቡኻሪ አል-ሳሂህ (ካይሮ 1958)፣ ቅጽ 1 (ኪታቡል ዒልም) ገጽ 38-9፣ ቅጽ 4፡ ገጽ 85፣ ቅጽ 6፣ ገጽ 11-12፣ ቅጽ 7 (ኪታቡል ጥብ) ገጽ155-6፣ ቅጽ 9 (ኪታቡል ኢእቲሳም ቢል ኪታብ ወልሱና) ገጽ፡ 137)*

(እዚህ ላይ የሆነ ነገር ማስተዋል ግድ ይላል። ይኸውም ቡኻሪ ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) በሚመለከት «*ይቃዣሉ*» የሚለውን ቃል ሲዘገብ የተናጋሪውን ስም አልጠቀሰም። በሌላ ቦታ ግን «*ይቃዣል*» የሚለውን ቃል በሌላ ጨዋነት የተሞላው ቃል ሲቀይር ግን የተናጋሪውን ስም - ኡመርን በግልጽ ይጠቅሳል።)

*(ኢብን ሰዕድ - አል-ጠበቃት፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 242፣ 324፣336፣338፣ አህመል - አል-ሙስነድ፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 232፣ 239፣ 3244፣ 336፣ 355)*

ጥቂት የቁርኣን መርፌዎች እዚህ ጋር ሊጠቀሱ ይገባል፡-

«***ሙስሊሞች ድምጻችሁን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ድምጽ በላይ ከፍ ማድረግ የለባችሁም። (ይህ ካልሆነ) ሥራችሁ በሙሉ ሳታውቁት ከንቱ ይሆንባቸዋል፡፡***» (ቁርኣን 49:2)

የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ቃላት ከአላህ የሆነ «ወህይ» (መገለጥ) ነው፡፡ «***ከራሱ ስሜት የሚናገረው አንዳች ነገር የለም፡፡ ከአላህ የወረደለት ወህይ ከሆነ እንጂ፡፡***» **(ቁርኣን 53:3)**

ሙስሊሞች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚሰጥን ማንኛውም ትዕዛዝ ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ መቀበልና መታዘዝ አለባቸው፡፡ «***ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚሰጣችሁን ማንኛውንም ነገር ተቀበሉ፡፡ የሚከለክላችሁን ማንኛውም ነገር ደግሞ ተከልከሉ፡፡***» **(ቁርኣን 39:7)**

እንዲህ አይነቱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ነው እንግዲህ ከመሞታቸው ከአምስት ቀን በፊት ህዝቡ ለጥመትና ጥፋት እንዳይዳረግ በማሰብ ከጥፋት የሚጠብቃቸውን ኑዛዜ ለመጻፍ ሲፈልጉ «በቅዠት ነው የሚቀባጥረው» ተብለው የተወቀሱት፡፡

ከሥህተትና ከጥፋት የመጠበቅ (ነፃ የመሆን) ዋስትና ያልተሰጠው አቡ በክር ግን የሞት አፋፍ ላይ ሆኖ የሹመት ደብዳቤውን ቃል በቃል ሲያጽፍ የተተኪውን ስም ሳይጠቅስ አእምሮውን የሳተበት ሁኔታ መኖሩ እየታወቀ እንኳን ዑመር ለአቡ በክር «በቅዠት እየቀባጠረ ነው» አላለውም፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመጻፍ ስላሰቡት ነገር ማንም እርግጠኛ መሆን አይችልም። ሆኖም የተጠቀሙት ሐረግ ፍንጭ ይሰጠናል፡-

*«ሰዎች ሆይ! በመካከላችሁ ሁለት ውድ ነገሮችን ትቼላችኋለው። (እነሱም) የአላህ ኪታብና የቤተሰቤ አባላት የሆኑ የዘር ሐረጎቼ (ኢትረቲ አህሉል ቤይቲ) ናቸው። እነዚህ ሁለቱን አጥብቃችሁ እስኪያዛችሁ ድረስ ከኔ በኋላ ወደ ጥመትና ጥፋት መንገድ አትገቡም፡»*

ከመሞታቸው ከአምስት ቀናት በፊት ተመሳሳይ ሐረግ ሲጠቀሙና
*«እስቲ አንድ ነገር በኑዛዜ መልክ ልጻፍላችሁ። ከኔ በኋላ ወደ ጥመትና ጥፋት እንዳትገቡ ይጠብቃችሁ ዘንድ ይፃፍላችሁ»* ብለው ሲናገሩ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለመጻፍ ያሰቡት የነበረው ጉዳይ ቀደም ሲል ይናገሩት የነበረው ስለ አላህ ኪታብና ቤተሰቡ (አህሉል ቤይት) መሆኑን ለመረዳት በቂ መረጃ መሆኑን እንገነዘባለን።

ዑመርም በዚሁ መልኩ ጉዳዩን በመገመት የደረሰበት ይመስላል። «የአላህ መጽሐፍ (ቁርኣን በቂያችን ነው» በማለት «ሁለቱን ውድ ነገሮች» እንደማይከተል ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማሳወቅ ፈለገ። ለኡመር አንዱ ብቻ በቂ ነበር።

ይህንን በተመለከተ ኡመር ራሱ ከአብደላህ ኢብን ኡመር ጋር ሲነጋገር ጉዳዩን እንዳመነ እናያለን፡፡

*«....በርግጥ እሱ (ቅዱሱ ነቢይ) በህመማቸው ወቅት የዓሊይን ስም በመጥቀስ አዋጅ ለመንገር እንዳሰቡ ስለገባኝ ይህ እንዳይሆን ከለከልኩ፡፡»*

*(ኢብን አቢል ሀዲድ-ሸርህ፡ ቅጽ 12፡ ገጽ 21 (ከአል-ኸጢባል በግዳዲ - ታሪክ በግዳዲ በማጣቀስ)*

ምናልባትም «ቅዠት» የሚለው ቃል ነቢዩ መልእክቱን ጽፈው በሆነም ኖሮ ጉዳዩን ለመቀልበስ የሚረዳው ይሆን ነበር፡፡ መልእክቱ ተጽፎ ቢሆን ኖሮም በ «ቅዠት» የተጻፈ ስለሚሆን ተዓማኒነት አይኖረውም ብለው ለማመን ይጠቀሙበት ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡

**አል-ሹራ (ጉባዔ/ምክር ቤት)**

ለአስር አመት ገደማ ካስተዳደረ በኋላ ኡመር የዞራስተር እምነት ተከታይ የነበረው ፊሩዝ የሚባል ባሪያ ባደረሰበት ጥቃት ክፉኛ ቆሰለ፡፡

በዛች በኡስማን የተጻፈችው የሹመት ደብዳቤ የተነሳ ኡስማን ባለውለታው እንደሆነ ኡመር ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ነገር ግን ኡስማንን በግልጽ ተከታዩ አድርጎ ለመሾም

አልፈለገም፡፡ ህዝቡ የፈቀደውን እንዲመርጥ የሚያደርግ መብትም አልሰጣቸውም፡፡ በጣም በተቀነባበረ ሁኔታ ሶስተኛ ዘዴ ፈጠረ፡፡ እንዲህም አለ፡-

«*እውነት እላችኋለሁ! የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲሞቱ ከቁረይሽ የሆኑ በስድስት ሰዎች ደስተኛ ነበሩ፡፡ እነዚህም ዓሊ፣ ኡስማን፣ ጦልሃ፣ አል-ዙበይር፣ ሰዕድ ኢብን አቢ ወቃስና አብዱራህማን ኢብን አውፍ ናቸው፡፡ እኔ ደግሞ የኸሊፋነት ምርጫ በነዚህ ሰዎች መካከል የሚደረግ ምክክር ወይም ጉባኤ እንዲሆን ወስኛለሁ፡፡ ስለዚህ ከራሳቸው መካከል አንድ ሰው እንዲመርጡ ይሁን፡፡*»

ኡመር ለሞት ሲቃረብ ስድስቱ ሰዎች ተጠሩ፡፡ አየት ካደረጋቸው በኋላ «*ስለዚህ ሁላችሁም ከኔ በኋላ ኸሊፋ መሆን ትፈልጋላችሁ*» አላቸው፡፡ ማንም መልስ አልሰጠም፡፡ ጥያቄውን ደገመው፡፡ ከዚያም አል-ዙበይር እንዲህ አለ፡-

«*ምን የሚከለክለን ነገር አለ? አንተም አገኘኸው (ኸሊፋነቱን) በደንብ ተወጣኸውም፡፡ እኛም ደግሞ በቁሬይሽ ውስጥ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለን ቅርበትም ሆነ ወደ ሀይማኖቱ ቀድመን በመግባት ከአንተ የምናንስ አይደለንም፡፡*»

ዑመር፡- «*ስለራሳችሁ (እያንዳንዳችሁ) መናገር የለብኝም?*» ብሎ ጠየቀ፡፡

አል-ዙበይር፡- «*ንገረን! ምክንያቱም ተው አትንገረን ብንልህ እንኳን እንደማትሰማን አውቃለሁ፡፡*» አለው፡፡

ከዚያም ኡመር የአል-ዙበይርን፣ የጦልሃን፣ የሰእድ ኢብን አቢ ወቃስንና የአብዱልረህማን አውፍ መጥፎ ጎኖችን ጠቃቀሰ፡፡

ከዚያም ወደ አሊይ መጣ፡፡ እንዲህም አለ፡-

«*እውነት እልሃለሁ! ቀልደኛ ብጤ ባትሆን ኖሮ ቦታው ለአንተ ይገባህ ነበር፡፡ ነገር ግን፣ በአላህ ይሁንብኝና እናንተ ሰዎች እሱን መሪ አድርጋችሁ ብትመርጡት ጥርት ወዳለ እውነትና ወደ ተባረከ መንገድ እንደሚመራችሁ በርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፡፡*»

ከዚያም ወደ ኡስማን መልከት አደረገና እንዲህ አለው፡-

«*ከኔ ውሰደው! ከፍቅርህ የተነሳ ቁሬይሾች ይህንን ሀብል (የኺላፍነት ስልጣን) በአንገትህ ላይ ሲያደርጉ ይታየኛል፡፡ አንተ ደግሞ በኒ ኡመያና በኒ አቢ ሙኤይት (የኡስማን ጎሳ) በህዝቡ ጫንቃ ላይ (መሪ አድርገህ) ስትጭንና የሙስሊሞችን ምርኮ በተለየ ሁኔታ ለነርሱ ብቻ ስትከፋፍልና ከአረብ ተኩላዎች የተውጣጣ አንድ ቡድን መጥቶ በራስህ አልጋ ላይ ሲያርዱህ የሚታየኝ ይመስለኛል፡፡ በአላህ ይሁንብኝ ቁሬይሾች የኸሊፋነቱን*

*ስልጣን ለአንተ ከሰጡህ በርግጠኝነት ለበኒ ኡመያህ የተለየ መብት እንደምትሰጥ ነው። ይህን ካደረግክ ደግሞ በእርግጥ ሙስሊሞቹ ይገድሉሃል፡*»

ከዚያም የኡስማን ግንባር ያዝ አደረገና እንዲህ አለው፡-

«*ይህ ያልኩህ ጉዳይ ከተፈጸመ ያልኩህን አስታውስ ምክንያቱም መሆኑ የማይቀር ነውና፡*»

ከዚህ በኋላ ኡመር አቡ ጦልሃ አል-አንሷሪን ጠራና ትእዛዝ ሰጠው። ይኸውም ከቀብር ሥነ-ስርዓቱ በኋላ ከአንሷር የሆኑ አምሳ የታጠቁ ሰዎችን ከሰበሰበ በኋላ እላይ የተጠቀሱት ስድስቱ እጩዎች በአንድ ቤት ውስጥ ሆነው ከመካከላቸው አንድ ሰው ኸሊፋ አድርገው እንዲመርጡ ይደረግ። አምስቱ ተስማምተው አንድ ሰው ብቻ ከተቃወመ ያ ሰው አንገቱ ይቆረጥ። አራት ሰው ተስማምተው ሁለቱ ከተቃወሙም እነዛ ሁለቱ አንገታቸው ይቀላ። ቡድኑ ሶስት ሶስት ቦታ ከተከፋፈሉ ደግሞ የአብዱራህማን ኢብን አውፍ ቡድን ምርጫ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል። ከዚህም በኋላ ሶስቱ የተቀሩት ውሳኔውን ካልተቀበሉ የሶስቱም አንገት ይቆረጥ። ሁላቸውም ውሳኔ ላይ ሳይደርሱ ሶስት ቀናት ካለፉ ሁላቸውም አንገታቸው ይቆረጥና ከዚያ ሙስሊሙ በፍላጎቱ የፈለገውን ሰው ኸሊፋው አድርጎ ይምረጥ።

*(ኢብን አቢል ሀዲድ-ሸርህ፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 185-8፣ በተጨማሪም ኢብን ቁተይባህ - አል-ኢማማህ ወል ሲያሰህ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 23-7 እና አል-ጠበሪ - አል-ታሪክ (ግብጽ ቀኑ ያልተጠቀሰ) ቅጽ 4፣ ገጽ 33-41 ይመልከቱ)*

የሺዓ ጸሐፊ ቂጥቡዲን አል-ረወንዲ እንደዘገበው ኡመር የአብዱራህማን ኢብን አውፍ ቡድን ማሸነፍ አለበት ብሎ ሲናገር አብዱላህ ኢብን አባስ ለዓሊ እንዲህ አለው፡-

«*አሁንም ተሸንፈናል። ይህ ሰው ኡስማን ኸሊፋ እንዲሆን ይፈልጋል፡*»

ዓሊ፡- «*እኔም ይህንን አውቃለሁ። ቢሆንም ግን በሹራው (ምክክሩ) እሳተፋለሁ ምክንያቱም ኡመር በዚህ ስምምነት መሠረት ቦታው ለእኔ እንደሚገባኝ በግልጽ ተቀብሏል። ቀደም ሲል ግን ነቢይነትና ኢማማህ ከአንድ ቤተሰብ አንድ ላይ መሆን አይችልም ብሎ በእርግጠኝነት ይናገር የነበረ ቢሆንም ስለዚህ የኡመር ቃላትና ተግባሩ እንደሚቃረኑ ለህዝቡ ለማሳየት በጉባኤው (ሹራው) እሳተፋሁ፡*»

***(ኢብን አቢል ሀዲድ - ሸርህ፡ ገጽ 189)***

ኡመር ኡስማንን ኸሊፋ አድርጎ መሾም እንደሚፈልግ ኢብን አባስና አሊ እንዴት እርግጠኛ መሆን ቻሉ?

ይህ የሆነው ከጉባኤው አባላት ስብስብና ለሹራው (ጉባኤው) የተቀመጠው ህገ-ደንብን በማስተዋል ነው።

አብዱራህማን የኡስማን እህት ባለቤት ነበር። ሰዕድ ኢብን አቢ ወቃስና አብዱህማን ደግሞ የአጎት ልጆች ናቸው። ቤተሰባዊ ቁርኝት በአረብያ ውስጥ የነበረውን ቦታ ስንመለከት ሰእድ አብዱራህማንን ይቃወማል ወይም አብዱራህማን ኡስማንን ይተዋል ብሎ ማሰብ የማይታሰብ ነው። ስለዚህ የአብዱራህማን ወሳኝ ውሳኔ ጨምሮ የሶስቱ ሰዎች ድምጽ በኡስማን ጥበቃ ስር ነው ያለው ማለት ነው።

ጦልሃ (ኢብን ኡበይድላህ) ከአቡ በክር ጎሳ ነበር። ከሰቂፋ ቀን በኋላ ደግሞ በኒ ሐሺምና በኒ ተይም ጠላትነት እንጂ ምንም ያተረፉት ነገር የለም።

በግለሰብ ደረጃ ስናይ ደግሞ ዓሊ አጎቱን ዑመር ኢብን ኡስማንን፣ ወንድሙ ማሊክ ኢብን ኡበይድላህን ና የወንድሙን ልጅ ኡስማን ኢብን ማሊክን በበድር ዘመቻ ወቅት ገድሎባቸዋል። *(አል-ሼክ አል-ሙፊድ - አል-ኢርሻድ፣ (ከሼክ ሙሀመድ ባቂር ሰዒድ ኹራሳኒ የፋርስኛ ትርጉም ገጽ 65)*

ስለዚህ ለዓሊ ድጋፍ መስጠት የማይታሰብ ነው ማለት ነው።

አል-ዙበይር ደግሞ የዓሊ አክስት የነበረችው የሶፍያ ልጅ ነው። ከሰቂፋህ በኋላ ዓሊይን ወደ አቡ በክር ለመውሰድ

ብለው ወደ ቤቱ (ዓሊይ ቤት) የመጡትን ሰዎች ለመዋጋት ሰይፍ የመዘዘ በመሆኑ የዓሊ ደጋፊ ይሆናል ብሎ ማሰብ ቢቻልም የኸሊፋነቱን ቦታ ለራሱ የማድረግ ስሜት ሊፈታተነው ይችላል፡፡ ስለዚህ ዓሊ ይደግፈኛል ብሎ ተስፋ የሚያደርገው ብቸኛው ሰው አል-ዙበይር ብቻ ነው የሚሆነው፡፡ እንደዛም ሆኖ የተቀሩት አራቱ ከተቃወሙ መሸነፉ አይቀሬ ነው ማለት ነው፡፡

ጦልሃ ዓሊን ቢደጋግፍ እንኳ ዓሊ ሊያሸንፍ አይችልም ምክንያቱም እኩል ቦታ ቢከፈሉም መለያው ነጥብ የአብዱረህማን ሐሳብ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ፡፡ (በአል-ጠባሪ - አል-ታሪክ ገጽ 35 ውስጥ ይህ ትንታኔ የዓሊ የራሱ ትንታኔ እንደሆነ ተዘግቧል፡፡ በዚህ ዘገባ ውስጥ ቃለ ምልልሱ በዓሊና በአጎቱ ዓባስ መካከል እንደሆነ ይነገራል፡፡)

እንግዲህ ለምርጫው የተቀመጡትን ህገ-ደንቦች ጠለቅ ብለን ስናይ ሹራ የተባለው ነገር ለይስሙላ ከመቀመጡ ሌላ የተለየ ሁኔታ ማስገኘት እንዳማይችል ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

ጦልሃህ ለኡስማን ለማመቻቸት ከውድድሩ ራሱን አገለለ፡፡ ይህ ደግሞ አል-ዙበይር ለዓሊ ሲል ከውድድሩ እንዲወጣ

ይገፋፋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰዕድ ደግሞ ለአብዱራህማን ኢብን አውፍ እድል ለመስጠት አስቦ ከውድድሩ ውጭ ሆነ፡፡

በሶስተኛው ቀን አብዱህማን ኢብን አውፍ ስሙን ከውድድሩ አስሰረዘና አሊ የአላህን ኪታብ፣ የነቢዩን ሱና እና የአቡ በክርና ኡመርን ፈለግ ለመከተል ቃል የሚገባ ከሆነ ኸሊፋ አድርጎ ሊመርጠው እንዳሰበ ነገረው፡፡

የዓሊይ ምላሽ ምን እንደሚሆን አብዱራህማን ጠንቅቆ ያውቃል፡፡ ዓሊይ (ዐ.ሰ) እንዲህ አለው «*እኔ የምከተለው የአላህ ኪታብ፣ የነቢዩን ሱና እና የራሴን እምነት ነው፡፡*»

ከዚያም አብዱራህማን ለኡስማን ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረበለት፡፡ ኡስማን ያለማንገራገር ጥያቄውን በአዎንታ ሲመልስ አብዱራህማን የኡስማንን ኸሊፋ ሆኖ መመረጥ አወጀ፡፡

ዓሊይ ለአብዱራህማን እንዲህ አለው፡-
«*በአላህ እምላለሁ! ኡመር ከጓደኛው ተስፋ አድርጎ ያደረገውን ነገር እንጂ አንተም ለሌላ ጉዳይ አላደረከውም፡፡*» ይህ ማለት አብዱራህማን ኡስማንን ኸሊፋ አድርጎ የመረጠው ኡስማንም በተራ አብዱራህማንን

ተተኪው አድርጎ ይመርጥ ዘንድ መንገድ ለመጥረግ ታስቦ ነው ለማለት ነው፡፡

በመቀጠልም ዓሊ የሚከተለውን ተናገረ፡- «*አላህ በሁለታችሁ መካከል ጠላትነትን ያውርድ!*» ከጥቂት አመታት በኂላ በአብዱራህማንና ኡስማን መካከል ጥላቻ ሰፈነ፡፡ ለረዥም ጊዜ ሳይነጋገሩ እንደተኳረፉ አብዱረህማን ኢብን አውፍ ሞተ፡፡

**ወታደራዊ ኃይል**

ሦስተኛው ኸሊፋ ኡስማን ለወገኑና ለቤተሰቦቹ በማድላት የተለየ ጥቅም የመስጠቱ የአድሎ አሰራር ባስቆጣቸው ሙስሊሞች ተገደለ፡፡ በጊዜው የነበረው ሁኔታ ተተኪን የመምረጥ እድል እንዲያገኙ አላደረገውም፡፡
ሙስሊሞች ለመጀመሪያ ጊዜ የራሳቸው መሪ (ኸሊፋህ) ለመምረጥ ነፃ የመሆን እድል አገኙ፡፡ ወደ ዓሊይ ቤት በር ተመሙ፡፡ ነገር ግን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኂላ በነበሩት *ሀያ* አምስት ዓመታት ውስጥ የህዝቡ ባህሪና አስተሳሰብ በሚያስጠላ ሁኔታ በመቀየሩ በጊዜው የነበሩ ብዙ ታዋቂ ሰዎች የአሊይን አስተዳደር (በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘመን እንደነበረው በፍጹም ፍትህና እኩልነትን የተላበሰ አስተዳደር ቢሆንም) መቋቋም የማይችሉበት ደረጃ

ላይ ደርሰው ነበር፡፡ አረብ ያልሆኑ ሙስሊሞች ጋ በእኩል የመታየቱ ጉዳይ አልዋጥላቸው አለ፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ጦልሃ፣ አል-ዙበይርና አኢሻ አመጽ ቀሰቀሱ፡፡ ቀጥሎም ሙዓዊያህ ዓሊይን ለመዋጋት ቆርጦ ተነሳ፡፡

ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) ከተሰዋ (ሸሂድ ከሆነ) በኋላ ኢማም ሐሰን (ዐ.ሰ) ከሙአዊያህ ጋር ጦርነቱን ለመቀጠል ፈልገው ነበር፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ ሰራተኞች በሙአዊያህ ጥቅማጥቅሞች በመታለል ኮብልለው ሙአዊያን ስለወገኑና ብዙዎቹ የጦር አዛዦች የሙዓዊያን ጦር ለመግታት ሲላኩ ኢማም ሐሰንን (ዐ.ሰ) በመካድ ከጠላት ጎራ ተቀላቀሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ኢማም ሐሰን (ዐ.ሰ) ከሙዓዊያህ የቀረበለትን የሰላም ስምምነት ለመቀበል ተገደዱ፡፡

ከዚህ ስምምነት በኋላ ሱኒዎች በወታደራዊ ኃይል የመሪነትን (ኸሊፋን) ቦታ መያዝ ህጋዊ ነው ብለው ደመደሙ፡፡ ስለዚህ ለኸሊፋነት የሚያበቁ አራቱ «ህጋዊ» መንገዶች በዚህ መልኩ «ህግ» ሆነው ተቀመጡ ማለት ነው፡፡

**አጠቃላይ ዳሰሳ**

በፖለቲካው ዓለም ብዙውን ጊዜ የአንድ ሀገር ህገ-መንግስት ቀደም ተብሎ ይዘጋጅና መንግስትን የመምረጥ ወይም ህግን ለመደንገግ ወይም ለማርቀቅ ጊዜ ሲመጣ ሁሉም ነገር የሚከናወነው ህገ-መንግስቱ በሚፈቅደው መልክ ይሆናል፡፡ ከህገ-መንግስቱ ጋር የማይጋጭ ማንኛውም ክንውን ህጋዊና ተቀባይነት እንዳለው ሲወሰድ ህገ-መንግስቱን የሚፃረር ማንኛውም ክንውን ደግሞ ህጋዊ ያልሆነና ተቀባይነት የሌለው ተብሎ ይመለሳል፡፡

ስለዚህ በሱኒዎች አስተሳሰብ መሰረት ኸሊፋን (መሪ) መምረጥ የህዝቡ ኃላፊነትና ግዴታ ነው፡፡ አላህና መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ህዝቡ መሪያቸውን የሚመርጡበትን ዝርዝር አካሄድና አፈጻጸም ያለው ህግ መስጠት ነበረባቸው፡፡ ይህ ሳይሆን ከቀረ ግን ሙስሊሞቹ ራሳቸው ከምርጫው በፊት ለምርጫው የሚሆን ህግና አጠቃላይ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችን ያካተተ መስፈርት ማጽደቅ አለባቸው፡፡ ነገር ግን በሚገርም ሁኔታ ይህ አልተደረገም ነበር፡፡

እንግዲህ አሁን በዓይነቱ ልዩ የሆነ «ያልተቋቋመ» ህግ እናገኛለን ማለት ነው፡፡ በህግ የተገደበ ተግባር ሳይሆን

ሁኔታዎችን የሚከተል ህግ እንደማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ነባራዊ ሁኔታዎች ለህጉ ድንጋጌ መጠቀሚያ ሆኑ እንጂ ቀደም ብሎ የተቀመጠ ህግ አልነበረማ፡፡

ሱኒዎች እንደ ብቸኛ ማስረጃ የሚያቀርቡት የመጀመሪያው ዘመን ሙስሊሞች ኸሊፋን (መሪ) መምረጥ ኃላፊነትና ግዴታቸው እንደሆነና የነገሩን እጅግ አስፈላጊነት ለማሳወቅ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሥርዓተ-ቀብር እንኳን ወደ ኋላ በመተው የመሪነት (ኸሊፋነትን) ጥያቄ ለመመለስ ብለው በበኒ ሰዓዳህ መጠለያ (የመሰብሰቢያ ቦታ) አንደተሰባሰቡ ነው፡፡

ከዚህ ከበኒ ሰዓዳ ሲቂፋህ ክስተት በኋላ ሱኒዎች መሪን መምረጥ የህዝቡ ኃላፊነት ነው ብለው ደመደሙ፡፡ ነገር ግን ሺዓዎች ይህን የሱኒ አስተሳሰብ የሚጋፈጡት «ምርጫ» የሚባለው ነገር ራሱ የህጋዊነቱ ምንጭ ከየት ተገኘ የሚለውን መሆኑ ሱኒዎች የተረዱ አይመስልም፡፡ በሌላ አገላለፅ ሺዓዎች የሚጋፈጡት የዚህን «ምርጫ» ተብዬውን ነገር ተቀባይነት መሆኑን እንጂ አስፈላጊነቱንና አፈጻጸሙን ብቻ እንዳልሆነ አልተረዱም ማለት ነው፡፡ ሺዓዎች ድርጊቱ/ክስተቱ ህጋዊ እንዳልሆነ ሲያምኑ ሱኒዎች ዳግም ህጋዊና ትክክለኛ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

ሱኒዎች ይህንን አስተሳሰባቸውን እንደማስረጃና ማረጋገጫ አድርገው ሊያስቀምጡ እንዴት ቻሉ? ይህን አስተሳሰባቸውን እንደማስረጃ ማስቀመጥ ማለት «ያደረግነው ነገር ህጋዊ ነው ምክንያቱም አድርገዋልና» እንደማለት ነው፡፡ የትኛው የፍትህ ፍርድ ቤት ይሆን ይህንን ማስረጃ የሚቀበለው?

**ተግባራዊ ጎኑ**

የነዚህን መንገዶች አካዳሚያዊ ጉዳይ ወደ ኋላ እንተውና በሙስሊሙ የመሪነት ወይም የአስተዳደር ግንዛቤና አስተሳሰብ ላይ ያደረሰውን ተጽዕኖ እንመልከት፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ ባሉት ሰላሳ ዓመታት ውስጥ ስልጣንን ለመቆናጠጥ የሚያስችሉ ሊታሰቡ የሚችሉ መንገዶችን ሁሉ መጠቀም ብቻ ሳይሆን ህጋዊና የተለመዱ ሆነው እንዲጸኑ ተደርጓል፡፡ ምርጫ፣ ድምጽ፣ ጥቆማ፣ ወታደራዊ ኃይል ወዘተ የዕለት ተእለት ቃላትና ሐረጎች ለመሆን በቁ፡፡

የዚህ ውጤት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ የሙስሊም መሪ የኸሊፋነትን ቦታና «የመንፈሳዊ መሪነትን» ቦታ ለማግኘት ሲቋምጡ እንዲታዩ አድርጓል፡፡ የዚህ የተሳሳተ የሙስሊሞች አስተሳሰብና አቋም ለዘመናትና እስከዛሬም

ድረስ ለሙስሊሙ ዓለም የፖለቲካ አለመረጋጋትና ድክመት መሠረታዊ ምክንያት ሆኖ ይታያል።

ወታደራዊ የበላይነት ህጋዊ የመሪነት/ኸሊፋህ ቦታ ማግኛ መስፈርት እንደሆነ እንደ ሙስሊም ትምህርት የተሰጠው እያንዳንዱ የሙስሊም መሪ በስልጣን ዘመኑ የበለጠ የበላይነትን ለመጎናጸፍ ሌሎችን የሙስሊም መሪዎች ለማዳከም ይታገላል።
ስለዚህ በዚህ መልኩ ይህ «ህግ» በቀጥታ በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች በሙሉ እንዲዳከሙ አድርጓል ማለት ነው።
ከዚህም በተጨማሪ እስቲ ይህ የምርጫ ህግና መንገድ ከተፈጠረ በኋላ ያደረሰውን ተጽዕኖ ለአፍታ እንመልከት።

ይህ በአራት አቅጣጫ የሚመጣ የኸሊፋህ/መሪነት ስልጣን ለአደጋ የተጋለጠ እንደሆነ እናያለን። ይኸውም ባህሪውና የእውቀት ደረጃው ምንም ይሁን ማንም ሰው ቦታውን ሊቆናጠጥ ይችላል ማለት ነው።
ከሙዓዊያህ በኋላ ለኸሊፋነት የበቃ የመጀመሪያው ሰው ልጁ (የሙዓዊያህ) የዚድ ነው። የዚድ የተመረጠው በአባቱ በሙዓዊያህ ነው። የዚድ ለድርድር የማይቀርብ በቂ የወታደራዊ ኃይልም ነበረው። ሙስሊሞች ደግሞ በሙዓውያህ ዘመነ-መንግስት የቃልኪዳናቸውን (ድምፃቸውን) ስለሰጡ «ኢጅማእ» የሚለውንም መስፈርት

ያሚሳል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ «ህጋዊ» ኸሊፋ ለመሆን በቃ ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ለመሆኑ የየዚድ እምነት ባህሪ እንዴት ነበር?

የዚድ በግልጽ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ማመን አሻፈረኝ ያለ ሰው ነበር፡፡ እምነቱንና አስተሳሰቡን ቀደም ሲል በተገለጸው ግጥሙ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

«ለዒባት ሐሺሙ ቢል ሙልክ ፈላ ኸበሩን ጀአወለ ወህዩን ነዘል፡፡»
«የሐሺም ልጆች እንዲሁ በስልጣን (በንግስና) አፌዙ የመጣም ኸበር (ዜና) ሆኖ የወረደ ወህይ የለም፡፡»
በመጨረሻው ቀን (በትንሳኤ ቀንም) አያምንም ነበር፡፡

«ውዴ ሆይ! ከሞት በኋላ ከኔ ጋር የመገናኘቱን ጉዳይ አትመን፡፡ ምክንያቱም ከሞት በኋላ ለፍርድ እንቀሰቀሳለን ተብሎ የተነገረህ ነገር ልባችን የዚህን አለም ደስታ እንድትረሳ ለማድረግ የተፈጠረ አጉል ተረት ስለሆነ፡፡»
*(ሲብጥ አል-ጀውዚ - ተዝኪረህ፣ ገጽ 291)*

የኸሊፋውን ቦታ ከተቆናጠጠ በኋላ በግልፅ ሶላትን (ኢስላማዊ ፀሎት) መጫወቻና መቀለጃ አድርጎ ነበር፡፡ የሃይማኖት ምሁራንን ካባና መጎናጸፊያ፣ ውሾችንና

ጦጣዎችን በማልበስ ለኃይማኖቱ ክብር እንደሌለው በግልጽ አሳይቷል፡፡

ቁማርና ከድቦች ጋር መጫወት ዋነኛው የጊዜ ማሳለፍያው ነበር፡፡ በማንኛውም ቦታና ወቅት ያለ ምንም ፍራቻ እድሜውን በሙሉ ወይን በመጠጣት ያሳለፈ ሰው ነበር፡፡ ለማንኛውም ሴት ቅንጣት ያህል ክብር አልነበረውም፡፡ በስጋ ዝምድናና በጋብቻ ቁርኝት ለተከለከሉት ሴቶች እንኳ ደንታ አልነበረውም፡፡ የእንጀራ እናት፣ እህት፣ አክስትና ልጅ ወዘተ… ለሱ ሁሉም አንድ ናቸው፡፡ በሱ እይታ ሁሉም እንደ ሌሎች ማንኛውም ሴት ናቸው፡፡

የጦር ጭፍራውን ወደ መዲና ላከ፡፡ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቅድስት ከተማ መዲና በግልጽ ተዘረፈች፡፡ ሌሎች ሴቶች እንዳሉ ሆኖ ሶስት መቶ ልጃገረዶች በወታደሮቹ ተደፍረዋል፡፡ ሶስት መቶ ሀፊዘል ቁርአኖችን (ሙሉ ቁርኣንን በልባቸው ማነብነብ የሚችሉ) እና ሰባት መቶ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሶሃባዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፡፡

የቅዱሱ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ) ቅዱስ መስጂድ ለብዙ ቀናት ተዘግቶ ቆየ፡፡ የየዚድ የጦር ጭፍራ መስጂዱን እንደፈረሰ ጋጣ ተጠቀመበት፡፡ ለውሾች መጠለያ ሆነ፡፡ የነቢዩ ምንበር (መድረክ) ፈረሰ፡፡

**በመጨረሻም የጦሩ አዛዥ የመዲና ሰዎች ቃል ኪዳናቸውን እንዲሰጡ (በይዓ እንዲያደርጉ) አስገደዳቸው፡፡ በበይዓው ወቅትም የሚከተለውን ቃል በቃል እንዲያሰሙ አደረጋቸው፡-**

**«እኛ የየዚድ ባሮች ነን፣ እሱ ከፈለገ ነፃነታችንን መልሶ ይሰጠናል፣ ከፈለገ ደግሞ ወደ ገበያ ወስዶ በባሪያ ገበያ እንዳሻው ይሸጠናል፡፡»**

**በይዓ ማድረግ የምንችለው የዚድ የአላህን ኪታብ (ቁርኣን) እና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱና የሚከተል ከሆነ ብቻ ነው ብለው ቅድመ ሁኔታ ያስቀመጡ ሰዎች በሙሉ ተገደሉ፡፡**

***(አል- ሱዩጢ-ታሪኩል ኹለፋእ፡ ገጽ 209፣ አቡል ፊዳ - አል-ታሪክ፣ ቅጽ 1፡ ገጽ 192፣ ሲብጥ ኢብኑል ጀውዚ - ተዝክረቱል ኸዋስ፣ ገጽ 288፣ ሚር ኸዋንድ - ረውደቱል ሰፋ፣ ቅጽ 3፡ ገጽ 66፣ ኢብኑል ሀጀር አል-ሀይተሚ - አል-ሳዋእቁል ሙህርቃ፡ ገጽ 79)***

**እዚህ ላይ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዴ ያሉትን መጥቀሱ ተገቢ ይሆናል፡-**

***«ያ የመዲናን ሰዎች የሚያስፈራራውን (የሚያሸብረውን) ሰው አላህ ይርገመው፡፡»***

ከዚያም በየዚድ ትእዛዝ መሰረት ጭፍራው ወደ መካ ቀጠለ፡፡ የአላህ ቅድስት ከተማ ተከበበች፡፡

ወደ ከተማው በቀላሉ መግባት ስላልቻሉ ባላ (ወስፈንጥር) በመጠቀም ጥቃት ጀመሩ፡፡ በመስፈንጥሩ ድንጋዮችንና በእሳት የተቀጣጠሉ ችቦዎችን ወደ ካዕባ ወረወሩ፡፡ የካዕባ ጣራ ተቃጠለ ቅዱሱ ካዕባ በከፊል ወደመ፡፡
*(አል-ሱዩጢ - ታሪኩል ኹላፋእ፣ ገጽ 209)*

## አል-ወሊድ እና ሃሩን አል-ረሺድ

የተለየ ነገር የለም በሚያሳዝን ሁኔታ የተለመደ ደንብ የሆነበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡
አል-ወሊድ ኢብን የዚድ ኢብን አብድል መሊክ ሌላኛው የኡመያዎች ኸሊፋ ነበር፡፡ እርሱም በሰካራምነቱ ነው የሚታወቀው፡፡

አንድ ሌሊት ከአንዷ ቅምጡ ጋር እየጠጣ አመሸና እስከ ንጋት ድረስ ፌሽታው ቀጥሎ ለሱብሂ ሰላት የሚደረግ ጥሪ (አዛን) ተሰማ፡፡ በዚህን ጊዜ ሶላቱን መምራት (ማሰገድ) ያለበት ቅምጧ እንደሆነች ምሎ ተናገረ፡፡ ከዚያም ቅምጧ የኸሊፋውን ካባ ለብሳ በሀይለኛ ስካር ውስጥ እንዳለች ሶላቱን አሰገደች፡፡

*(አል-ዲያር በክሪ፦ ታሪኩል ከሚስ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 320 በነዋብ አህመድ ሁሴን ኻን ታሪክ አህመዲ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ በገጽ 328 ላይ የተጠቀሰ፡ ኢብን ሻክር፦ ፈዋቱል ወፍያት፣ ቅጽ 4፡ ገጽ 256-9)*

ከዕለታት አንድ ቀን በአስራዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የምትገኝን አንዷን ልጁን አንዷ የሴት ባሪያ አገልጋዩ ባለችበት ሲተናኮላት አየች።

ከዚያም ይህ ኢስላም አይደለም። ይህ የመጁሲ ሀይማኖት ነው። በዚህን ጊዜ አል-ወሊድ ስንኝ (ግጥም) አነበነበ።

«*ለሰዎች ምላስ (ወሬ) የሚጨነቅ ሰው እያዘነ ይሞታል። ብልጥ ሰው የፈለገውን ደስታ ሁሉ ያገኛል።*»

*(አል-ሱዩጢ፦ ታሪኩል ኹለፋእ፡ ገጽ 291)*

ገናናው የአባሲያዎች ኸሊፋና «የአንድ ሺህ አንድ ሌሊቶች» ዋነኛ ባህሪ የሆነው ስመጥርና ታላቅ ኸሊፋ ተብሎ የተነገረለት ሃሩን አል-ረሺድ ከአንዷ የማች አባቱ ቅምጥ ጋር አንሶላ ለመጋፈፍ ፈለገ።

በዚህን ጊዜ ሴትየዋ እንዲህ ዓይነቱ ነገር የስጋ ዝምድና ካላቸው ሰዎች ጋር እንደመተኛት እንደሚቆጠርና እንደ እናቱ መቆጠር እንዳለባት በግልጽ ነገረችው። በዚህን ጊዜ ሃሩን አል-ቃዲ አቡ ዩሱፍን አስጠራና ፍላጎቱን ያማላ ዘንድ ቃዲው በነገሩ ላይ ፍርድ እንዲሰጥ ተደረገ። በዚህን ወቅት ቃዲው እንዲህ አሉ፡-

«ከእነዚህ ሶስቱ የትኛው ይበልጥ እንደሚደንቅ አላውቅም፡፡» የሙስሊሙን ንብረትና ደም እንዳሻ የሚጫወትበት እንጀራ እናቱን የማያከብረው ኸሊፋ ወይም የኸሊፋውን ምኞት ለማሟላት አሻፈረኝ የምትልዋ ባሪያዋ አገልጋይ ወይም አባቱን አዋርዶ ከእንጀራ እናቱ ጋር ይተኛ ዘንድ ለኸሊፋው ፍርድ የሚሰጥ ቃዲ ተብዬው፡፡
*(አል-ሱዩጢ ታሪኹል ኹለፋእ፡ ገጽ 291)*

## በአላህ ፍትሃዊነትና በነቢዮች እንከን-የለሽነት (እስመህ) እምነት ላይ ያለው ተጽዕኖ

ሱኒዎች «በምርጫ ለተሾሙት ኸሊፋዎች» ያላቸው አስተሳሰብ ሙስሊሙን ህብረተሰብ ለፖለቲካ ድቀት እንደዳረገውና ያለምንም መስፈርትና ስነ-ምግባር ለስልጣን ባደረጉት ተጋድሎና ወታደራዊ ሀይል ብቻ ስልጣን ላይ የወጡትን መገዛትና መታዘዝ ግድ እንደሆነባቸው ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡

በዚህም የተነሳ ህዝቡ ለሀይማኖታቸው ያላቸውን እይታና እምነት በጥቅሉ እንዲቀይሩ ተገደዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ አብዛኛዎቹ ኸሊፋዎች ምንም የሀይማኖት ስሜት የሌላቸውና ጨዋነት የተነፈጋቸው የአላህ ፍራቻ የራቃቸው ነበሩ፡፡

የእንዲህ ዓይነቶቹን ኸሊፋዎች ኺላፋህ ተቀባይነት እንዲያገኝ ለማድረግና ጥፋታቸው ለመደባበስ ነቢዮች እንኳን ስህተት ይፈጽማሉ፣ ከሐጢአት የፀዱ አይደሉም ብለው አምነው ሌላውንም ለማሳመን ጥረት አደረጉ፡፡ ስለዚህ የነቢዮች እስመህ (ሐጢአት የለሽ መሆን) እምነት ተቀየረ፡፡

ምንም እንኳ ለኸሊፋነት ቦታ የሚበቁ ዕውቀት የተካኑና አላህን ፈሪ የሆኑ ስልጣን ላይ ከነበረው መሪ በብዙ መልኩ የሚሻሉ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የነበሩ ቢሆንም ቦታው ከሚገባቸው በማንኛውም መስፈርት ብልጫ ላላቸው ሰዎች ይልቅ ቦታው ለማይገባቸው የበታች ለሆኑ ሰዎች ቅድሚያ መስጠት ችግር የለውም ለማለት ተገደው ነበር፡፡

ሺዓዎች ቦታው የሚገባው በላጭ ሰው እያለ ለማይገባው ለበታች ሰው መስጠት ጤናማ አስተሳሰብ አይደለም በማለት የዚህን አሰራር መጥፎነት ሲያጋልጡ ሱኒዎች ደግሞ አንድ ነገር በራሱ ጥሩም መጥፎም የለውም፣ አላህ ያዘዘው ማንኛውም ነገር ጥሩ ነው፣ አላህ የከለከለው ማንኛውም ነገር ደግሞ መጥፎ ነው ብለው ያውጃሉ፡፡

«ምክንያት»ን በተመለከተ በሀይማኖት ውስጥ የትም ቦታ ይገኛል ብለው ይክዳሉ፡፡ የሱኒዎች «ህጋዊ ኺላፋህ» አስተሳሰብ በእስልምና አስተምህሮ ላይ የሚያሳድረውን

አጠቃላይ ተጽዕኖ በዝርዝር ለማስቀመጥ ይህ ቦታው አይደለም፡፡ በአጭሩ የሚከተሉት ነጥቦችን ማንሳት በቂ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ፡፡

እነዚህን ኸሊፋዎች ከጥፋት ለማዳንና ለመከላከል እንዲሁም ህጋዊ ለማስመሰል ነቢዮችን እስማህ (እንከን-የለሽነት) መንፈግ ሳይሆን አላህንም «ፍትህ» አልባ አደረጉት፡፡
ከዚህ ተነስተን በገዲር ኹም የወረደውን አያህ አስፈላጊነትና ጥቅም በቀላሉ መረዳት ይቻላል፡፡

«አንተ መልዕክተኛ ሆይ! ከጌታ የተወረደልህን መልዕክት (የዓሊን ኺለፋህ በተመለከተ) አውጅ፡፡ ይህንን ካላደረግክ መልዕክቱን (የአላህ) ሁሉ አላደረስክም፡፡ አላህ ከሰዎች (ተንኮልና እኩይ ተግባር) ይጠብቀሃል፡፡»

የእስላማዊ እምነትና ተግባር ንጽህና በአሊ ኺላፋህ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ያ አንድ መልዕክት ባይተላለፍ ኖሮ ሁሉም መልዕክት እንዳልተላለፈ ይቆጠር ነበር፡፡ የሀይማኖቱ አጠቃላይ ደህንነት ከቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) በኋላ በዓሊይ ኸሊፋነት ላይ የተመሰረተ ነበር ማለት ነው፡፡

**ሺዓነት ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነው?**

ተቃዋሚዎቻችን የቀደምት ኸሊፋዎችንና ኢማሞችን የሰልጣን ሽግግር በመመልከት ሺዓነት ኢ-ዲሞክራሲያዊ ነው ብለው ያምናሉ፡፡

አስራ ሁለቱ ኢማሞች በሙሉ ከአንድ ቤተሰብ የተገኙ ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ አራት ኸሊፋዎች ደግሞ ከተለያየ ጎሳ የተውጣጡ ነበሩ፡፡ ስለዚህ የሱኒ መዝሀብ በመሰረቱ ዲሞክራሲያዊ እንደሆነና ከሁሉ ተመራጭ እንደሆነ አድርገው ይናገራሉ፡፡ በአንፃሩ ግን የሺዓ ኢማማህ በዘር የሚተላለፍ ከአንድ ቤተሰብ የመነጨ በመሆኑ ጥሩ አካሄድ አይደለም ብለው ይገምታሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ አንድ የመንግስት ስርዓት በራሱ ጥሩ ወይም መጥፎ ሊሆን አይችልም፡፡ የጥሩነቱ ወይም መጥፎነቱ መጠን የሚለካው ስልጣኑን ይዘው የመሪነቱን ስራ በሚሰሩ ሰዎች የመጥፎነት ወይም ጥሩነት መጠን ነው፡፡ በዚህ መሰረት በሺዓዎች እምነት መሰረት መሪው ወይም ኢማሙ መዕሱም (እንከን-የለሽና ከማንኛውም እኩይ ተግባራት የፀዱ) ናቸው ማለት ስርዓተ-መንግስቱም (አስተዳደሩም) እጅግ ፍጹምና ፍትሃዊ ነው ማለት ነው፡፡

በአንድ በኩል የመጀመሪያው ኢማም የሆኑት በኢማም ዓሊ የአጭር ጊዜ አስተዳደር የነበረው ወደር የለሽ ፍትህና

በሌላው በኩል ደግሞ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለመጨረሻው ኢማም - ኢማም አል-መህዲ (የመገለጫውን ጊዜ አላህ ያፍጥንና) የተናገሩት ትክክለኛነቱ የተረጋገጠ ሀዲስ ይገኛ ል፡-

«በጭቆናና ኢ-ፍትሃዊነት የምትሞላዋን ምድር በፍትህና በእኩልነት ይሞላል፡፡»

*(አቡ ዳውድ፡- አል-ሱነን፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 106 9፣ አህመድ፡- አል-ሙስነድ ቅጽ 1 ገጽ 377፣ 430፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 28፣ አል-ሃኪም፡- አል-ሙስተድረክ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 557፣ 865)*

ስለዚህ መነሻችን እንዲሁ ሆን ተብሎ ያለ ማስረጃ የተቀመጠ አይደለም ሁለተኛው ማስተዋል ያለብን ነገር ደግሞ ሁሉም የሱኒ ኸሊፋዎች ከአቡ በክር ጀምሮ እስከ ሙእተሲም ቢላህ (የአቢሲያዎችን ሥርወ-መንግሥት በ 656 ሂጅሪያ/1258 ዓ.ክ በመገርሰስ ኢራንን በገዛ በሞንጎሊያዊው ንጉስ ሆላኮኻን የተገደለ) ያሉት በሙሉ ከቁሬይሽ ነበሩ፡፡

ታዲያ ይህ ማለት አንድ ቤተሰብ ከምሥራቅ ቻይና እስከ ስፔን ያሉትን ሙስሊሞች ለስድስት ተኩል ምዕተ ዓመታት ገዙ ማለት አይደለም?

ሦስተኛ የሱኒ ኸሊፋህ ሥርዓት በዲሞክራሲ ላይ የተመሠረተበት አጋጣሚ ታይቶ አይታወቅም፡፡ የመጀመሪያው ኸሊፋን ብንመለከት ስልጣን ለመቆናጠጥ

የበቃው ህዝቡን ባሳተፈ ምርጫ ሳይሆን በጥቂት ሰሃባዎች በተደረገ ጉባዔ ከብዙ ብጥብጥና አተካሮ በግፊት የተገኘ ሹመት ነው:: ሁለተኛው ኸሊፋ የተመረጠው ደግሞ በመጀመሪያው ኸሊፋ ነው:: ሦስተኛ ኸሊፋ የተመረጠው ደግሞ ለይስሙላ በአምስት ሰዎች በእውነቱ ግን በአንድ ሰው ነው:: ሙዓዊያህ ደግሞ ሥልጣኑን የተረከበው በወታደራዊ ሃይል ነው:: ከሱ በፊት የኦሊጋርኪ (በጥቂት ሰዎች/ቡድን ብቻ የሚያዝ ስልጣን) ጥሩ ምሳሌ ነው ማለት ሲቻል ከሱ በኋላ ደግሞ ሞናርኪ (ንጉሳዊ አገዛዝ) ሆኖ መጣ::

የዲሞክራሲ መገለጫ ስለሆነው እኩልነትን በተመለከተ የቀደምት መሪዎች ተግባር ምን ይመስል ነበር የሚለውን ማየት ይቻላል::

ዑመር አረብ ያልሆነ ሰው አረቢያ ውስጥ ካልተወለደ በስተቀር አረብ ከሆነ ሰው መውረስ እንደማይችል ውሳኔ አስተላልፎ ነበር::

*(ማሊክ:- አል-ሙወጠእ፣ ቅጽ 2: ገጽ 60)*

በተጨማሪም ሱኒዎች ወደ ድንቁርናው ዘመን ደግሞ በመመለስ በአብዛኛው አረብ ያልሆነ ሰው አረብ የሆነችን ሴት ማግባት አይፈቀድለትም ነበር:: ከዚህም አልፎ ቁሬይሽ ወይም ሓሺም ያልሆነ ሰው ቁሬይሽ ወይም ሓሺም የሆነችዋን ሴት ማግባት አይችልም ነበር::

በሺዓ ህግ መሠረት ግን ባሪያ (ነፃ የወጣ እንኳን ቢሆን) ነፃ የሆነችን (ባሪያ ያልሆነች) ሴት ማግባት ይቻላል:: *(አል-ጀዝሪ:- አል-ፊቂህ አለል መዛህብል አርበዓ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 60)*
እላይ የተጠቀሰው ሁኔታ በሙሉ በሁሉም ዘንድ የሚታወቀውን ቀጥሎ ያለውን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አዋጅ በመጻረር ነው ማለት ይቻላል::

«*አረብ፣ አረብ ባልሆነው ላይ የበላይነት የለውም:: አረብ ያልሆነው አረብ በሆነው ላይም የበላይነት የለውም:: ነጭ በጥቁር ላይ ጥቁርም በነጭ ላይ የበላይነት የለውም:: የሰው ልጅ ለአላህ ያላቸው ተቅዋ (ፍራቻ) መጠን ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንኛውም መስፈርት አይበላለጡም:: የሰው ልጅ በሙሉ ከአደም ነው፣ አደም ደግሞ ከአፈር ነው::*»
*(አል-ሱዩጢ:- አል-ዱሩል መንሱር፣ ቅጽ 6፣ ገጽ 98)*

በተጨማሪም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባሪያ የነበረውንና በኋላ ነፃ የወጣውን ዜይድ ኢብን ሀሪስን የአጎቱን ልጅ በመዳርና ለኢትዮጵያው ባሪያ ቢላል ቁሬይሻዊት የሆነችዋን የአብዱረህማን ኢብን አውፍን እህት ለጋብቻ በመስጠት በተግባር ያስቀመጡትንና በፍትህ ያቋቋሙትን ሥርዓት በመጣስ ነው አረቦች ቀድሞ ወደ ነበረው ጃሂሊያ የተመለሱት::
*(ኢብኑል ቀይም:- ዛዱል መዓድ፣ ቅድ 4፣ ገጽ 22)*

የሺዓ ህግ በሚከተለው መልኩ በግልጽ ያስቀምጣል:- «ሁር (ነፃ) የሆነችን ሴት ለባሪያ መዳር ይፈቀዳል፣ አረብ

የሆነችን ሴትም አረብ ላልሆነ መዳር ይቻላል፡፡ ከበኒ ሓሺም የሆነች ሴት ከበኒ ሓሺም ያልሆነ ወንድ ወይም ከበኒ ሓሺም የሆነን ወንድ ከበኒ ሓሺም ያልሆነች ሴት ጋር መጋባት ይችላል/ትችላለች፡፡ እንዲሁም ከሀብታም ወይም ከተማረ ቤተሰብ የሆነችን ሴት አነስተኛ ትምህርት ወይም ሀብት ወይም የማይከበር ሙያ ካለው ሰው ጋር መዳር ይፈቀዳል፡፡

*(አል-ሙሀቂቅ አል-ሂሊ፡- ሸራኢኡል ኢስላም (ኪታቡ አል-ኒካህ) ቅጽ 4፣ ገጽ 300)፣ አል-ሃኪም፡-ምንሀጁሳሊኒን፣ (ኪታብ አል-ኒካህ) ቅጽ 2፣ ገጽ 279)*

በጦርነት ጊዜ ከምርኮ የሚገኘን የንብረት ክፍፍል በተመለከተ ነቢዩ(ሰ.ዐ.ወ) በፍትህና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አሰራር አቋቁመው ነበር፡፡ በዘመቻው ላይ ለተካፈሉት አባላት በሙሉ እኩል እንዲከፋፈል አድርገው ነበር፡፡

አቡ በክር ይህንኑን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈለግ ተከትለው ይሠሩ ነበር፡፡ ነገር ግን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ ከአራት አመት በኋላ በ15ኛው ሂጅራ ዑመር አሠራሩን በመቀየር ለተለያዩ ሰዎች፣ ጎሳዎችና ነገዶች የተለያየ አመታዊ ድርሻ (ክፍፍል) አደረገ፡፡ በዚህም መሠረት ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አባስ በዓመት 12000 ወይም 2500 ዲናር፣ ለአኢሻ 12000 ዲናር በዓመትና ለተቀሩት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤቶች ለእያንዳንዳቸው በዓመት 10000 ዲናር፣ በበድር ዘመቻ ላይ ለተካፈሉት ለእያንዳንዳቸው 500 ዲናር፣ በበድርና

በሁዴይቢያህ መካከል ለተቀላቀሉት ደግሞ 4000 ዲናር፣ ከሁዴይቢያህ በኋላና ከቃዲሲያህ በፊት ለተቀላቀሉት ደግሞ ለእያንዳንዳቸው 3000 ዲናር ይደርሳቸው የነበረ ሲሆን የዓመታዊ ክፍያ መጠኑ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ሄዶ በዓመት እስከ 2000 ዲናር ደርሶ ነበር።

*(አል-ጠበሪ - አል-ታሪክ፡ ቅጽ 4፣ ገጽ 2411-4 ኒኮልሰን R.A. ኤ ሊተረሪ ሂስትሪ ኦፍ አረብስ ገጽ 187)*

ይህ የአሠራር ሥርዓት የሙስሊሙን ማህበረሰብ በሙስናና በራስ ወዳድነት ውስጥ ዘፈቀው። ሀብትና ንብረትን ማካበት ብቸኛው ዓላማና ራዕይ እየሆነ መጥቶ ከሃይማኖት የሚገኘው ጥቅም ከዚህ ያለፈ እንዳልሆነ የታመነበት ጊዜ ላይ ደረሱ። አስተሳሰባቸው በሙሉ በማቴሪያል (ቁስ) ላይ የተመሰረተ ሆኖ ነበር። ሀብትን በዜጎች መካከል እኩል የማከፋፈል አሠራር ሊዋጥላቸውና መቋቋም አልቻሉም። ዓሊ የኸሊፋነቱን ቦታ እንደተረከበ በፍትህና እና እኩልነት ላይ የተመሰረተ የሀብት ክፍፍልን አስመልክቶ ያደረገው ንግግር በቀላሉ የሚዋጥላቸውና በደስታ የሚቀበሉት ሥርዓት አልነበረም። ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ኢማም ዓሊ (ዐ.ሰ) የሚከተለውን እንደተናገረ ይነገራል።

«ከሙጀሂሮችም ሆነ (ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ከመካ ወደ መዲና የተሰደዱ) ከአንሷሮች (ስደተኞቹን በመወገን በመዲና የመጀሃሮቹ ረዳት የሆኑ) የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሃቦች በመሆናችሁ አንዱ በሌላው ላይ የበላይነት እንዳለው የሚሰማችሁ ካላችሁ አንጸባራቂው ብልጫ ነገር በአላህ

ፊት ብቻ መሆኑን አስታውሱ:: ለአላህና ለነቢዩ ጥሪ ምላሽ የሰጠ፣ የሃይማኖቱን እውነታ ተቀብሎ ፈቅዶ የገባበት፣ ወደ ቂብላችን ፊቱን ያዞረ ማንኛውም ሰው በኢስላም ውስጥ ሙሉ መብትና በግዴታዎቹ ላይ እኩል ገደብ አለው:: እናንተ የአላህ አገልጋዮች ናችሁ:: ሀብትና ንብረቱ በአጠቃላይ የአላህ ነው:: በመካከላችሁ እኩል ይከፋፈላል:: አንዱ ከሌላው የተለየ ጥቅም የሚያገኝበት አሠራር አይኖርም::

*(ኢብን አቢል ሀዲድ-ሸርህ፣ ቅጽ 7፣ ገጽ 35-7፣ በተጨማሪም ከኢማም ዓሊ ጥቅሶች በነህጁል በለጋህ የጥቅስ ቁጥር 126 ይመልከቱ)*

ከዓሊ (ዐ.ሰ) ኸሊፋነት በፊት ባሉት ሃያ ዓመታት ውስጥ በእኩልነት ላይ ያልተመሠረተ የሀብት ክፍፍል የለመዱ ወገኖች ዓሊ ሁኔታዎችን አይቶ አስተያየት እንዲያደርግና ቀደም ሲል የተለመደውን አሠራር እንዲከተል ምክር ሰጡት:: ሆኖም ምንም ለውጥ ሳይመጣ ሲቀርና ዓሊ ለእስላም ህግጋትና መርሆዎች የድርድር ቀዳዳ እንደሌለው ሲያረጋግጡ በዓሊ ላይ ሴራ ማቀነባበር ጀመሩ::

ኡመያዎች ድልን ከተቀዳጁ በኋላ ኢ-ፍትሃዊና እኩል ያልሆነው የሀብት ክፍፍል ሥርዓት በሙስሊሙ መካከል ዳግም አንሰራርቶ ቀጠለ:: አንድ ሰው እስላምን ቢቀበል እንኳ የሙስሊምነቱን መብት አያገኝም ነበር:: እንዲያውም ሙስሊም ያልሆኑ ወንድሞቻቸው የተሻለ መብት ነበራቸው:: የሙስሊሞቹ ሁኔታ ሙስሊም ካልሆኑት እንኳ የባሰ ነበር ማለት ነው:: ሙስሊም ያልሆኑ የአካባቢው

ነዋሪዎች ጅዝያህ የተሰኘ ቀረጥ ብቻ ይከፍሉ ነበር፡፡ ሙስሊሞቹ ግን ጅዝያም ዘካም ይከፍሉ ነበር፡፡

በዑመር አብድልዓዚዝ ሁለት ዓመት ተኩል የአስተዳደር ዘመን በስተቀር በኡመያዎች ዘመነ መንግስት ጅዝያህ ከሁሉም አረብ ያልሆኑ ዜጎች (ሙስሊሞችን ጨምሮ) ይሰበሰብ ነበር፡፡

*(አል-ጠባሪ-አል-ታሪክ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 1354-1367)*

ይህ ሥርዓት ምን ያህል እስላምን እንደጎዳና ሊያስገኝ የሚችለው ጥቅም ይህ የማይባል ኢምንት መሆኑን መገመት አያዳግትም፡፡

ዋና ከተሞቻቸውና ከተሞቻቸው «ኢስላማዊ» ናቸው የተባሉት ሀገራት በሙሉ እንኳ ሳይቀር ወደ ኢስላም መቀየር አልቻሉም ነበር፡፡ የአረቦችን ወረራ ለጥቂት ጊዜያት ብቻ መቋቋም የቻሉትና ከመጀመሪያው መቋቋም በኋላ ምላሽ የሰጡትና በእስፔንና ከዚያም በፈረንሳይ ላይ በሚደንቅ ሁኔታ አገልግሎት የሰጡት ባርበሮች እንኳን የመጀመሪያው የሺዓ መንግስት በሞሮኮ እስኪቋቋም ድረስ አልተለወጡም ነበር፡፡

የኢማም ሐሰን (ዐ.ሰ) የልጅ ልጅ የሆነውና የኢድሪሳዊ ሥርወ-መንግስት (**789-985**AD) መስራች የሆነው ኢድሪስ ኢብን አብደላህ በነሱ ላይ በዘመተ ጊዜ አብዛኞቹ ሙስሊሞች አልነበሩም፡፡ ይህ የመጣው ደግሞ ቀደም ሲል በነበሩት ብልሹ ሥርዓቶች ምክንያት ነው፡፡

የዚድ ኢብን አብዱልመሊክ የኡመያዎችን ዘውድ ባጠለቀ ጊዜና የዚድ ኢብን አቢ ሙስሊም ዲናርን የሞሮኮ ገዢ አድርጎ በሾመ ጊዜ፣ ይህ የሞሮኮው ገዥ የዚድ ከሰለሙት (ሙስሊም ከሆኑት) ዜጎች ደግሞ ጅዝያ (ቀረጥ) ይሰበስብ እንደነበረና ሙስሊም ከመሆናቸው በፊት (ከመስለማቸው በፊት) ወደ ነበሩበት መንደር እንዲመለሱ እንዳደረገ እንሰማለን፡፡

*(አል-አሚን - የሺዓ ኢስላም ኢንሳይክሎፒዲያ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 38-41)*

የኢድሪሳዊው ሥርወ-መንግስት የፖሊሲ ለውጥና ኢስላማዊ መብትን ለሁሉም ሙስሊሞች ለማዳረስ ያደረገው መረባረብ የባርበሮችን መለወጥ (መስለም) አስገኘ፡፡

የአረብ የበላይነት አባዜ ምን ያህል ውስብስብና ሥር የሰደደ ስለመሆኑ ለማየት የቀደምት ገዢዎችን አስተሳሰብና ውሳኔ ማጤን በቂ ይሆናል፡፡ ይኸውም በአረቦች የተያዘ ሀገር ውስጥ አንድ ሰው ቢሰልም (ሙስሊም ቢሆን) ያ ሰው እንደ ሙስሊም አይታይም፣ ኢስላማዊ መብቶችንም አያገኝም፡፡ ይህንን ማግኘት የሚችለው ሙስሊም በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ለአንዱ የአረብ ጎሳ ደንበኛ ወይም አገልጋይ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ኢስላማዊ መብቱን ለማግኘት አልፎም ሙስሊም ለመባል ከአንዱ አረብ ጎሳ ጋር መወዳጀት እንደመስፈርት ይታይ ነበር ማለት ነው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ ወዳጆች «መዋሊ» በመባል ይታወቁ ነበር፡፡

እንደዚህም ሆነው ግን እኩልነትና ፍትህን መጎናጸፍ ይቅርና አምባገነን ጓዶቻቸው መሳቂያና መሳለቂያ ያደርጓቸው ነበር፡፡ እየተወሳሰበ የመጣውን ቢሮክራሲ ተገን በማድረግ እንደፈለጉ ይጫወቱባቸውና ክብር እንደሌለው ግዑዝ ነገር ይቆጥሮአቸው ነበር፡፡

አላሁ ተአላ ሙስሊሙን የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነቱን እንከን-የለሽና ስህተት አልባ ለሆኑት አስራ ሁለቱ ኢማሞች ብቻ በመስጠት፣ ጭቆናን፣ ራስ ወዳድነትን፣ ብጥብጥን፣ አሻጥርን፣ የይስሙላና የውሸት ምርጫን፣ የማህበራዊና የዘር አድሎ እንዲሁም የጎሳ ዘረኝነትን ከሥር መሠረቱ ፈነገለው፡፡

**በዘር የሚተላለፍ ስልጣን?**

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት የሺዓ መዝሀብ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቤተሰባቸው የማይወጣ በዘር የሚተላለፍ (ሥርወ-መንግስት) ለቤተሰባቸው ለማቋቋም ፈልገው ነበር (በርግጥ ሳይሳካላቸው ቀረ እንጂ) ብለው ያምናሉ፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከእንዲህ ዓይነቱ የራስ ወዳድነት ባህሪ የፀዱና የነጡ እንደሆኑ በመግለፅ የሺዓ መዝሀብ ከዚህ አንፃር የተሳሳተ ነው ብለው ይናገራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚሁ ሰዎች ደግሞ «ኢማሞቹ በሙሉ ከቁሬይሽ ናቸው» (አል-አኢመቱ ሚን ቁረይሽ) በማለት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተናግረዋል ብለው ይዘግባሉ፡፡

ታዲያ የዚህ ሀዲስ ትርጉሙ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለቤተሰባቸው ንጉሳዊ መንግስት ለማቋቋም ፈልገው ነው?
ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነዚህን ቃላት የተናገሩት «ከራስ ወዳድነት ስሜት» በመነሳሳት ነው ሊባል ነው ታዲያ? (አላህ ይቅር ይበለን)::

ቀደም ሲል እንደተገለፀው አቡ በክር አንሷሮችን (የመዲና ሰዎችን) ያረጋጋውና ዝም ያሰኛቸው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከቁሬይሽ እንደሆኑና አረቦች ቁሬይሽ ያልሆነን ሰው ኸሊፋ አድርገው መያዝ እንደማይችሉ በመናገር እንደሆነ ተወስቶአል:: ይህ የመከራከሪያ አጀንዳ ነበር አንሷሮችን ዝም ያሰኛቸው::

ይህንኑን ምክንያት መሠረት በማድረግ ከቅዱስ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) የቤተሰብ አባላት (እንደ ዓሊ ያሉት) ኸሊፋ ተደርገው ተመርጠው በነበረ ሁሉም በደስታ ይታዘዛቸው ስለነበረ ምንም ብጥብጥ ችግር አይኖርም ነበር ማለት ነው::

የዓሊ (ዐ.ሰ) ኸሊፋ ሆኖ መመረጥን በተመለከተ ሙስሊም ያልሆኑ ፀሀፊዎችም ብዙ ጽፈዋል:: ሚስተር ሴዲሎት የሚከተለውን ጽፎአል::
«የዓሊይ (ዐ.ሰ) በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መተካትና ስልጣን በዚህ መልኩ የመተላለፉ ስርዓት ከመጀመሪያው ተቀባይነት አግኝቶ በነበር ከዚያ በኋላ የተከሰተው አስከፊ ስቃይና

ኢስላምን በሙስሊሞች ደም ውስጥ የዘፈቀው አሳዛኝ ታሪክ አይፈጠርም ነበር፡፡»

*Sedillot, L.P.E.A., Historie des Arabes (የአረብኛ ትርጉም) ገጽ 126-7)*

እውነታው እንዲህ ዓይነቶቹ ተቀናቃኞች (ተቃዋሚዎች) ነጥቡን በፍጹም አላገኙትም፡፡ ሺዓዎች ኢማማህን (መሪነትን) ከዘር ወይም ውርስ ጋር አያይዘው አይተው አያውቁም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ኢማም (መሪ) መዕሱም (እንከን-የለሽ) መሆን አለበት፡፡ በሁሉም ህዝብ ላይ የበላይነትን የተጎናጸፈና በአላህ የተመረጠ መሆን አለበት፡፡

ሆኖም ኃያሉና ያሻውን አድራጊ አላህ በነብዩ ኢብራሂም በቅዱሱ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በዋለው ወደር የለሽ ፀጋው፣ እውነታውና በተግባር የታየው ሲሆን ነብያቱን የተኩ ኸሊፋዎች (ኢማሞች) በሙሉ የተገኙት ከነብያቱ ቤተሰብ ናቸው፡፡ የመሪነቱን (የኢማማነቱን) መስፈርት ማሟላት የሚችሉ ሰዎችም የተገኙት ከዘር ሐረጋቸው ብቻ ነበር፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት


- አቡ ዳውድ፣ ሱለይማን ኢብን አል-አሽ አስ አል-አዝዲ አስ-ሳጂስታኒ: አስ-ሱነን፣ ካይሮ (ቀ.የ)
- አቡ አል-ፊዳዕ፣ ኢማሙዲን፣ ኢስማኢል ኢብን አሊ ኢብን ማህሙድ አል-አዩቢ: አት-ታሪክ (አል-ሙኽተሰር አል-በሸር)፣ ቤሩት (ቀ.የ)
- አህመድ፣ አቡ አብደላህ፣ አህመድ ኢብን ሙሐመድ ኢብን ሀንበል: አል-ሙስነድ፣ ካይሮ 1313 ሂጅራ
- ሙሀመድ እና አሚሩ ዲን፤ ፋልኩነጃት ፊ ኢማማህ ወ ሰላት፣ ላሆር፣ 2ኛ እትም 1950
- አል-አላማህ አል-ሂሊ፣ አቡ መንሱር፣ አል-ሀሰን ኢብን ዩሱፍ ኢብን አሊ ኢብን አል-ሙጠሀር አል-አሰዲ: አል-ባቡ አል-ሃዲ አሸር፣ Eng. Tr, W.M. Miller, Luzac and Co.,London 1958
- አል-አሚን፣ ሀሰን: ኢስላሚክ ሺዓ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ ቤሩት (ቀ.የ)
- አል-አሚኒ፣ አሽ-ሼይክ አብዱ አል-ሁሴይን ኢብን አህመድ አት-ተብሪዚ አንነጃፊ: አል-ገዲር፣ 3ኛ እትም፣ ቤሩት 1967
- አምሪትሳሪ፣ ኡበይደላህ: አርጃሁ አል-መጣሊብ፣ ላሆር 1318 ሂጅራ
- አል-አያሺ፣ አቡ ነድር፣ ሙሀመድ ኢብን መስኡድ አስ-ሱለሚ አስ-ሰመርቀንዲ: አት-ተፍሲር፣ ተህራን (ቀ.የ)
- አል-በገዊ፣ አቡ ሙሐመድ፣ አል-ሁሴይን ኢብን መስኡድ አሽ-ሻፊዒ: አት-ተፍሲር (መዕሊሙ ፊ ተንዚል)፣ በየአል-ከንዚ አት-ተፍሲር የግርጌ ማስታወሻ ካይሮ 1955

- *አል-በይሃቂ፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን አል-ሁሴይን አን-ነይሳቡሪ አሽ-ሻፊዒ፡ ደላኢል ኢብን አን-ኑቡዋህ፣ ካይሮ 1969*
- *አል-ቡኻሪ፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን ኢስማኢል፡ አስ-ሰሂህ፣ ካይሮ (ቀ.የ)*
- *CARLYLE, T.: On Heroes, Hero-Worship and the Heroic in History, Edinburgh edition (n.d)*
- *DAVENPORT,J.: An Apology for Mohammad and the Koran, London, 1869*
- *አድ-ዲያር በክሪ፣ ሁሴይን ኢብን ሙሐመድ አሽ-ሻፊዒ፡ ታሪኹን ኸሚስ፣ ካይሮ 1283 ሂጅራ*
- *ፋይድ አል-ካሻኒት፣ ሙሐመድ ሙህሲን፡ አት-ተፍሲር (አስ-ሳፊ)፣ ጠህራን 1374 ሂጅራ*
- *አል-ጋንጂ፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን ዩሱፍ አሽ-ሻፊዒ፡ ኪፋየቱ ጣሊብ (ፊ መናቂብ አሊ ኢብን አቢ ጣሊብ)፣ አንነጀፍ አል-አሽረፍ (ኢራቅ) 1937*
- *አል-ጋዛሊ፣ አቡ ሀሚድ፣ ሙሐመድ ኢብን ሙሐመድ አት-ቱሲ አሽ-ሻፊዒ፡ ኢህያ ኡሉሚ ዲን፣ ቤሩት 1975*
- *ጊያሱ ዲን፣ ሙሐመድ ኢብን ጀላሉ ዲን ራም-ፑሪ ጊያሱ አል-ሉጋት፣ ነዋል ኪሾር ሉክናው 1867*
- *GIBBON, E: The Decline and Fall of the Roman Empire, The modern Library, New York, (n.d)*
- *አል-ሀኪም፣ አቡ አብደላህ፣ ኢብን አል-በዩ፣ ሙሐመድ ኢብን አብደላህ - አነይሳቡሪ አሽ-ሻፊዒ፡ አል-ሙስተድረክ (አላ አስ-ሰሂኸይን)፣ ሀይደረባድ 1335 ሂጅራ*
- *አል-ሀኪም፣ አስ-ሰይድ ሙህሲን አል-ጠባጠባኢ፡ ሚንሀጁ ሳሊሂን፣ ዳሩ ዘሀራ፣ ቤሩት፣ 10ኛ እትም*
- *አል-ሀሙዩ፣ አቡ ኢስሀቅ፣ ኢብራሂም ኢብን ሙሐመድ አል-ጁዋይኒ፡ ፋራኢድ አስ-ሲምጠይን፣ ቤሩት 1978*

- *ኢብን አብድል በር፣ አቡ ኡመር፣ ዩሱፍ ኢብን አብደላህ አል-ቁርጡቢ አል-ማሊኪ: አል-ኢስቲአብ ፊ ማዕሪፈቲ አል-አስሀብ፣ ካይሮ 1960*
- *ኢብን አቢ አል-ሐዲድ፣ ኢዙ ዲን አብዱ አል-ሐሚድ: ሻርህ ነህጂ አል-ባላጋህ፣ ግብጽ፣ 2ኛ እትም*
- *ኢብን አል-አሲር፣ አቡ አል-ሐሰን፣ ኢዙ ዲን፣ አሊ ኢብን ሙሐመድ አል-ጀዘሪ አሽ-ሻፊዒ: አል-ካሚል (ፊ ታሪክ)፣ ቤሩት 1965፣ ኡስዱ አል-ጋባህ፣ ካይሮ 1285 ሂጅራ*
- *ኢብን ሐጀር አል-አስቃላኒ፣ ሺሀቡ ዲን፣ አቡ አል-ፈድል፣ አህመድ ኢብን አሊ አሽ-ሻፊዒ: ፈትሁ አል-ባሪ (ፊ ሸርህ ሰሂህ አል-ቡኻሪ)፣ ካይሮ 1379*
- *ኢብን ሐጀር አል-ሀይተሚ፣ አቡ አል-አባስ፣ አህመድ ኢብን ሙሐመድ አል-መኪ አሽ-ሻፊዒ: አስ-ሰዋዒቂ አል-ሙህሪቃህ፣ (ቀ.የ)*
- *ኢብን ከሲር፣ አቡ አል-ፊዳ፣ ኢስማኢል ኢብን ኡመር አድ-ዲማሽቂ አሽ-ሻፊዒ: አል-ቢዳያህ ወ አንኒሃያህ፣ ቤሩት፣ 1ኛ እትም 1966*
- *ኢብን አል-ቀይም፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን የዚድ አል-ቀዝዊኒ: አስ-ሱነን፣ ደልሂ (ቀ.የ)*
- *ኢብን አል-ቀይም፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን አቢ በክር ኢብን ቀዩሚ አል-ጀውዚያህ አድ-ዲመሽቂ አሽ-ሻፊዒ: ዛዱ አል-ማዓድ፣ ካይሮ 1950*
- *ኢብን ቁተይባህ፣ አቡ ሙሐመድ፣ አብደላህ ኢብን ሙስሊም አድ-ዲናዋሪ: አል-ኢማማህ ወ ሲያሳህ፣ ካይሮ 1967 እና ቤሩት 1981*
- *ኢብን ሰዓድ አብደላህ፣ መሐመድ ኢብን ሰዓድ አል-ባግዳዲ: አል-ጠበቃት (አል-ከበር)፣ ቤሩት (ቀ.የ)*
- *ኢብን ሻኪር፣ ሙሐመድ ኢብን ሻኪር አል-ኩጡቢ: ፋዋቱ አል-ወፋያት፣ ቤሩት 1974*

- *IRVING, Washington (1783-1859): Mahomet and His Successors, London, (Part of the Astor Prose serios), 1905*
- ***አል-ጀሳስ፣ አቡ በክር፣ አህመድ ኢብን አሊ አር-ራዚ አል-ሀነፊ: አህካሙ አል-ቁርአን፣ ኢስታንቡል 1335 ሂጅራ***
- ***አል-ጀዚሪ፣ አብዱራህማን ኢብን ሙሐመድ: አል-ፊቅህ አለል መዛሂቢ አል-አርበዓ፣ ቤሩት 1919***
- ***አል-ኸጢብ አል-ባግዳዲ፣ አቡ በክር፣ አህመድ ኢብን አሊ አሽ-ሻፊዒ: ታሪክ ባግዳድ፣ ቤሩት (ቀ.የ)***
- ***አል-ካቲብ አል-ኸዋሪዝሚ፣ አቡ አል-ሙአየድ፣ አል-ሙወፈቅ ኢብን አህመድ አል-ሀነፊ: አል-መናቂብ፣ አል-ነጀፍ አል-አሸራፍ (ኢራቅ) 1965***
- ***አል-ካቲብ አት-ተብሪዚ፣ ወሊዩ ዲን ሙሐመድ ኢብን አብደላህ: ሚሽካቱ አል-መሳቢህ፣ (የእንግሊዝኛ ትርጉም)*** James Robson ***ፓኪስታን፣ 1975***
- ***አል-ኻዚን፣ አሽ-ሻፊዒ: አት-ተፍሲር (ሉባቡ አት-ተዕዊል ፊ መዓኒ አት-ተንዚል)፣ ካይሮ 1955***
- ***አል-ኸዛዝ፣ አቡ አል-ቃሲም፣ አሊ ኢብን ሙሐመድ ኢብን አሊ: ኪፋየቱ አል-አሳር፣ ኢራን 1981***
- ***አል-መጅሊሲ፣ አል-አላማህ፣ ሙሐመድ ባቂር ኢብን ሙሐመድ ተቂ: ቢሃሩ አል-አንዋር፣ ተህራን 1392 ሂጅራ***
- ***ማሊክ ኢብን አነስ አቡ አብደላህ፣ አል-አስበሂ አል-መደኒ: አል-ሙወጣዕ፣ ካይሮ 1353 ሂጅራ***
- ***አል-ማወርዲ፣ አቡ አል-ሀሰን፣ አሊ ኢብን ሙሐመድ ኢብን ሀቢብ አሽ-ሻፊዒ: አል-አህካሙ ሱልጣኒያህ፣ ካይሮ 1916***
- *MILLER, W.M.,* ***አል-አላማህን ይመልከቱ***
- *MIR AHMED ALI S.V., The Holy Quran, with English translation and commentary, Karachi, 1964*

- *ሚር ኸዋንድ፣ ሙሐመድ ኢብን ኸዋንድ ሸህ ኢብን ማህሙድ: ረውደቱ ሰፋዕ፣ ነዋል ኪሾር ሉክናው (ቀ.የ)*
- *አል-ሙፊድ፣ አሽ-ሼይክ፣ አቡ አብደላህ፣ ሙሐመድ ኢብን ሙሐመድ ኢብን አንኑዕማን: አል-ኢርሻድ፣ ተህራን፣ 1951 (የእንግሊዝኛ ትርጉም* I.K.H. Howard *ለንደን 1981)*
- *አል-ሙግኒያህ፣ ሙሐመድ ጀዋድ: ፊልሰፈት ኢስላሚያህ፣ ዳሩ ተዕሩፍ፣ ቤሩት 1978*
- *አል-ሙሐቂቅ አል-ሂሊ፣ ነጅሙዲን፣ አቡ አል-ቃሲም፣ ጃዕፈር ኢብን አል-ሀሰን፣ ኢብን ሰዒድ አል-ሁዛሊ: ሸራኢኡ አል-ኢስላም፣ (ኪታቡ ኒካህ)፣ አን-ነጀፍ አል-አሽረፍ (ኢራቅ) 1969*
- *አል-ሙሂብ አል-ጠበሪ፣ ሙሂቡዲን፣ አቡ አል-አባስ፣ አህመድ ኢብን አብደላህ አሽ-ሻፊዒ: ዘካኢር አል-ኡቅባ (ፊ መናቂቢ ዘዊ አል-ቁርባ)፣ ቤሩት 1974*
- *ሙስሊም፣ አቡ አል-ሁሴይን፣ ሙስሊም ኢብን አል-ሐጃጅ አን-ነይሳቡሪ: አስ-ሰሂህ፣ ካይሮ (ቀ.የ)*
- *አል-ሙታቂ አል-ሂንዲ፣ አላ ኡዲን፣ አሊ ኢብን ሁሳሚ ዲን: ከንዙል-ኡማል፣ ሀይደራባድ 1968*
- *ነጅሙ አል-ሀሰን፣ ሰይድ: አን-ኑቡዋህ ወ አል-ኺሊፋህ፣ ትርጉም ሊቃዕ አሊ ሃይደሪ፣ ሉክናው፣ 1964*
- *አን-ነሰኢ፣ አቡ አብዱራህማን፣ አህመድ ኢብን አሊ አሽ-ሻፊዒ: አል-ኸሳ ኢሱ አል-አለዊያህ፣ ግብጽ 1948 ሂጅራ*
- *ነዋብ አህመድ ሁሴይን ኻን: ታሪክ አህመዲ፣ ሃቅ ብራዘርስ (መክተበ ሪዝቪያ)፣ ላሆር (ቀ.የ)*
- *NICHOLSON, R.A. (1868-1945): A Literary History of the Arabs, Cambridge, 1979*
- *አል-ቁሚ፣ ሼይክ አባስ: ሰፊነት አል-ቢሃር፣ አን-ነጀፍ አል-አሽረፍ 1355 ሂጅራ*
- *አል-ቁንዱዚ፣ አስ-ሰይድ ሱለይማን ኢብን ኢብራሂም አል-ሀነፊ: የናቢዕ አል-መወዳህ፣ ኢስታንቡል 1301 ሂጅራ*

- *አር-ራዲ፣ አሽ-ሸሪፍ፣ አቡ አል-ሀሰን፣ ሙሐመድ ኢብን አል-ሁሴይን አል-ሙሳዊ፡ ነህጁ አል-በለገህ፣ ቤሩት 1967*
- *አር-ራዚ፣ ፈኽሩ ዲን፣ ሙሐመድ ኢብን ኡመር አሽ-ሻፊዒ፡ አት-ተፍሲሩ አል-ከቢር፣ ካይሮ 1938*
- *RIZVI, S.S.A: Prophethood, Dar-es-Salaam (Tanzania), 2nd ed., 1975*
- *Justice of God, Mombasa (Kenya), ed., 1980*
- *አስ-ሰዱቅ፣ አቡ ጃዕፈር፣ ሙሐመድ ኢብን አሊ ኢብን አል-ሁሴይን፣ ኢብን ባባዋይህ አል-ቁሚ፡ ዝላሉ ሸራኢዕ፣ አን-ነጀፍ አል-አሽረፍ 1966*
- *SEDILLOT, L.P.E.A., Historie des Arabes, (Arabic translation Adil Zu'aytir), Cairo, 1948*
- *ሲብጥ ኢብን አል-ጀውዚ፣ ሸምሱዲን፣ ዩሱፍ ኢብን ቂዛ-ኡጊል ኢብን አብደላህ አል-ሀነፊ፣ ተዝኪረት ኸዋሲ አል-ኡማህ፣ ተህራን (ቀ.የ)*
- *ሲዲቅ ሀሰን ኻን፡ መንሀጁ አል-ዉሱል ኢላ ኢስጢላሂ አሃዲሲ ረሱል፣ ህንድ (ቀ.የ)*
- *አል-ሱዩጢ፣ ጀላሉዲን፣ አብዱራህማን ኢብን አቢ በክር ኢብን ሙሐመድ አሽ-ሻፊዒ፡ ሉባቡ ነቁል ፊ አስባቢ ኑዙል፣ ከ ተፍሲር አል-ጀላለይን ጋር የታተመ፣ ዳሩል ኪታቢ አል-አረቢ፣ ቤሩት (ቀ.የ) «ታሪክ አል-ኹሉፋዕ»፣ ካይሮ፣ 1952 ንግሊዝኛ ትርጉም* Major H.s. Jarret, *በ «የኻሊፍ ታሪክ» ርዕስ ስር፣ ካራቺ 1977*
- *አድ-ዱሩ አል-መንሱር፣ ቤሩት (ቀ.የ)*
- *አል-ጠበሪ፣ ኢብን ጀሪር፣ ሙሐመድ፡ ታሪክ አል-ኡመም ወ አል-ሙሉክ፣ ለይደን 1980 እና ግብጽ (ቀ.የ)*
- *አት-ተፍሲር (ጃሚዕ አል-በያን ፊ ተፍሲሪ አል-ቁርዓን)፣ ግብጽ፣ ቡላቅ 1326 ሂጅራ*

- *አት-ተፍታዛኒ፣ ሰዓዱዲን፣ መስኡድ ኢብን ኡመር አሽ-ሻፊዒ: ሸርህ አቃይዲ አን-ነሰፊ፣ ኢስታንቡል፣ 1326 ሂጅራ*
- *ሸርሁ አል-መቃሲድ አል-ባሊባን፣ ኢስታንቡል፣ 1305 ሂጅራ*
- *አል-ቲርሚዚ፣ አቡ ኢሳ፣ ሙሐመድ ኢብን ኢሳ አስ-ሱለሚ: አል-ሰሂህ፣ ካይሮ 1292 ሂጅራ*
- *ዋሂዱ ዘማን: ተፍሲር ዋሂዲ፣ ላሆር (ቀ.የ)*
- *አንዋር አል-ሉጋህ፣ ባንግሎር 1334 ሂጅራ*
- *አል-ዋሂዲ፣ አቡል ሀሰን፣ አሊ ኢብን ሙሐመድ አል-ሻፊዒ፣ አስባቡል ኑዙል (ቀ.የ)*
- *አል-ያዕቁቢ፣ ኢብን ዋዲህ፣ አህመድ ኢብን ኢስሀቅ: አል-ታሪክ ቤሩት፣ 1960*
- *አል-ዘመኽሸሪ፣ ማህሙድ ኢብን ኡመር አል-ሀነፊ: አል-ተፍሲር (አል-ከሻፍ)፣ ቤሩት (ቀ.የ)*